የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# ቃለ ዓዋዲ




(ማር. ፩÷፲፭)

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድትና አስተዳደር ለማጠናከር
በ፳፻፱ ዓ.ም ለአራተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ

## የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ

## ጸሎት፤እምነትና ምግባር፡፡

በአንድ አምላክ በአብ፡ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በቅድስት ሥላሴ እያመንሁና እየተ ማፀንሁ፤ በእናቴ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ፊት ሰይጣንን እክዳለሁ፡፡ ይህችም የዘለዓለም መጠ ጊያ ምስክሬ ማርያም ናት፡፡

### አምነው የሚጸልዩት የሃይማኖት ጸሎት

፩ኛ/ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚ ታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን፡፡

፪ኛ/ ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን፡፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተ ካከል፡፡ ሁሉ በርሱ የሆነ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም፡፡ በሰማይም ያለ በምድርም ያለ፡፡ ስለ እኛ ስለ ሰው ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያምም ፈጽሞ ሰው ሆነ፡፡

ሰው ሁኖ በጳንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ፡፡ ታመመ ሞተ ተቀበረም በሦስተ ኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ፡፡ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፡፡ ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፡፡ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፡፡

፫ኛ/ ጌታ ማሕየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፡፡ እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት የተናገረ፡፡

፬ኛ/ ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበ ሰብዋት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን፡፡

፭ኛ/ ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናለምናለን፡፡

፮ኛ/ የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደ ርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን፡፡

### አምላክን የወለደች የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት፡፡

ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፡ መንፈሴም በአም ላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፡ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና፡፡ እነሆም፡ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው፡፡ ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትው ልድና ትውልድ ይኖራል፡፡ በክንዱ ኃይል አድር ጎአል፤ ትእቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤ ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታ ንንም ከፍ አድርጎአል፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፡፡ ባለጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአ ቸዋል፡፡ ለአባቶቻችን እንደተናገረ፤ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል (ሉቃ ፩፡፵፮—፶፭)

### ከቅዱስ ያሬድ መዝሙር

ለቤተ ክርስቲያን ስትል በአደባባይ በጥፊ የተመታህ አቤቱ፡፡

ይህን ማድረግህ እርስዋን በከበረ ደምህ ትቀድሳት ዘንድ ነው፡፡

ለርስዋ ሲል ታሥሮ መጎተትን የቻለ፡፡

የበደለውም በደል ሳይኖር ርኩስ ምራቅን ሲተፋበት የታገሡ፡፡

አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፡፡

## እናንተስ እንዲህ ጸልዩ

ስትጸልዩም እንደግብዞች አትሁኑ፤ ... አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል፤

አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ::... እናንተስ እንዲህ ጸልዩ:- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥት ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የእለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደ ምንል በደላችንን ይቅር በለን ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን:: (ማቴ ፮:፭—፲፫)

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ፤ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ላንች ሰላምታ ይገባል:: ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋራ ነውና ከተወደደ ልጅሽ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ::

## አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ

በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ:: (ኤፌ ፬:፬-፮)

## እምነትህን በሥራ አሳይ

ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የእለት ምግብንም ቢያጡ ከእናንተ አንዱም:-በደኅና ሂዱ እሳት ሙቁ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው::

ነገር ግን አንድ ሰው አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል:: እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል:: አንተ ከንቱ ሰው እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሰዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ:: ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ:: እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው:: (ያዕ ፪:፲፬—፳፮)

## ሕገ ኦሪትና ሕገ ወንጌል::

### አሥሩ ቃላተ ኦሪት

፩ኛ/ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ:: ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ:: በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድ ርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፤ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ:: አትስገድላቸው አታምልካቸውም::

፪ኛ/ የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ::

፫ኛ/ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፤ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው::

፬ኛ/ አባትህንና እናትህን አክብር::

፭ኛ/ አትግደል::

፮ኛ/ አታመንዝር::

፯ኛ/ አትስረቅ::

፰ኛ/ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመ ስክር::

፱ኛ/ የባለእንጀራህን ቤት...ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ::

፲ኛ/ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ (ዘፀአ. ፳÷፪-፲፯:: ዘሌዋ. ፲፱÷፲፰)

### ሕገ ወንጌል (እሷም የፍጹምነት የትሩፋት ሕግ ናት)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕገ ርትዕን በሕገ ትሩፋት በመፈጸም የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ፍጹማን ሁኑ እያለ ያስተማረው የፍቅ ርና የፍጹምነት ሕግ ፮ቱ ቃላተ ወንጌል እነሆ:-

፩ኛ/ ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታ ችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ "በከንቱ" የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል::..........

፪ኛ/ አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመ ኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል::

፫ኛ/ ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ:: እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል:: ("ንስሐ መግባቷን መምህረ ንስሐዋ ጎረቤቶቿ መስክረውላት ታግባ":: ብለው ሊቃውንት ይተረጉማሉ) (ትርጓሜ ወንጌል ማቴዎስ ፭÷፴፪)

፬ኛ/ ደግሞ ለቀደሙት:- በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ ከቶ አት ማሉ.... በራስህም አትማል፤....

ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው::

፭ኛ/ ዓይን ስለዓይን ጥርስም ስለጥርስ (ማለት) "ዓይን ቢጠፋ ዓይን ይጥፋ ጥርስ ቢሰ በር ጥርስ ይሰበር የተባለውን ሰምታችኋል (ዘፀ.፳፩÷፳፬ ዘሌ.፳፬÷፳ ዘዳ.፲፱÷፳፩):: .....ወአ ንሰ እብለክሙ ኢትትቃወምዎ ለእኩይ በእኩይ (፩ኛ ቆሮ.፮÷፯) (ትርጓሜ ወንጌል ማቴ. ፭÷ ፴፱) እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉን በክፉ አትቃወሙት «ወኢትማዖ ለእኩይ በእኩይ ክፉን ሰው በክፉ ነገር ድል እነሳዋለሁ፤ ክፉውን ግብር በክፉ ግብር አጠፋዋለሁ አትበል:: አላ ማዖ ለእኩይ በገቢረ

ስናይ፡፡ ከፉን ግብር በበጎ ግብር አጥፋው እንጂ ከፉውን ሰው በበጎ ግብር ድል ንሳው እንጂ"፡፡ (የግዕዙ ንባብ ከነትርጓሜው ሮሜ ፲፪፥፳፩)...

፭ኛ/ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በሐጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና፡፡ የሚወ ድአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮ ችም ያንኑ ያደርጉ የለምን? "ወንድማችሁን ብቻ የምታከብሩ ከሆነ አብልጣችሁ ምን ትሩፋት ሠራችሁ?....ወንድማቸውንማ ብቻ መውደድ አሕዛብስ ያደርጉት የለም? ..... እናንተስ ሰማያዊ አባታችሁ ሁሉን አስተካክሎ በመውደድ ፍጹም እንደሆነ ሁሉን አስተካክላችሁ በመውደድ ፍጹ ማን ሁኑ፡፡ (ትርጓሜ ወንጌል ማቴ.፭ ፥፵፯ —፵፰) (ማቴ. ፭፥፳፩—፵፰)፡፡

## ክፉውን በመልካም አሸንፍ፡፡

ተወዳጆች ሆይ፣ ራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፣በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው፣ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከም ራለህና፡፡ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አታሸንፍ፡፡ (ሮሜ. ፲፪፥፲፱)

## ፪ቱ ትእዛዛት፤እምላክን ውደድ ባለንጀራህን ውደድ፡፡

መምህር ሆይ ከሕግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው፡፡ ኢየሱስም አለው ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስሕም በፍጹም ሐሳብህም ውደድ፡፡ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት፡፡ ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርሷም ባለእንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት፡፡ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል፡፡ (ማቴ.፳፪፥ ፴፯-፵)

## ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው

እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር በማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና፡፡ አታመንዝር አትግደል አትስረቅ በውሸት አትመስክር አትመኝ የሚለው ከሌላ ይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል፡፡ ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው፡፡ (ሮሜ ፲፫፥፰—፲)

## ወንድምህ ቢበድልህ ምን ታደርጋለህ?

ወንድምህም ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው ቢሰማህ ወንድ ምህን ገንዘብ አደረግኸው ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረ መኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ፡፡...............

በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለው እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም፡፡ (ማቴ ፲፰፥፲፭—፳፪)

## አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ

እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህም ከወንድምህ

ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ:: አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባለጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው: ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስከት ከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም:: (ማቴ ፭፥፳፫—፳፮)

## አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ

እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል:: በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፣ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም? ወይም ወንድምህን ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም በዓይንህ ምሰሶ አለ:: አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ:: (ማቴ. ፯፥፩—፭)

## ፮ቱ ቃላተ ወንጌልን ያልፈጸሙ ይፈረድባቸዋል፤

(በመጨረሻው የፍርድ ቀን ጌታ ኃጥአንን እንዲህ ይላቸዋል) ተርቤ አላበላችሁኝምና ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና ታምሜ ታሥሬም አልጠየቃችሁኝምና:: እነርሱ ደግሞ ይመልሱና፦ ጌታ ሆይ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል:: ያን ጊዜ፦ እውነት እላችኋሁ፡ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል:: እነዚያም ወደ ዘለዓለም ቅጣት፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይሄዳሉ (ማቴ ፳፭፥ ፵፪—፵፮)

## ናሁ ቃለ ዐዋዲ ዘይሰብክ በገዳም (እነሆ የአዋጅ ነጋሪ ቃል በምድረ በዳ የሚጮኽ)

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ:: በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መጽሐፍ::

የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምጽ፤ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል፡ ጠማማውም የቀና መንገድ ይሁን፡ ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን፤ ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ ተብሎ እንደተጻፈ ለኃጢአት ሥርየት የንሥሐን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለችው አገር ሁሉ መጣ::

ስለዚህ ከእርሱ ሊጠመቁ ለወጡት ሕዝብ እንዲህ ይላቸው ነበር:: እናንተ የእፉኝት ልጆች፡ ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንሥሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ በልባችሁም አብርሃም አባት አለን ማለትን አትጀምሩ፤ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና:: አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጦአል እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል:: ሕዝቡም፦ እንግዲህ ምን እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር:: መልሶም፦ ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል፡ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ ይል ነበር:: ቀራጮችም ደግሞ ሊጠመቁ መጥተው፡ መምህር ሆይ፡ ምን እናድርግ አሉት:: ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው:: ጭፍሮችም ደግሞ፦ እኛ ደግሞ ምን እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር:: እርሱም በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፡ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ አላቸው::

ሕዝቡም ሲጠብቁ ሳሉ ሁሉም በልባቸው ስለ ዮሐንስ፡ ይህ ክርስቶስ ይሆንን? ብለው ሲያስቡ ነበር፡ ዮሐንስ መልሶ፡ እኔስ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመ ጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃ ችኋል፤ መንሹም በእጁ ነው፡ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፡ ስንዴውንም በጎተራው ይከ ታል፡ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥ ለዋል አላቸው።

ስለዚህ ሕዝቡን በብዙ ሌላ ምክር እየመከራቸው ወንጌልን ይሰብክላቸው ነበር። (ሉቃ ፫፥፲፭—፲፰)

## የአዋጅ ነጋሪው የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት

አይሁድም አንተ ማነህ? ብለው (ጠየቁት)። ................እርሱም (ዮሐንስ መጥምቁም)፤ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ (አዋጅ ነጋሪ) እኔ ነኝ አለ። በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ እነሆ የዓለምን ኃጢአት እሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ። አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል። ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው። እኔም አላውቀውም ነበር ዳሩ ግን ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ። ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ በእርሱ ላይም ኖረ። እኔም አላውቀውም ነበር ዳሩ ግን በውኃ አጠ ምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያ ጠምቅ እርሱ ነው አለኝ። እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬ አለሁ። (ዮሐ. ፩፥፲፱_ ፴፬)

## ጩኽ፤ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ንገር

በኃይልህ ጩኽ፤ አትቆጥብ፤ ድምጽህን እንደ መለከት አንሣ፤ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ለያዕቆብ ቤትም ኃጢአታቸውን ንገር። ነገር ግን ዕለት ዕለት ይሹኛል መንገዴንም ያውቁ ዘንድ ይወድዳሉ፤ ጽድቅን እንዳደረጉ የአምላካቸ ውንም ፍርድ እንዳልተው ሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል። ወደ እግዚአብሔርም ለመቅ ረብ ይወዳሉ። ስለምን ጾምን፤ አንተም አልተመ ለከትኸምን? ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን፤ አንተም አላወቅህምን? ይላሉ። እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፤ ሠራተኞቻ ችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ። እነሆ ለጥልና ለክርክር ትፆማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታ ላችሁ፤ ድምጻችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም እኔ የመረጥ ሁት ጾም ይህ ነውን? ሰው ነፍሱን የሚያዋርደው እንደዚህ በአለ ቀን ነውን? በውኑ እራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋ ለህን? እኔስ የመርጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቁ ዘንድ የተገፉትንስ አርነት ትሰዱ ዘንድ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራህንስ ለተራበ ትቆርስ ዘንድ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፤ ከሥጋ ዘመድህ እንዳት ሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፤ ጽድ ቅም በፊትህ ይሄዳል፤ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሀል። የዚያን ጊዜ ትጣ ራለህ እግዚአብሔርም ይሰማሃል፤ ትጮኻለህ እርሱም፤ እነሆኝ ይላል። (ኢሳ. ፶፰፥፩—፱)

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# ቃለ ዓዋዲ




የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና አስተዳደር ለማጠናከር
በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ለአራተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ

# የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ

## ስለ ማኅበረ እስጢፋኖስ ምርጫ፤ ስለ ማኅበረ ምእመናን የገንዘብ መዋጮና ስለ ፍትሕ መንፈሳዊ

### ስለ ማኅበረ እስጢፋኖስ ምርጫና ሹመት

አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉዋቸው የእግዚብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም:: ወንድሞች ሆይ፤ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን:: ይህም ቃል ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ:: በሐዋርያትም ፊት አቆሙዋቸው፤ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው (ግብ.ሐዋ፤ ፮፥፪__፯)

### ስለ ማኅበረ ምእመናን የገንዘብ አሰተዋጽኦ

ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩዋቸው ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ከአለው አንድ ነገርስ እንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም:: ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ፀጋ ነበረባቸው:: በመካከላቸውም አንድስኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር:: (ግብ.ሐዋ.ምዕ.፬፥፴፪__፴፭)::

ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለማዋጣት፡ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደደነገግሁት እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ:: እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፤ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ:: ስመጣም ማናቸውም ቢሆኑ የታመኑ የሚመስሉአችሁ ሰዎች ቸርነታችሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርሱ ዘንድ ደብዳቤ ሰጥቼ እልካቸዋለሁ፤ እኔ ደግሞ ልሄድ የሚገባኝ ብሆን ከእኔ ጋር አብረው ይሄዳሉ:: ..... እናንተም ወደምሄድበት ወደ ማናቸውም ሥፍራ በጉዞዬ እንድትረዱኝ (፩ኛ. ቆሮንቶስ ፲፮፥፩—፮)

### ስለ ፍትሕ መንፈሳዊ

ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? በዓለምስ ላይ ብትፈርዱ ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለሚሆን ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን? .... በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል፤ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን? እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በእርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ፤ ያውም ወንድሞቻችሁን:: (፩ኛ ቆሮ. ፮፥፪__፰)

## ማውጫ


መግቢያ... ፩—፫

**ምዕራፍ ፩**

**ጠቅላላ**

**አንቀጽ ፩**

አጭር ርእስ ፫

**አንቀጽ ፪**

**ትርጓሜ**

፩. "ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ" ማለት ፫

፪. የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ማለት በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ፬

**ምዕራፍ ፪**

በየደረጃው የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የወል ድንጋጌዎች ፭

**አንቀጽ ፫**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መቋቋም ፭

**አንቀጽ ፬**

የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አደረጃጀት ፮

**አንቀጽ ፭**

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዐላማ ፮

**አንቀጽ ፮**

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተግባር ፯

**ምዕራፍ ፫**

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አወቃቀር ፱

## አንቀጽ ፯

፩. አመሠራረት ........................................ ፱

፪. አወቃቀር ........................................ ፲

## አንቀጽ ፰

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
የሥራ አፈጻጸም ........................................ ፲

## አንቀጽ ፱

የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባርና የሥራ አፈጻጸም ........................................ ፲፫

## አንቀጽ ፲

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር
ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት ........................................ ፲፬

፩. የአባላት ዓይነትና ብዛት ........................................ ፲፬

፪. የአባላት አመራረጥ ........................................ ፲፭

## አንቀጽ ፲፩

ምርጫን ማሻሻል፣መሻርና ማጽደቅ ስለተመራጮች የአገልግሎት ዘመን ........................................ ፲፯

## አንቀጽ ፲፪

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር
ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፲፰

## አንቀጽ ፲፫

የአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፳፬

## አንቀጽ ፲፬

የአጥቢያ ሰበካ መንፈሣዊ አስተዳደር ጉባኤ ም/ሰብሳቢ
ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፳፯

## አንቀጽ ፲፭

ስለ ገዳማት አስተዳደርና ሥርዓተ ምንኵስና ........................................ ፳፯

## ምዕራፍ ፬


የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና
የሥራ ክፍሎች ........................................ ፴፫

**አንቀጽ ፲፮**

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና
የሥራ ክፍሎች መቋቋም ........................................ ፴፫

**አንቀጽ ፲፯**

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ፀሐፊ
ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፴፮

**አንቀጽ ፲፰**

የስብከተ ወንጌል ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፴፰

**አንቀጽ ፲፱**

የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፴፱

**አንቀጽ ፳**

የካህናት አገልግሎት ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፵፩

**አንቀጽ ፳፩**

የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፵፬

**አንቀጽ ፳፪**

የዕቅድና ልማት ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፵፯

**አንቀጽ ፳፫**

የምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፵፰

**አንቀጽ ፳፬**

የሕግ ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፶

**አንቀጽ ፳፭**

የንብረት፣የንዋየ ቅድሳትና የቅርሳ ቅርስ ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፶፩

**አንቀጽ ፳፮**

የሒሳብ ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፶፫

**አንቀጽ ፳፯**

የገንዘብ ቤት ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፶፭

አንቀጽ ፳፰

የቁጥጥር ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፶፯

አንቀጽ ፳፱

የሕንጻ ሥራ፣ጥገናና እድሳት ክፍል የሥራ ኀላፊነት ........................................ ፶፰

አንቀጽ ፴

የአኃዛዊ መረጃ /ስታትስቲክስ/ ክፍል ሥራና ኀላፊነት ........................................ ፷፩

ምዕራፍ ፭

ስለ ወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎች ........................................ ፷፫

አንቀጽ ፴፩

የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት የሥራ ክፍሎች
ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፷፫

አንቀጽ ፴፪

የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት ........................................ ፷፬

አንቀጽ ፴፫

የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፷፭

አንቀጽ ፴፬

የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ)
አባላት ........................................ ፷፯

አንቀጽ ፴፭

የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ
(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፷፰

አንቀጽ ፴፮

የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ........................................ ፷፱

አንቀጽ ፴፯

የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፸

ምዕራፍ ፮

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት
የሥራ ክፍሎች ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፸፪

**አንቀጽ ፴፫**

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
አመሠራረትና አደረጃጀት ................................................ ፸፱

**አንቀጽ ፴፬**

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት ........................ ፹

**አንቀጽ ፵**

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
ሥልጣንና ተግባር ................................................ ፹፩

**አንቀጽ ፵፩**

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር
ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት ........................................ ፹፪

**አንቀጽ ፵፪**

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር
ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር ........................... ፹፫

**አንቀጽ ፵፫**

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ........................................ ፹፭

**አንቀጽ ፵፬**

የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሥልጣንና ተግባር ................................. ፹፮

**አንቀጽ ፵፭**

የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር ............................ ፹፱

**ምዕራፍ ፲**

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ .......................... ፺፩

**አንቀጽ ፵፮**

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
አመሠራረትና አደረጃጀት ................................................ ፺፩

**አንቀጽ ፵፯**

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት .................. ፺፪

**አንቀጽ ፵፰**

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፹፰

**አንቀጽ ፵፱**

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ
አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት ........................ ፹፱

**አንቀጽ ፶**

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ
አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር ................ ፺

**አንቀጽ ፶፩**

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ........................ ፺፩

**አንቀጽ ፶፪**

የፓትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር ........................................ ፺፫

**አንቀጽ ፶፫**

የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር ................................ ፺፬

**አንቀጽ ፶፬**

ስለ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ ................................ ፺፮

**ምዕራፍ ፰**

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ................................................ ፺፮

**አንቀጽ ፶፭**

የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የአመራር ሥነ ሥርዓትና ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ
........................................................................ ፺፮

**አንቀጽ ፶፮**

ስለ ሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ገቢ ................................ ፺፯

**አንቀጽ ፶፯**

ስለ ሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ወጪ ................................ ፻፩

**አንቀጽ ፶፰**

የንብረትና ታሪካዊ ቅርሶች አመዘጋገብና አያያዝ ........................ ፻፪

**አንቀጽ ፶፱**

ስለሚሾሙ፣ስለሚቀጠሩና በበጎ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያገለግሉ ........ ፺፫

**አንቀጽ ፷**

የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች መብትና ግዴታ ........ ፺፯

፩. መብት ........ ፺፱

፪. ግዴታ ........ ፻፩

**አንቀጽ ፷፩**

የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መብትና ግዴታ ........ ፻፫

፩. መብት ........ ፻፫

፪. ግዴታ ........ ፻፬

**አንቀጽ ፷፪**

የአገልጋይ ካህናትን ብዛት ስለመወሰን ........ ፻፮

**አንቀጽ ፷፫**

ይህን ቃለ ዐዋዲ እና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በሚተላለፍ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ........ ፻፮

**አንቀጽ ፷፬**

የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ........ ፻፯

**አንቀጽ ፷፭**

የተፈጻሚነት ወሰን ........ ፻፱

**አንቀጽ ፷፮**

የቃለ ዐዋዲው መሻሻል ........ ፻፲

**አንቀጽ ፷፯**

ቃለ ዐዋዲው የሚጸናበት ጊዜ ........ ፻፲

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ
# የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና አስተዳደር ለማጠናከር
# በ፳፻፱ ዓ.ም ለአራተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ
# የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቃለ ዐዋዲ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በካህናትና በምእመናን ኅብረት በሰበካ ጉባኤ እንድትደራጅ ታስቦ በትእዛዝ አዋጅ ቍጥር ፹፫/፷፭ ተፈቅዶ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ታትሞ የወጣው አንደኛ ዓመት ቍጥር ፩ ቃለ ዐዋዲ፣ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም. ተሻሽሎ የወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማሻሻያ ቃለ ዐዋዲ፣ ታኅሣሥ ፲ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማሻሻያ ደንብ፣ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. የወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማሻሻያ ውስጠ ደንብ፣ በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ የተሻሻለው ቃለ ዐዋዲ እን ዲሁም በየጊዜው የተላለፉት መመሪያዎች መሻሻልና በአንድነት እንዲጠ ቃለሉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ቤተ ክርስቲያን በማኅበረ ካህናትና ምእመናን መደራጀቷ፣ በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር መመራቷ ከጥንት ያለ እንጂ አዲስ አለመሆኑን በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን በተለይም ግብረ ሐዋርያትን መሠረት በማድረግ፣

አመራሯና አስተዳደሯ በኢየሩሳሌም በተደረገው በሐዋርያት ጉባኤ ተመክሮና ተወስኖ በተላለፈው ሕግና ሥርዓት ይመራና በማኅበረ ካህናቱና ምእመናኑ ጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ ቅዱስ መንፈስ ባደረባቸው ኀላፊዎች ሥራ አስፈጻሚነት ይካሄድ እንደነበረ በመገንዘብ (የሐዋ ሥራ ምዕ.፮÷፩-፮)

## ቃለ ዐዋዲ

[illegible]

[illegible]

[illegible] (

ምዕ. ፲፯÷፩-፲፩)

[illegible]

[illegible]

ምዕ.፯÷፩-፲)

መንፈሳዊ ሥልጣን መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን ቃለ ዐዋዲ አውጥቷል፡፡

## ምዕራፍ ፩
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች
### አንቀጽ ፩
### አጭር ርእስ

ይህ ቃለ ዐዋዲ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና አስተዳደር ለማጠናከር በ፳፻፱ ዓ.ም. ለአራተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ "ቃለ ዐዋዲ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፪
### ትርጓሜ
### ፩. "የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ" ማለት

ሀ) በአጥቢያ ለተቋቋመውና ለሚቋቋመው የቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና በአባልነትም ለመመረጥ የሚችሉ ቤተ ክርስቲያንን በዕውቀታቸው፣ በጕልበታቸው፣ በሀብታቸውና በአገልግሎታቸው የሚረዱ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፣ ስብስብ ነው፡፡

ለ) በወረዳ ለተቋቋመውና ለሚቋቋመው የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉና የአጥቢያውን ሀብትና አገልግሎት የሚያስፋፉና የሚቈጣጠሩ ከእያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተወ

ከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የወረዳው ሰበካ መን ፈሳዊ ጉባኤ ነው።

ሐ) በሀገረ ስብከት ለተቋቋመውና ለሚቋቋመው የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚያስፈልጉትን አባላት ለመም ረጥና ለመመረጥ ከእያንዳንዱ ወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ ነው።

መ) በመንበረ ፓትርያርክ ለተቋቋመው የመንበረ ፓትርያርክ ሰበካ መንፈ ሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሀብትና አገልግሎት የሚያስፋፉ ከእያንዳንዱ መንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (የሀገር አቀፍ አጠቃላይ የቤተ ክርስ ቲያን ጉባኤ) ነው።

፪. **"የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ" ማለት በአጥቢያ ቤተ ክርስ ቲያን፣** በወረዳ፣ በሀገረ ስብከት፣ በመንበረ ፓትርያርክ በአጠቃላይ በየደረጃው በተቋቋሙትና በሚቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባ ኤያት በየራሳቸው መንፈሳዊ ጉባኤ የሚመረጥና ለየራሳቸው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አገልግሎት የተሠየመ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው።

፫. "የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ" ማለት-

ሀ) የገዳም አበምኔት /መምህር/ ወይም እመምኔት

ለ) የደብር አለቃ

ሐ) ለገጠር ቤተ ክርስቲያን ዋና ኀላፊ ሆኖ የተሠየመ ቄስ ገበዝ ወይም መርጌታ ነው፡፡

፬. "ሥራ አስኪያጅ" ማለት፡-

ሀ) የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ

ለ) የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ

፭. "ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ" ማለት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡

## ምዕራፍ ፪

## በየደረጃው የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የወል ድንጋጌዎች

## አንቀጽ ፫

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መቋቋም

፩. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በቃለ ዐዋዲው መሠረት ተቋቁሟል፡፡

፪. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቦታና እንደ ዚሁም የቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በሚገኝበት ሁሉ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲቋቋም ይህ ቃለ ዐዋዲ ያስገድዳል፡፡

፫. የታወቁ የአንድነት ገዳማት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው የገዳማት አስተዳደር ደንብና መመሪያ የሚተዳደሩ ስለሆነ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲያቋቁሙ አይገደዱም፡፡ ሆኖም እንደ አካባቢውና እንደ አስፈ ላጊነቱ እየታየ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

፬. ከአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጀምሮ ከወረዳ እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ድረስ በየደረጃው የተቋቋመውና የሚቋቋመው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቍጥር ፫፻፺፰ እና ፫፻፺፱ መሠረት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጣት ሕጋዊ መብትና ግዴታ በቤተ ክርስቲያኒቱ ይሠራበታል፡፡

፭. የየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ዋና ከተማ እንደ አንድ ወረዳ ስለሚ ቈጠር የራሱ የሆነ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ያቋቁማል፡፡

## አንቀጽ ፬

## የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አደረጃጀት

፩. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ፣

፪. የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፣

፫. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፣

፬. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፡፡

## አንቀጽ ፭

## የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዐላማ

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚከተሉት ዐላማዎች ይኖሩታል፡፡

፩. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅና አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ማድረግ፣

፪. የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች በሐዋርያዊ ተግባር ማደራጀት፣ ችሎታቸ ውንና ኑሮአቸውን ማሻሻል፣

፫. ምእመናን በመንፈሳዊ ዕውቀት ጐልምሰው በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው በክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖሩ ማድረግ፣

፬. የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ማጠናከርና በገቢ ራሷን ማስቻል፡፡

## አንቀጽ ፮
## የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተግባር

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዐላማውን ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፩. የእግዚአብሔርን ወንጌለ መንግሥት መስበክና ትምህርቱንም ማስፋፋት፣

፪. የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ የአብነት እና ዘመናዊ ትምህርት ቤትን ማቋቋምና ማደራጀት፣

፫. መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለምእመናን ሁሉ ማዳረስ፣

፬. የሰንበት ትምህርት ቤትን ማቋቋምና ማጠናከር፣

፭. ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያስፈልጉትን ሁሉ ማሟላት፣

፮. የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደርና አገልግሎት በመንፈሳዊ ሕግና ሥነ ሥርዓት መምራት፣

፯. ቤተ ክርስቲያንን በሀብትና በንብረት ራሷን ማስቻል፣

፰. የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ሕግና ደንብ መሠረት እየተመዘገበ እንዲያዝ፣ እንዲጠበቅ፣ እንዲለማና እንዲ ያድግ ማድረግ፣

፱. ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት ከበላይ የሚሰጡትን ሕግጋት፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ትእዛዞችና ውሳኔዎችን መፈጸምና ማስፈጸም፣

፲. በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚገኙ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት እርስ በርሳ ቸው ተባብረውና ተረዳድተው እንዲሠሩ ማድረግ፣

፲፩. ልዩ ልዩ የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን ማቋቋምና አገልግሎታቸውን ማሟላት፣

፲፪. የሕንጻ ሥራ፣ እድሳት፣ ጥገናና የመሳሰሉት ሥራዎች ሁሉ ወቅቱን ጠብቀው የሚፈጸሙበትን ዕቅድና መርሐ ግብር ማዘጋጀት፤ በተግባር መዋላቸውንም መቈጣጠር፣

፲፫. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮችን ብዛት፣ የሰበካውን ንብረት፣ ገንዘብ፣ ገቢና ወጪ የመሳሰሉትንም አኃዛዊ መረጃዎች /ስታቲስቲክስ/ በወቅቱ እየመዘገቡ ለየሚመለከ ታቸው አካላት በሪፖርት እንዲገለጽ ማድረግ፣

፲፬. በዚህ ቃለ ዐዋዲ መሠረት ማንኛውንም ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ጉዳይ መፈጸምና ማስፈጸም፣

፲፭. በዚህ አንቀጽ ከተራ ቍጥር ፩ እስከ ፲፬ የተዘረዘሩትን ተግባራት በቅድሚያ እያጠና ተገቢውን ማድረግና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር እየተነጋገረ መፈጸምና ማስፈጸም፡፡

## ምዕራፍ ፫

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አወቃቀር

## አንቀጽ ፯

### ፩. አመሠራረት፣

ሀ) በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ካህናት፣ ምእመናንና የሰን በት ትምህርት ቤት ወጣቶች በቃለ ዐዋዲው መሠረት በአንድነት በመደራጀት የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ይመሠርታሉ፡፡

ለ) በዚህ አኳኋን የተመሠረተው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንደአስ ፈላጊነቱ ሁለት ጊዜ በዓመት የሚሰበሰብ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ካህናትና ምእመናን በአንድነት የሚገኙበት መንፈሳዊ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡

ሐ) የአጥቢያው መንፈሳዊ ጉባኤ የቃለ ዐዋዲውን ዐላማና ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንዲችል በወር ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ የተጣለበትን ሥራና ኀላፊነት የሚያከናውን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣል፡፡

መ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያልታወቀና ያል ታቀፈ፣ በሀገረ ስብከቱ ወይም በጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ ያልተፈቀደ ምንም ዓይነት የካህናት፣ የምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ማኅበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም መቋቋም አይችልም፡፡

፪. አወቃቀር

ሀ) የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሰብሳቢ የሆነበት አንድ መንፈሳዊ ጉባኤ፣

ለ) የየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሰብሳቢ የሆነበት አንድ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ)

ሐ) የአጥቢያው መንፈሳዊ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት፣

መ) የአጥቢያው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ናቸው፡፡

## አንቀጽ ፰
## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
## የሥራ አፈጻጸም

፩. በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ጥሪ ተደርጎ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፪. በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሰብሳቢነት የመንፈሳዊ ጉባኤው አባላት የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት በመከተል ሥራውን ሁሉ ይፈጽማሉ፤ ያስፈጽማሉ፤ ድምፅ የሚሰጥባቸው ጉዳዮችንም በድምፅ ብልጫ ይወስናሉ፡፡

፫. ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አባላት፣

ሀ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ፣

ለ) በአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተመዝግበው መታወቂያ ካርድ የወሰዱና፤ ቢያንስ ለስድስት ወራት በአጥቢያው ነዋሪ የሆኑ፡፡

፯. ሀ/ በአስተዳደሩ ጉባኤ (በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው) አቅራቢነት መንፈሳዊ ጉባኤው በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ አራት በአንቀጽ ፲፪ የተመለከቱት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ ክፍል ኀላፊዎችንና አባላትን ይመርጣል፡፡

ለ/ ቋሚ አገልጋዮችን በተመለከተ ሀገረ ስብከቱ የአጥቢያውን የገቢና የሥራ ሁኔታ እየተመለከተ አሠረ ክህነት ካላቸው መካከል በሃይማኖታቸው፣ በሥነ ምግባራቸው፣ በዕውቀታቸውና በሥራ ልምዳቸው እያወዳደረ በጉባኤ ወስኖ ይመድባል፡፡

ሐ/ የገቢ ዐቅማቸው አነስተኛ በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ከካህናትና ከምእመናን በሚመረጡ አባላት ሥራው እንዲሠራ ያደርጋል፡፡

፰. በአስተዳደር ጉባኤ ተጠንቶ የሚቀርበውን ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መርምሮ ሲስማማበት እንዲፈቀድ ደረጃውን ጠብቆ ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

፱. የአጥቢያውን ቤተ ክርስቲያን ገንዘብና ንብረት ጠቅላላ ገቢና ወጪ በበጀት ዓመቱ መጨረሻና በሌላም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የሒሳብ ባለሙያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በሀገረ ስብከቱ ሲፈቀድ በጠቅላይ ቤተ ክህነት እንዲሁም ሀገረ ስብከቱ አወዳድሮ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

፲. ከአጥቢያ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ) የሚቀርበውን የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ፣ የንብረት፣ የሥራ ክንውን መግለጫና የኦዲት ሪፖርት ይሰማል፤ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ሲገጥምም በድምፅ ብልጫ ይወስናል፡፡

፲፩. የዚህ ጉባኤ ተጠሪነት ደረጃውን ጠብቆ ለወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተ ዳደር ጉባኤ እና ለወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፱

## የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባርና የሥራ አፈጻጸም

፩. አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩዎችን በዕለቱ አስጠቁሞ ምርጫውን ያስፈ ጽማል፡፡ ሆኖም በዕለቱ ማስፈጸም ካልተቻለ በቀጣዩ እሑድ ምርጫ ውን ያከናውናል፡፡

፪. ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን አጣርቶና የምርጫውን አፈጻጸም አዘጋጅቶ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ለምርጫ ያቀርባል፡፡

፫. መራጮቹም በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፰ ተራ ቍጥር ፫ የተገለጸውን መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

፬. የምርጫው ድምፅ አሰጣጥ ከመጀመሩ አስቀድሞ አስመራጭ ኮሚቴው መራጮቹ የሚመርጧቸውን አባላት በትክክል እንዲያውቁና ብቁነታቸ ውንም አመዛዝነውና ተረድተው ለመምረጥ እንዲችሉ ለመራጮች ብቻ በተዘጋጀ ቦታ ትምህርትና ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

፭. የምርጫው የድምፅ አሰጣጥም እንደ አካባቢውና እንደ አመችነቱ፡- በጽሑፍ ወይም በካርድ ወይም እጅ በማውጣትና በማስቈጠር ሊሆን ይችላል፡፡

፮. የአስመራጭ ኮሚቴው ካቀረባቸው ዕጩዎች መካከል በአጥቢያው ካህናትና ምእመናን  ያልተደገፉ ቢኖሩ በጉባኤው ጠቋሚነት ሌሎች ዕጩዎች ቀርበው እንዲመረጡ የማድረግ ኀላፊነት አለበት፡፡

፲. የድምፅ አሰጣጡ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ እና አስመራጭ ኮሚቴው ወዲያውኑ ከመዘገበና ከተፈራረመበት በኋላ የጉባኤው ሰብሳቢ ለሆነው ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ያቀርባል።

፲፩. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪም በአስመራጭ ኮሚቴው የቀረበለትን የምርጫ ቃለ ጉባኤ ጸድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ለወረዳው ቤተ ክህነት ያቀርባል።

## አንቀጽ ፲

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የአባላት ዓይነትና ብዛት፣ የአባላት አመራረጥ፣ የተመ ራጮች አባላት መመዘኛ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል።

### ፩. የአባላት ዓይነትና ብዛት

የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈ ጻሚ ኮሚቴ) ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ጋር ከአምስት ያላነሱ ከዘጠኝ ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል።

ሀ) የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ..................................የጉባኤው ሰብሳቢ፣

ለ) በዚህ ተራ ቍጥር በፊደል (ሐ) እና (መ) ከተጠቀሱት ካህናትና ምእ መናን አባላት መካከል የአስተዳደር ችሎታ ያለው ሆኖ በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸናና ግብረገብ የሆነ በዚህ ጉባኤ የሚመረጥ ካህን

ወይም ምእመን ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፷ ዓመት ያልበለ ..................................... የጉባኤው ም/ሰብሳቢ

ሐ) በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን በግንባር ከሚያገለግሉት መደበኛ ካህናት መካከል የሚመረጡ ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ ካህናት .......................... የጉባኤው አባላት

መ) ከአንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣት ጋር ከሰበካው ምእመናን መካከል የሚመረጡ ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ ምእመናን ....................... የጉባኤው አባላት

ሠ) የቤተ ክርስቲያኑ መደበኛ ጸሐፊ የአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ጸሐፊ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በውሳኔ ወቅት ድምፅ አይኖረውም፡፡ መደበኛ ጸሐፊ በሌለባቸው የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከመደበኛ አገል ጋዮች መካከል ለሰበካ ጉባኤ አባልነት የተመረጠው ካህን የሰበ ካው ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ............................. የጉባኤው ጸሐፊ ይሆናል፡፡

## ፪. የአባላት አመራረጥ

### ሀ) የካህናት ተመራጮች መመዘኛ

ከካህናት ወገን የሚመረጡት አባላት፡-

(፩) ለአስተዳደር ሥራ ተገቢና ብቁ የሆኑ መደበኛ አገልጋይ ካህናት፣

(፪) ኢክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የማይታይባቸው፣ ኅጠኝነትና መሰል ተግባራት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ፣

(፫) ከትዕቢት፣ ከተንኮል፣ ከአድማ፣ ከስካር፣ ከፍቅረ ንዋይ የራቁ፣ ግብረ ገብነታቸው እና ትሕትናቸው የተመሰከረላቸው፣

(፬) ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጸሎት የሚተጉ፤ ለስብከተ ወንጌል የሚ ፋጠኑ፤

(፭) የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው፣ በሌላም ወንጀል ተከሰው በጉባኤ ያልተወሰነባቸው ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደባቸው ወይም በማና ቸውም ሁኔታ መብታቸው በሕግ ያልተገደበባቸው ዕድሜያቸው ከ፳፩ ዓመት በላይ የሆናቸው ይመረጣሉ፡፡

ለ) <u>የምእመናን ተመራጮች መመዘኛ</u>

<u>ከምእመናን ወገን የጾታ ልዩነት ሳይደረግ፡-</u>

፩) በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በሰበካ ጉባኤ በአባልነት ተመዘግበው ግዴታቸውን የተወጡ፤

፪) የአጥቢያው ነዋሪ ስለመሆናቸው ሕጋዊ የሆነ የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው፤

፫) ኢክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የማይታይባቸው፣ ኅጠኝነትና መሰል ተግ ባራት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ፤

(፬) ከትዕቢት፣ ከተንኮል፣ ከአድማ፣ ከስካር፣ ከፍቅረ ንዋይ የራቁ፣ ግብረ ገብነታቸውና ትሕትናቸው የተመሰከረላቸው የገንዘብ ጉድለት ያልተገ ኘባቸው በሌላም ወንጀል ተከሰው በጉባኤ ያልተወሰነባቸው ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደባቸው ወይም በማናቸውም ሁኔታ መብታ ቸው በሕግ ያልተገ ደበባቸው፤

(፭) በአጥቢያው ነዋሪ የሆኑ ዕድሜያቸው ከ፳፩ እስከ ፰ ዓመት የሆኑ ምእመናንና ምእመናንት ይመረጣሉ፡፡

ሐ) <u>ከሰንበት ት/ቤት የሚመረጡት ቊጥራቸው ከምእመናን ወገን ሆኖ</u>

፩) በሰበካው ሰንበት ት/ቤት በአባልነት የተመዘገቡ፤

፪) ዕድሜያቸው ከ፲፰ እስከ ፴፭ ዓመት የሆናቸው፤

(፫) ብቁ ችሎታ ያላቸውና በአስተዋይነታቸው የተመሰገኑ፤

(፬) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የጸኑ፤

(፭) በቤተ ክርስቲያኒቱ ዶግማ፣ ቀኖናና ሥርዓት የማይጠረጠሩ ወጣቶች የጾታ ልዩነት ሳይደረግ ይመረጣሉ።

## <u>አንቀጽ ፲፩</u>
## <u>ምርጫን ማሻሻል፣መሻርና ማጽደቅ ስለ ተመራጮች የአገልግሎት ዘመን</u>

<u>፩. ምርጫውን ማሻሻል፣ መሻርና ማጽደቅ፡-</u>

ሀ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው የሰበካ ጉባኤ ምርጫ ሁሉ በወረዳው ቤተ ክህነት አቅራቢነት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይጸድቃል። የምርጫው አፈጻጸም ትክክል ሆኖ ባያገኘው ሊቀ ጳጳሱ ምርጫውን በጉባኤ አይቶ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል።

ለ) የሰበካ ጉባኤ አባላት ተመርጠው ሥራ ከጀመሩ በኋላ የሃይማኖት ሕጸጽ፣ የገንዘብ ብክነት ወይም ሌላ ችግር ቢፈጠር ሀገረ ስብከቱ በአስተዳደር ጉባኤ ሁኔታውን አጥንቶ የመሻር ሥልጣን አለው።

፪. ለአባልነት የተመረጠው ካህን ወይም ምእመን በተመረጠበት አገልግሎት ላይ የሚቆየው ለሦስት ዓመታት ይሆናል። ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም።

፫. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ ዘመኑ ከማለቁና ቀጣዩ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት የሥራ ክንውን ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፬. በሥራ ላይ ያሉት የሰበካ ጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት የአዳዲስ አባላት ምርጫ ይፈጸማል፤ ነገር ግን አዳዲስ የተመረጡት አባላት ሥራቸውን የሚጀምሩት በሥራ ላይ ያሉት አባላት የሥራ ዘመን ሲያበቃ ነው፡፡

፭. ለተመረጡት አባላት ስለ ቃለ ዐዋዲና የቤተ ክርስቲያን ሕግጋት በሚመለከታቸው አካላት ሥልጠና ይሰጣል፡፡

፮. <u>ስለ ተተኪ አባላት፤</u>

አንድ አባል የሥራ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት በሞት ወይም በዝውውር ምክንያት ወይም በአንቀጽ ፲ ተራ ቍጥር ፪ ከ (ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩትን የማያሟላ መሆኑ ሲታወቅ ወይም ለወረዳው አስተዳደር ጉባኤ በመመረጡ ወይም በሌላ ምክንያት ቦታው ክፍት የሆነ እንደሆነ ባለፈው ምርጫ ከተመረጡት አባላት ቀጥሎ ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው አባል ሆኖ ቦታውን ይተካል፡፡ በዚህ ዓይነት የሚተካ አባል ከታጣ እንደገና በካህናቱና ምእመናኑ መንፈሳዊ ጉባኤ ድምፅ ብልጫ ተመርጦ የተባለውን ክፍት ቦታ በአባልነት እንዲተካ ይደረጋል፡፡ ተተኪውም አባል የሚያገለግለው የዘመኑ ምርጫ እስኪፈጸም ድረስ ይሆናል፡፡

## <u>አንቀጽ ፲፪</u>

## <u>የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ</u>

## <u>(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር</u>

በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ ፪ በአንቀጽ ፫ እና ፯ የተዘረዘሩትን ዐላማና ተግባር እየፈጸመ በተጨማሪ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. የቤተ ክርስቲያን ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ሲኖዶሳዊ መዋቅር የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፪. ስለ ንዋየ ቅድሳት፣ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ስለ ልዩ ልዩ ታሪካዊ ቅርሶች አጠባበቅ፣ አያያዝ እያጠና ይመክራል፤ ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፡፡

፫. በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ የሚነሱትን የሃይማኖትና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚመለከት ልዩ የካህናት ጉባኤ ያቋቁማል፡፡

፬. በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን በፈጸሙ ባልና ሚስት መካከል የሚቀርቡትን ክሶች እና እንዲሁም ሥልጣነ ክህነትን እና ልዩ ልዩ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ በተለይ ለዚሁ ተብሎ በተሠየመው የካህናት ጉባኤ እንዲወሰን ያደርጋል፡፡ ጉዳዩ ከዚህ ጉባኤ ሥልጣን በላይ ሆኖ ከተገኘ ደረጃውን ጠብቆ ወደ በላይ አካል ያቀርባል፡፡

፭. የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን ከክፉ ነገር ሁሉ የመጠበቅ፣ የሚሰጣቸው ትምህርትም ሆነ የሚዘምሩት መዝሙር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዶግማ፣ ቀኖናና ትውፊት መሠረት መሆኑን የማረጋገጥ፣ ሥራቸውና ጠባያቸው ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውጭ እንዳይሆን የመከታተልና የመቈጣጠር ኀላፊነት አለበት፡፡ በሰንበት ት/ቤት ያልተመዘገቡ ወጣቶችን እንዲመዘገቡ፣ በሃይማኖትና በሥነ ምግባር እንዲጸኑ ያደርጋል፡፡

፮. ፩ ሀ/ ስጦታዎችን ይቀበላል፤ ለሚመለከተው ክፍልም ያሳውቃል፡፡

ለ/ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ስም ይከሳል፤ይከሰሳል፡፡

፪. ቃለ ዐዋዲውን መሠረት በማድረግ ዕቅዱንና ጥናቱን ለሀገረ ስብከቱ እያቀረበ ሲፈቀድለት በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ስም፡-

ሀ) ውል መዋዋል

ለ) መክሰስ

ሐ) ለሥራው በሚያስፈልገው መጠን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በውል ማከራየትና መከራየት፤

መ) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም አዋጭ ለልማት ሥራ ብቻ የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት ሲስማማበትና ሊቀ ጳጳሱ ፈቃዳቸውን በጽሑፍ ሲያረጋግጡ ገንዘብ ከባንክ መበደር ይችላል፡፡

፫. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቋሚ ንብረቶችና ግምታቸው ከፍተኛ በሆኑ በማንኛውም ጉዳዮች ላይ ውል መዋዋል በአስፈለገ ጊዜ በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት በሚመራው አስተዳደር ጉባኤ ሲወሰን፣ ይኸውም በጽሑፍ ሲፈቀድና ሲረጋገጥ መዋዋል ይችላል፡፡

፰. ስለ አጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት አያያዝ ዝርዝር ጉዳይ ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣ ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፱. በቃለ ዐዋዲ በአንቀጽ ፶፮ ተራ ቍጥር ፩ በተጠቀሰው መሠረት የሰበካው ካህናትና ምእመናን የሚከፍሉትን የገንዘብ መጠን ያሳውቃል፤ ገቢ መሆኑንም ይቈጣጠራል፡፡

፲. ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ገቢ ውስጥ በቃለ ዐዋዲ በአንቀጽ

፶፯ ተራ ቍጥር ፩ መሠረት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደር፣ ለትምህርት፣ ለስብከተ ወንጌል፣ ለል ማት፣ ለበጎ አድራጎት እና በየሰበካው ለሚከናወኑት የኅብረት ሥራ ዕቅዶችና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከማንኛውም ገቢ ላይ ፳% (ሃያ ከመቶ) እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

፲፩. በማእከል ደረጃ ተፈቅዶ አዲስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን፣ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክና የመሳሰሉት በሚሠሩበት ጊዜም ቢሆን ከግለሰብ፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ከበጎ አድራጊዎች በርዳታ ከሚገኘው በስ ተቀር ከልማትም ሆነ ከማናቸውም ገቢ ላይ ፳% (ሃያ ከመቶ) እንዲ ከፈል ያደርጋል፡፡

፲፪. የአብነት ትምህርት ቤትን በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ለመምህራኑና ለደቀ መዛሙርቱ በጀት ይመድባል፡፡

፲፫. ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያኑን ገቢ ገንዘብ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ በሚከፈት ባንክ ሒሳብ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም ያስቀምጣል፡፡

፲፬. ሀ/ በቃለ ዐዋዲ በአንቀጽ ፶፯ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቤተ ክርስቲያኑን ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መርምሮ እንዲ ፈቀድ ደረጃውን ጠብቆ ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

ለ/ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤትም የቀረበውን በጀት መር ምሮ ሲስማማበትና በጀቱን አጽድቆ ሲልክለት በተግባር እንዲ ውል ያደርጋል፡፡

፲፫. የቤተ ክርስቲያኑን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎችን ያቋቋማል፡፡

፲፬. ከቤተ ክርስቲያኑ ጽ/ቤት በተወሰነው ጊዜ የሚቀርበውን የሥራ መግለጫና የሰበካው ተቈጣጣሪ የሚያቀርበውን የሒሳብ ምርመራ ውጤት ተመልክቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፲፭. በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ ሕንጻ ለመሥራት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለታቀደው ሥራ ከሀገረ ስብከቱ ፈቃድ በማግኘትና መመሪያ በመቀበል የሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ የዚህን ኮሚቴ አባላትም በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ጉባኤ ያስመርጣል፡፡

፲፮. ለሕንጻ ሥራ በሀገረ ስብከቱ ፈቃድ የተለየ የባንክ ሒሳብ ቍጥር በዚህ አንቀጽ ተራ ቍጥር ፲፫ በተጠቀሰው መሠረት በቤተ ክርስቲያኑ ስም እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

፲፱. ከባንክ ገንዘብ ወጪ በሚደረግበት ጊዜ፡-

ሀ) መደበኛው የሰበካ ጉባኤ ወጪ ሒሳብ በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪና በሰበካው ም/ሰብሳቢ በሁለቱ ጣምራ ፊርማ፤ ከመደበኛ ወጪ ሌላ ገንዘብ ማውጣት ሲያስፈልግ በሰበካ ጉባኤ ተወስኖ በሥራ ላይ እንዲውል ይሆናል፡፡

ለ) ለሕንጻ ሥራው ወጪ ሲያስፈልግ በኮሚቴው ተወስኖ በአስተዳዳሪውና በሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ በም/ሰብሳቢው ጣምራ ፊርማ በወጪ ማዘዣ ቼክ እየተፈረመ ገንዘቡ እንዲወጣና በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፳. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቋቋሙት የሥራ ክፍሎች የሚወስኑትን ልዩ ልዩ ጉዳዮች እየመረመረ ያሻሽላል፣ ይሽራል፣ ያጸድቃል፡፡

፳፩. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሚያደርሱት ጥፋት አስተ ዳደር ነክ የሆነውን አይቶና መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ወንጀል ነክ ጉዳዮች በሕግ እንዲታዩ ያደርጋሉ፡፡

፳፪. ከመንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት መካከል ለወረዳው ሰበካ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ አንድ ካህን፣ አንድ ምእመንና አንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣት መርጦ ይልካል፡፡

፳፫. በዚህ ቃለ ዐዋዲ አንቀጽ ፺ ተራ ቍጥር ፩ (ለ) መሠረት በየስድስት ወር በሚደረገው ስብሰባና የሰበካ መንፈሳዊ አስተደደር ጉባኤ የሥራ ጊዜውን ከመፈጸሙ ከአንድ ወር በፊት ስለአከናወናቸው ሥራዎችና የገንዘብ ወጪዎች በማስመልከት በሀገረ ስብከቱ ሲፈቀድ ሪፖርት ለካህናትና ምእመናን ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡፡

፳፬. በቤተ ክርስቲያኒቱ በዐበይት በዓላትና በበዓለ ንግሥ ጊዜ በዓሉን ለማሳመር በሚል ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጪ የሚፈጸሙትን ተግ ባራት እንዳይፈጸሙ ይቈጣጠራል፤ ይከላከላል፡፡

፳፭. በቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረትና አካባቢው የድምፅ ማጉያዎችን /በካይ ድምፆችን/ በመጠቀም የካሴትና የልዩ ልዩ ሸያጮችንና ፈቃድ ከተሰጣቸው ውጭ የሚካሄድን ልመና እንዳይካሄድ ይቈጣጠራል፡፡

፳፮. በማሕሌት፣ በጸሎተ ቅዳሴ፣ በትምህርተ ወንጌልና መንፈሳዊ አገል

ግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን በሚገኙ አዳራሾችና ልዩ ልዩ መጠለያዎች ሌሎች መርሐ ግብሮች እንዳይካሄዱ ይቈጣጠራል፤ ይከላከላል::

፳፲. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተጠሪነቱ ለወረዳው ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ይሆናል::

## አንቀጽ ፲፫
## የአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፫ እና ፯ የተመለከተውን ዐላማና ተግባር ለመፈጸም እና ለማስፈጸም አስተዳዳሪው የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

፩. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን በዚህ ቃለ ዐዋዲና ይህን ቃለ ዐዋዲ ተከትሎ በሚወጣው የውስጥ ደንብ መሠረት ስለ ሰበካው ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ ጉባኤና ስለ አስተዳደሩ ጉባኤ የሥራ አፈጻጸም በአጥቢያ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ላለው መንፈሳዊ አገልግሎትና አስተዳደር ኀላፊና ተጠሪ ነው::

፪. ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መንፈሳዊ አገልግሎትና አስተዳደር ከቅዱስ ሲኖዶስ በወጣውና በሚወጣው ደንብ መሠረት የአጥቢያውን ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መንፈሳዊ አገልግሎት ይመራል::

፫. የአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ከመከናወኑ

በፊት ለአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ካህናትና ምእመናን የግ ንዛቤ ትምህርት ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያደርጋል።

፬. በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ በቃለ ዐዋዲው ምዕራፍ ፬ አንቀጽ ፲፫ ተራ ቍጥር ፩ የተዘረዘሩት ንኡሳን ክፍሎች እንዲደራጁና በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ ተገቢውን ክትትልና ቍጥጥር ያደርጋል። የልዩ ልዩ ክፍል ሥራ ኀላፊዎችን ያስተባብራል፤ ይቈጣጠራል።

፭. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ካህናትና ምእመናን የአባልነት መታወቂያ ያላቸው መሆናቸውንና በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ ያሉት ምእመናን ሁሉ መመዝገባቸውን፤ የጥምቀት፣ የጋብቻ እና የሙታን መዛግብት እየተሠራባቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

፮. የአጥቢያውን ሰበካ ምእመናንና የምእመናኑንም ልጆች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር እንዳይወጡ ያስተምራል፤ ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፤ በጠቅላላው ካህናትን ይልቁንም የንስሓ አባቶችን በማስተማሩና በጥበቃው ተግባር እንዲጠናከሩ መመሪያ ይሰ ጣል፤ ይቈጣጠራል።

፯. የቤተ ክርስቲያኑ ገቢ በትክክል እንዲሰበሰብ ገንዘቡና ማንኛውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረት እንዲጠበቅና በአስተ ዳደሩ ጉባኤ እየታየ በሚወሰነው መሠረት በተገቢው ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል።

፰. ከበላይ በተፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መሠረት ማንኛውንም ወጪ በማዘዝ እንዲሠራበት ያደርጋል።

፱. በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፲፪ ከተራ ቍጥር ፯ እስከ ፱ የተደነገገውን ጠብቆ የውሉ ረቂቅ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው ሲስማማበትና በሀገረ

ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ተወስኖ በጽሑፍ ሲፈቀድ ብቻ ከም/ሰብ ሳቢ ጋር ሆኖ በቤተ ክርስቲያኑ ስም ውል ይዋዋላል፤ ይፈርማል፡፡

፲. የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ ያስተላልፋል፤ በጉባኤ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት እንዲሠራበት እያደረገ አፈጻጸሙን ይቈጣጠራል፡፡

፲፩. የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላትን እና የልዩ ልዩ ክፍል ኀላፊዎችን ምርጫ እንዲጸድቅለት ለወረዳው ቤተ ክህነት ያቀርባል፡፡

፲፪. በአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተደደር ጉባኤ ስም አስተዳዳሪው ስለ ሰበካው ካህናትና ምእመናን ሁኔታ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ አገል ጋዮች፣ ስለ ገንዘብና ንብረት እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሥራ ክንውን መግለጫ ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ያቀርባል፤ የጉባኤውንም ውሳኔ ለወረዳው ቤተ ክህነት ያስተላልፋል፡፡

፲፫. አስተዳዳሪው ቅጥርን፣ ደመወዝ ጭማሪን፣ እድገትን፣ ዝውውርንና ከሥራ ማሰናበትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ የሰበካው ሥራ አስ ፈጻሚ ኮሚቴ ሳይነጋገርበትና ሳይወስን በተጨማሪም የበላይ አካል ሳያውቀውና ሳይፈቅድ ብቻውን መፈጸም አይችልም፡፡

፲፬. በየዘርፉ ካሉ የሥራ ኀላፊዎች በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት የአገል ጋዮችን የሥራ ሂደት ይቈጣጠራል፤ ይመክራል፤ አጥፊዎችንም ይገ ሥጻል፤ የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

፲፭. በቃለ ዐዋዲው መሠረት በሚሰጠው መመሪያ የሚወሰንለትን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

## አንቀጽ ፲፬
## የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ም/ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

፩. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በሌለ ጊዜ ም/ሰብሳቢው የአስተዳዳሪውን ተግባር ይፈጽማል፡፡

፪. የተፈቀደውን መደበኛ የሰበካ ጉባኤ ወጪ ሒሳብ ከአስተዳዳሪው ጋር በጣ ምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡

፫. ም/ሰብሳቢው ሥልጣነ ክህነት የሌለው ከሆነ ምሥጢራተ ቤተ ክርስ ቲያንን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማየት አይችልም፡፡

፬. ም/ሰብሳቢው ተጠሪነቱ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ነው፡፡

## አንቀጽ ፲፫
## ስለ ገዳማት አስተዳዳርና ሥርዓተ ምንኵስና

፩. የገዳማት አስተዳደር፡-

ሀ) የአንድነት ገዳማት የሚተዳደሩበት እንደየገዳማቱ ሥርዓት በየአህጉረ ስብከቱ እየተጠና የሚፈቀድ ደንብና መመሪያ ይኖራቸዋል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ በሀገረ ስብከቱ አቅራቢነት በቅዱስ ሲኖዶስ ሊወጣላቸው ይችላል፡፡

ለ) ሥርዓተ ገዳም በሚፈቅደው መሠረት በየገዳማቱ ውስጥ ጽ/ቤቶችና ልዩ ልዩ የአመራር አካላት ይቋቋማሉ፡፡

ሐ) በገዳሙ አስተዳደር መሠረት የጾም የጸሎት ሥርዓት እንደተጠበቀ ሆኖ መነኮሳት የሚማሩበት ቦታና በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሠማ ሩበት የሥራ መስኮች ይኖሩታል፡፡

መ) መነኮሳይያትም በተወሰነላቸው የገዳም ክልል ጸንተው በሥርዓተ ምንኵስና መሠረት ራሳቸውንና ሌሎችንም እየረዱ እንዲኖሩና እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡

ሠ) ገዳማት የየራሳቸው የተከበረ የቦታ ክልል ይኖራቸዋል፡፡

ረ) በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፫ ተራ ቍጥር ፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት ገዳማት ዙሪያ የሚኖሩ ምእመናን በሰበካ ጉባኤ ቢደ ራጁም ባይደራጁም በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

ሰ) ማንኛውም የገዳማቱ ገቢ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የበላይ ተቈጣ ጣሪነት እና በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ኀላፊነት በሚታተሙ ካርኒዎች ብቻ ገንዘቡን በሞዴል ፴ እና ፰፬ ንብረቱን በሞዴል ፲፱ እንዲ ሰበሰብ ያደርጋል፡፡ ሀገረ ስብከቱ ወይም ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ፈቃድ ባልሰጠው ካርኒ ገንዘብም ሆነ ንብረት የሰበሰበ ገዳም በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሸ) ማንኛውም የገዳሙ ገቢ ገንዘብ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ በሚከፈት ባንክ ሒሳብ በገዳሙ ስም ይቀመጣል፡፡ የባንኩ ሒሳብ የሚንቀሳቀሰውም በገዳሙ አበምኔት ወይም እመምኔት እና ማኅበረ መነኮሳቱ /መነኮሳይያቱ/ በሚወክሉት አንድ ተወካይ ጣምራ ፊርማ ይሆናል፡፡

ቀ) ሰበካ ጉባኤ በተቋቋመባቸውም ሆነ ባልተቋቋመባቸው ገዳማት ምእ መናኑ ከከፈሉትና ከልዩ ልዩ ገቢያቸው ላይ ከመቶ ሃያ ፳% ለሀገረ ስብከት ይከፍላሉ፡፡

በ) በገዳማት የሚኖሩ መነኮሳትም ሆኑ መነኮሳይያት እንዲሁም በገዳማት ዙሪያ የሚኖሩ ምእመናን በገዳሙ አማካይነት በሰበካ ጉባኤ ቅጽ ይመዘገባሉ፡፡

ተ) ማዕርገ ምንኵስና የሚሰጠው በገዳሙ አስተዳደር ቍጥጥር ውስጥ በአመክሮ ለሦስት ዓመታት ለቆዩና በዚህ አንቀጽ ተራ ቍጥር ፫ መሠረት መመዘኛውን ላሟሉት ብቻ ይሆናል፡፡

ቸ) አሠረ ክህነት ላላቸው በሊቀ ጳጳስ ታውቆና ተፈቅዶ ካልሆነ በቀር ማዕርገ ምንኵስና ከገዳም ውጭ አይሰጥም፡፡

ኀ/ የገዳም አበ ምኔት /መምህር/ ወይም እመ ምኔት ከገዳሙ ውጪ መንቀሳቀስ ባስፈለጋቸው ጊዜ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ነ/ የገዳሙ ተጠሪነት ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## ፪. የገዳም አበምኔት /መምህር/ ወይም እመ ምኔት

ሀ) የገዳም አበ ምኔት ወይም እመ ምኔት በማኅበረ መነኮሳትና መነኮሳይያት የሚገለገለውን የአንድነት ገዳም ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያና ደንብ መሠረት ያስተዳድራል፡፡

ለ) ከገዳሙ ውስጥ በግብረ ገብነታቸው፣ በትምህርታቸውና በጸሎታቸው ትሩፋት ይሠራሉ ተብለው የሚታመንባቸው መነኮሳት ተመርጠው ሲቀርቡ በሊቀ ምርፋቅነት፣ በሊቀ አርድእትነትና በዕዷል መጋቢነት እየሠየመ እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡

ሐ) የገዳሙ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የሚስፋፋበትን፣ መነኮሳትና መነኮሳይያት በተግባረ እድ ሙያ የሚሠለጥኑበትንና ራሳቸውንም ሆነ ገዳሙን የሚረዱበትን ልማት ከገዳሙ አስተዳደር ጋር እየመከረና የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ እያስፈቀደ ያቋቁማል፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፫ የተገለጸውን መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸው የተረጋገጠላቸውና ለምንኵስና ብቁ ለመሆናቸው ከገዳሙ አስተዳደር የተወሰነላቸው ሰዎች ሲቀርቡ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ በዚሁ ገዳም ውስጥ ምንኵስናን እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

ሠ) የምንኵስና ማዕርግ ለተቀበሉ መነኮሳት ወይም መነኮሳይያት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

ረ) ያለበቂ ምክንያትና ያለገዳሙ ፈቃድ ከገዳሙ ክልል ውጭ የሚወጡ ትንና የሚገቡትን መነኮሳት በጥብቅ ይቈጣጠራል፤ ቀኖናዊ ቅጣትም ይሰጣል፡፡

## ፫. <u>የምንኵስና መመዘኛ</u>

ሀ) <u>ሥርዓተ ምንኵስናን የሚቀበሉ ምእመናንና ምእመናት</u>

(፩) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ሥነ ምግባር የጸኑ ለመሆ ናቸው የሚኖሩበት አጥቢያ ሰበካ ጉባኤ የመሰከረላቸው እና መሸኛ የሰጣቸው፤

(፪) የምንኵስናን ዐላማና ተግባር በትክክል የተረዱና ይህንኑም ለመፈ ጸም ቍርጥ ሐሳብ ያላቸው፡፡

(፫) ከምንኵስና በፊት በድንግልና ወይም በጋብቻ ለመኖራቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤

(፬) ልዩ ችግርና በቂ ምክንያት ከሌለ በቀር ዕድሜያቸው ከ፴ ዓመት በላይ የሆኑ፤

(፭) ጤናማ አእምሮ ያላቸው፣ ትዕግሥተኛና አርቆ አስተዋይ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው፤

(፮) በገዳም ውስጥ ሦስት ዓመት በአመክሮ የቆዩ ማዕርገ ምንኵስና ይቀበላሉ፡፡

(፯) የሦስት ዓመቱ አመክሮ ዕድሜያቸው ከ፷ ዓመት በላይ የሆኑትን ምእመናንና ምእመናት አይመለከትም፡፡

ለ) <u>በክህነት ሥራ ለማገልገል ማዕርገ ምንኵስናን ለሚቀበሉ የቤተ ክርስ ቲያን አገልጋዮች</u>

(፩) በዚህ ተራ ቍጥር በፊደል ተራ (ሀ) ከ(፩) እስከ (፯) የተዘረዘረውን ማሟላታቸው በማስረጃ የተረጋገጠላቸው፤

(፪) መጻሕፍተ መነኮሳትን የሚያውቁና ሥርዓተ ገዳምን የሚጠብቁ፤

(፫) የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸውና ቅዱሳት መጻሕፍትን የተማሩ፤

(፬) በአርአያነታቸውም ሆነ በትምህርታቸው የታወቁና ችሎታ ያላቸው ማዕርገ ምንኵስናና ክህነት ይሰጣቸዋል፡፡

## <u>፬. ከምንኵስና በኋላ</u>

(ሀ) ሥርዓተ ምንኵስና ሲቀበሉ በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት እስከ ዕድ

ሚያቸው መጨረሻ ድረስ በምንኵስናቸው መጽናት ይኖርባቸዋል::

(ለ) በመነኮሱበት ገዳም እንደየስጦታቸውና እንደየችሎታቸው መጠን አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል::

(ሐ) በቋሚነት ከሚኖሩበትና ከሚያገለግሉበት ገዳም ያለበቂ ምክንያትና ያለ ገዳሙ ፈቃድ ወደ ውጭ መውጣት የተከለከለ ነው::

(መ) በልዩ ልዩ ምክንያት ተፈቅዶላቸው ከገዳሙ ውጭ የሚኖሩ መነኮሳትና መነኮሳይያት ሥርዓተ ምንኵስናቸውን ጠብቀው፣ ከክፉ ነገር ርቀውና በመልካም ሥነ ምግባር ለአካባቢያቸው ሕዝበ ክርስቲያን አርአያ መሆን አለባቸው::

(ሠ) በምንኵስና ሥርዓት ለሚኖሩ መነኮሳትና መነኮሳይያት ከማይስማማ የሥራ ዓይነትና መገኘት ከማይገባቸው ቦታ መከልከል ግዴታቸው ነው:: የምንኵስና ምልክታቸው የሆነው ቆባቸው ከራሳቸው ላይ እንዳይለይ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

(ረ) በገጠርም ሆነ በከተማ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በልዩ ልዩ አገልግሎት የተመደቡ መነኮሳት በአኗኗራቸውና በአነጋገራቸው ለካህናትና ምእመናን የመልካም ሥነ ምግባር አብነት መሆን ይገባቸዋል::

(ሰ) ሳይበቁ በቅቻለሁ ብሎ ከመመጻደቅና ከውዳሴ ከንቱ ርቆ ለመነኮሳት የሚስማማውን ትሕትናና ትዕግሥትን መያዝ አለባቸው::

(ሸ) ከመነኮሳት መካከል ተመርጠውና ችሎታቸው ተመዝኖ ሥልጣን ባለው የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል ካልተፈቀደ በስተቀር ማስተማር አይገባቸውም፡፡

## ምዕራፍ ፬

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎች

## አንቀጽ ፲፯

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎች መቋቋም፤

### የሥራ ኃላፊዎች ምርጫና የአገልግሎት ዘመን

፩. የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በቃለ ዐዋዲ አንቀጽ ፰ እና ፺ የተገለጸውን ዐላማና ተግባር ለመፈጸም እንዲችል አንድ ጽ/ቤትና በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፩ ተራ ቍጥር ፬ የተደነገገውንና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ያቋቁማል፡፡

ሀ) የስብከተ ወንጌል ክፍል

ለ) የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል

ሐ) የካህናት አገልግሎት ክፍል

መ) የሰንበት ት/ቤት ክፍል

ሠ) የዕቅድና ልማት ክፍል

ረ) የምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) ክፍል

ሰ) የሕግ ክፍል

ሸ) የንዋየ ቅድሳት፣ የንብረትና የቅርሳ ቅርስ ክፍል

ቀ) የሒሳብ ክፍል

በ) የገንዘብ ቤት

ተ) የቊጥጥር ክፍል

ቸ) የሕንጻ ሥራ፣ እድሳትና ጥገና ክፍል

ኀ) አኃዛዊ መረጃ /ስታትስቲክስ/ ክፍል

ነ) የሰበካ ጉባኤ ማስተባበሪያ ክፍል

ኘ) የገዳማት ክፍል

፪. በዚህ አንቀጽ በተራ ቊጥር ፩ ከ (ሀ) እስከ (ኘ) የተዘረዘሩት የሥራ ክፍሎች የሥራ ዓይነትና ጠባይ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ተመሳሳይ የሆነውንና የማይቃረነውን ክፍል ሁለት ሦስቱን አንድነት በማደራረብ በአንዳንድ የሥራ ኀላፊዎች ማሠራት ይቻላል፡፡ እንደ ሁኔታውም እየታየ ኮሚቴ ለሚያስፈልጋቸው የሥራ ክፍሎች ኮሚቴ ማቋቋም ይቻላል፡፡

፫. በአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት አንድ ጸሐፊና በቋሚነት የሚመደቡ የየክፍል ኀላፊዎች ይኖራሉ፡፡

፬. በገጠር አብያተ ክርስቲያናት ለዋና ጸሐፊነትም ሆነ ለክፍል ኀላፊነት በግብረ ገብነታቸው፣ በችሎታቸውና በሥራ ልምዳቸው የተመሰከረላቸው ካህናት እና ምእመናን የወረዳው ቤተ ክህነት ኀላፊ በተገኘበትና የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሰብሳቢ በሆነበት በካህናት ጉባኤ ተመርጠው በሀገረ ስብከቱ ሲጸድቅ ይመደባሉ፡፡

፫. በከተማ በሚገኙ ገዳማትና አድባራት ግን የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት እንደ የሙያቸው እያወዳደረ ይመድባል፡፡

፬. በገንዘብ ያዥነትና በንብረት ኀላፊነት የሚመደቡት ሠራተኞች በቂ ሀብትና ንብረት ያለው ተያዥ ማቅረብ ግዴታቸው ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፩ ከ(ሀ) እስከ (ኘ) ለተዘረዘሩት ክፍሎች ኀላፊዎችን በቋሚነት መመደብ በማይቻልበት አካባቢና ጊዜ በግብረ ገብነታቸው፣ በችሎታቸውና በሥራ ልምዳቸው የተመሰከረላቸው ዕጩዎች በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ተመርጠው በወረ ዳው ሲጸድቅ ይመደባሉ፡፡

፮. በደመወዝ ከሚቀጠሩት ቋሚ አገልጋዮች ሌላ በበጎ ፈቃድ እንዲ ያገለግሉ የሚመረጡት የየክፍሉ ኀላፊዎች የአገልግሎት ዘመናቸው በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፲፩ ተራ ቍጥር ፪ ስለ ሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት የአገልግሎት ዘመን በተመለከተው መሠረት ይፈጸማል፡፡ ስለሆነም የየክፍሉ የሥራ ኀላፊ ዎች ምርጫ የሚደረገው የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት ከተመረጡ በኋላ ይሆናል፡፡

፱. በዚህ አንቀጽ ከፊደል ሀ እስከ ኘ የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት ክፍሎች እና በሥራቸው ያሉ ንኡሳን ክፍሎች ቋሚ በሆኑ በማንኛውም የንግድ ዘርፎች እንዲሰማሩ አይፈቀድም

፲. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የሥራ ክፍሎች ተጠሪነታቸው ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፲፪

## የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ሥልጣንና ተግባር

፩. የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ክህነት ያለው፤ ተጠሪነቱም ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሆኖ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት ውስጥ የሚከናወኑትን ጠቅላላ የጽሕፈት፣ የሒሳብና የንብረት አጠባበቅ ሥራዎችን እንደዚሁም የልዩ ልዩ ክፍሎችን የሥራ ሂደት በቅርቡ እየተከታተለ በመቈጣጠር ይሠራል ያሠራል።

፪. የአጥቢያው ሰበካ ካህናትና ምእመናን እየተመዘገቡ የአባልነት መታወቂያ ካርድ እንዲያገኙ ያደርጋል።

፫. ሕፃንም ሆነ ዐዋቂ ክርስትና ሲነሣ በመዝገብ ጥምቀት፤ እንዲሁም ጋብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን የፈጸሙ ተጋቢዎች በጋብቻ የክብር መዝገብ እንዲመዘገቡና የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

፬. ከእያንዳንዱ የሰበካው አባል ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በወቅቱ ገቢ መሆኑን ይከታተላል።

፭. መዝገብ ቤቱን ያደራጃል፣ ሥራውም በሥርዓት እንዲመራና ልዩ ልዩ ጽሑፎች፣ መዛግብት፣ ማኅደረ ጉዳዮች ሁሉ እንዲጠበቁና የጽ/ቤቱ ማኅተም በመዝገብ ቤት ተቀምጦ እንዲሠራበት ያደርጋል፤ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ በሌለበት ጊዜም ደርቦ ይሠራል።

፮. የአኃዛዊ መረጃ /የስታትስቲክስ/ ሠራተኛ በሌለበት በሕይወት ያሉትንና በሞት የተለዩትን የምእመናን ስም እየመዘገበ በክብር እንዲቀመጥ ያደርጋል።

፯. ስለ ቤተ ክርስቲያኑ የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ይዘት መግለጫ ለመጭው ዓመት ከሚፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) ጋር አዘጋጅቶ በአስተዳዳሪው አማካይነት ለአስተዳደር ጉባኤው ያቀርባል፡፡

፰. የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ጸሓፊ ሆኖ በስብሰባው ላይ በመገኘት ጉባኤው የተነጋገረባቸውን ዝርዝር ጉዳዮችና ውሳኔ የተሰጠበትን ቃለ ጉባኤ ያዘጋጃል፤ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፤ በጸሓፊነቱ ይፈርማል፡፡

፱. በቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ሰበካ ውስጥ ሃይማኖትን፣ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ስለሚፈጠሩ ሁኔታዎች አስተዳዳሪውንና የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤውን እያሳሰበ እንዲጠና ያደርጋል፡፡

፲. የቤተ ክርስቲያን ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች በየተግባራቸው እየተገኙ መሥራታቸውን በመቈጣጠር ሁኔታውን በየጊዜው ለአስተዳዳሪው በማቅረብ ተገቢውን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፲፩. የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን አባላትና አገልጋዮች ሁኔታ፣ የገንዘብና ንብረት መግለጫ፣ የጽ/ቤቱንና ከሰበካው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የሚቀርብለትን የሥራ ክንውን እንዲሁም አኃዛዊ መረጃዎችን በማጠቃለል በየሦስት ወሩ ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፲፪. ከአስተዳዳሪውና ከሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው የሚታዘዘውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፲፫. የሰው እጥረት ባለበት ቦታም፣ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሲወስን የሒሳብ ሥራና ኀላፊነትን ደርቦ ይሠራል፡፡

## አንቀጽ ፲፰
## የስብከተ ወንጌል ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. የስብከተ ወንጌል ክፍል የየዕለቱን መርሐ ግብር በማዘጋጀት በዕለተ ሰንበትና በዐበይት በዓላት ለሕዝበ ክርስቲያኑ በማእከል በተፈቀደ ላቸውና በታወቁ መምህራን ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

፪. አመች በሆነ ጊዜና ቦታ ምእመናንን በመሰብሰብ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ያስጠናል፡፡

፫. በቅዳሴ ጊዜ የዕለቱ ወንጌል ከተነበበ ወይም ከቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ ትምህርተ ወንጌል መሰጠቱን ይከታተላል፡፡

፬. ምእመናን በሚረዱት እና በሚያውቁት ቋንቋ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰጥ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች እንዲበዙና በሰበካ ጉባኤም እንዲመዘገቡ በማድረግ ሐዋርያዊ ተልእኮውን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

፭. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መመሪያ እየተዘጋጁ የሚወጡትን ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና ልዩ ልዩ እትሞችን እየተቀበለ ለምእመናን በወቅቱ የማድረስ ኀላፊነት አለበት፡፡

፮. በሊቃውንት ጉባኤ ታይተውና በማእከል ተፈቅደው ያልታተሙ መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ ካሴቶች፣ ሲዲዎች፣ ቪሲዲዎች፣ ዲቪዲዎች እና ልዩ ልዩ እትሞች በቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረትና በቅጽሩ ዙሪያ ለምእመናን እንዳይሰራጩ ያደርጋል፡፡

፯. ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጭ የሆኑ መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ ካሴቶች፣ ሲዲዎች፣ ቪሲዲዎች፣ ዲቪዲዎች እና ልዩ ልዩ አትሞች ለምእመናን እንዳይሠራጩ ይቈጣጠራል፡፡

፰. ያለ ፈቃድ እንሰብካለን እናስተምራለን የሚሉትን ሕገ ወጥ ግለሰቦችን የመቈጣጠር ኀላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ ፲፱
## የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አቅሙ በሚፈቅድለትና ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ መንፈሳዊ ት/ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

፪. በዚህ ትምህርት ቤት

ሀ) የንባብ፣ የጽሕፈት፣ የስሌትና የቋንቋ፤

ለ) የጸዋትወ ዜማ፣ የአቋቋምና የቅዳሴ፤

ሐ) የግእዝ (ቅኔ)

መ) የትርጓሜ መጻሕፍት (ትምህርተ ሃይማኖት)፣

ሠ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤

ረ) የኪነ ጥበባት፣ የተግባረ እድና ልዩ ልዩ የሙያ ትምህርቶች እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

፫. የአጥቢያ ሰበካውን ሕፃናት እያሰባሰበ ፊደል ከማስቈጠር ንባብ ከማስተማር ጋር መሠረተ ሃይማኖትን እንዲያውቁና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሩ ይሆናል፡፡

፬. ስለ ትምህርቱም ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣው ደንብና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት መርሐ ግብር በማዘጋጀት የትምህርቱን ይዘትና አመራር ይከታተላል።

፭. ሕፃናት በሥነ ምግባርና በሃይማኖት ተኰትኩተው እንዲያድጉ ያደርጋል።

፮. የትምህርት መስጫ ቦታዎች (ጉባኤ ቤቶች) አሠራርና አቀማመጥ ለትምህርት አሰጣጥና ለጤንነት ተስማሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፯. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መደበኛ መምህራን ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ በየሳምንቱ እሑድ፣ በወርና በዓመት በዓላት የሚደርሰውን ቃለ እግዚአብሔር ለአገልጋዮች ካህናት ቀደም ብለው እንዲያስጠኑ መርሐ ግብር ያዘጋጃል።

፰. ቤተ መጻሕፍት እንዲቋቋምና በሥርዓት እንዲያዝ ካህናቱም በተወሰነ ጊዜ በቤተ መጻሕፍት እየተገኙ በማንበብ ዕውቀታቸውን እንዲያሻሽሉና አእምሮአቸውም በትምህርት እንዲበለጽግ ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል።

፱. በማእከል በተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የተመረጡ መጻሕፍትን ለትምህርት እንዲያገለግሉ የማቅረብ ኀላፊነት አለበት።

፲. ተማሪዎች በየዕለቱና በየሰዓቱ በትምህርት ገበታ ላይ እየተገኙ የሚሰጣቸውን ትምህርት መከታተላቸውን ይቈጣጠራል፤ የትምህርት ችሎታቸውንም ይመዝናል።

፲፩. ተማሪዎች እንዳለፈው ጊዜ ደበሎ ለብሰው እና ለምነው ለመማር ወቅቱ ስለማይፈቅድ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን፣ ካልተቻለም

በአካባቢው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በኅብረት አንድ አዳሪ ማእ ከላዊ ትምህርት ቤት አቋቁመው ለመምህራን ደመወዝ፣ ለተማሪዎች ለምግባቸውና ለልብሳቸው የሚሆን የድጐማ በጀት እንዲመደብ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያስተባብራል፡፡

፲፪. በአብነት መምህርነት የተቀጠሩ መምህራን በወንበራቸው ተገኝተው ማስተማር ግዴታቸው መሆኑን ያሳውቃል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፲፫. መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ቤተ ክርስቲያንን የማገልገልና የማስገ ልገል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያሳውቃል፤ ያስፈጽማል፡፡

፲፬. በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት መምህራንና ተማሪ ዎች በሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት ተመዝግበው መታወቂያ እንዲኖራቸውና እያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱን ፈጽሞ በሚወጣበት ጊዜ በመምህሩ፣ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤውና በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አማ ካይነት የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፳

## የካህናት አገልግሎት ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ አገልግሎትና የክህነት ተግባርን የሚያጠቃልል ሆኖ ቄሰ ገበዙን፣ ሊቀ ዲያቆኑን፣ ሊቀ ጠበብቱንና አጋፋሪውን እያስተባበረ ይሠራል፡፡

፪. ሥርዓተ ማሕሌቱ፣ ሰዓታቱ እና ቅዳሴውም ሆነ ሌላው መንፈሳዊ አገልግሎት ትክክለኛውን ሥነ ሥርዓት ይዞ እንዲካሄድ ይከታተላል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፫. ካህናት የንስሓ ልጆቻቸውን ከክሕደት፣ ከኑፋቄ፣ ከክፉ ልማድና

ግብር ለመጠበቅ እንዲችሉ ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመተባበር በትም ህርተ ወንጌል እንዲሠለጥኑ ያደርጋል፤ ያስተምራል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፬. መምህራን፣ ቀሳውስት፣ መዘምራን፣ ዲያቆናትና ሌሎችም የቤተ ክርስ ቲያን አገልጋዮች በየተግባራቸው ላይ በሰዓቱ ተገኝተው የተመደቡበትን የክፍል ሥራቸውንና መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሳያጓድሉ በሥነ ሥርዓት መፈጸማቸውን እየተቈጣጠረ ሁኔታውን ለጽ/ቤቱና ለአስተ ዳዳሪው በማቅረብ ተገቢውን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፭. ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ለምእመናኑ ሁሉ በእኩልነትና በትክ ክል እንዲዳረስ ያደርጋል፡

፮. በቤተ ክርስቲያኑና በጠቅላላው በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ የመንፈሳዊ አገልግሎትን፣ የካህናት ተልእኮንና ተግባርን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ስለሚፈጠሩ ሁኔታዎች ጽ/ቤቱንና አስተዳዳሪውን እያሳሰበ አስፈላ ጊውን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፯. መስበክ፣ ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቍረብ፣ ናዝዞ ማሰናበት በአጠቃላይ አማንያን በሃይማኖት እንዲጸኑና በሥነ ምግባር እንዲጐለምሱ ማድ ረግ የካህናት ተልእኮና ግዴታ መሆኑ እንዲታወቅ ያደርጋል፤ ካህና ቱም ለዚህ ሥራ ብቁ እንዲሆኑ ያዘጋጃል፡፡

፰. የቃል ትምህርት ያጠና፣ ዳዊት የደገመ እና አምስቱ አዕማደ ምሥ ጢራትን ያወቀ ግብረ ገብነቱና መንፈሳዊ ዝንባሌው በካህናትና በምእ መናን የተመሰከረለትን ለዲቁና ማዕርግ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፱. መዝገበ ቅዳሴ የተማረ፣ ሰዓታት፣ ኪዳን፣ ሊጦንና መስተብቍዕ አጠና

ቅቆ ያወቀ፣ ቅኔና ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ያጠና፣ ቅዱ ሳት መጻሕፍትን ተርጉሞ ማስተማር የሚችል፣ ግብረ ገብነቱና መንፈ ሳዊነቱ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የተመሰከረለትን ዲያቆን የቅስና ማዕርግ እንዲቀበል ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ያቀርባል፡፡

፲. ዐበይት በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ ስለ በዓሉ አፈጻጸም መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ያቀርባል፤ መርሐ ግብሩንም ያስፈጽማል፡፡

፲፩. የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አግባብነት በሌላቸው ስፍራዎች እንዳ ይገኙ ይመክራል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፲፪. በሰንበቴና በዝክር ጽዋዕ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ቀኖና ውጭ በአንድ አንድ አካባቢ ጃንጥላ ይዘውና መብራት አብርተው በየመንገዱና በየመንደሩ በሚዘዋወሩት ካህናትና ምእመናን ላይ ጥብቅ ቍጥጥር ያደርጋል፣ ምእመናኑም አድራጎቱ ከሃይማኖት ሥር ዓት ውጭ መሆኑን ዐውቀው ከእንደዚህ ዓይነት ተግባር እንዲርቁ ትምህርትና ምክር ይሰጣል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

፲፫. ሥራቸው ያልታወቀና ክህነታቸው ያልተመረመረ ግለሰቦች ቄስ ወይም መነኰሴ በመምሰል ለምእመናን የንስሓ አባት እየሆኑ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ይቈጣጠራል፤ ለምእ መናንም ትምህርት ይሰጣል፡፡

፲፬. በስመ ዲያቆን፣ በስመ ቄስና በስመ መነኰሴ ማዕርገ ክህነት ያላቸው ለመሆኑ ያልታወቁ ካህናት በውክልና እንዳይቀድሱ እና የውስጥ አገልግሎት እንዳይፈጽሙ በጥብቅ ይቈጣጠራል፡፡

፲፫. ምእመናን በሰንበትም ሆነ በበዓላት ቀናት ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት የቤተ ክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት እንዲያጠኑ ለማድረግ ለንስሓ አባቶች መመሪያ ይሰጣል፡፡

፲፬. ሌሊት በሰዓታት ጠዋት በኪዳን ያልተገኙ ቀሳውስት እና ዲያቆናት መቀደስ የማይገባቸው መሆኑን ያሳውቃል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፲፭. የክርስትና አባቶች ወይም እናቶች በአንቀጸ ጥምቀት በተደነገገውና በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት ለክርስትና ልጆቻቸው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና እምነት የማስተማር ኀላፊነትና ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ ፳፩
## የሰንበት ት/ቤት ክፍል ሥራና ኀላፊነት

ስለ ሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እየተከታተለ የሰበካው የሰንበት ት/ቤት ክፍል ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፩. የሰንበት ት/ቤትን በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ያቋቁማል፣ ያደ ራጃል፣ በአጥቢያው ሰበካ ከአራት እስከ ሠላሳ አምስት ዓመት የዕድሜ ክልል የሚገኙት ሕፃናትና ወጣቶች የሰንበት ት/ቤት አባላት ይሆናሉ፡፡ ዲያቆናት በመማርና በማስተማር፣ ቀሳውስትና መምህራን በማስተማር በሰንበት ት/ቤቱ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

፪. ለሕፃናትና ለወጣቶች እንደየዕድሜያቸው መጠን መምህር በመመደብ በማዕከል ደረጃ በሚወጣው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ትምህርት መስጠቱን ይከታተላል፡፡

፫. በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ተምረው የማስተማር ብቃት ያላቸውን እየመረጠ ተጨማሪ ሥልጠና በመስጠት የበላይ አካልን እያስፈቀደ እንዲያስተምሩ ያደርጋል፡፡ ያልተፈቀደላቸው እንዳያስተምሩ ይቈጣጠራል፤ ይከላከላል፡፡

፬. በሰንበት፣ በዐበይት በዓላትና ቀናት የዕለቱንና የሳምንቱን መርሐ ግብር በማውጣት የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት፣ የሃይማኖት ትምህርት፣ የቅዳሴ ተሰጥዎና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

፭. ሕፃናትና ወጣቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እን ዲጸኑ የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ፣ ግብረገብ እንዲሆኑ ከአስተዳደሩ መመሪያ እየተቀበለና በቅርብ እየተከ ታተለ ያስተምራል፤ ይመክራል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፮. ለምእመናን ትምህርት የሚሰጡ፣ በሊቃውንት ጉባኤ የተመረመሩና በማ ዕከል የተፈቀዱ መንፈሳዊ መዝሙራትን እንዲያጠኑ የዕለትና የሳምንት መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

፯. ወጣቶች መንፈሳዊ ዕውቀታቸው እንዲዳብር ልዩ ልዩ የመማሪያ መሣሪያዎች የሚገኙበት ቤተ መጻሕፍትን ያቋቁማል፡፡

፰. ከሰንበት ተማሪዎች በበዓላትም ሆነ በሌላ ዝግጅት ጊዜ በትርኢት መልክ የሚቀርበው መንፈሳዊ ዝግጅት በቅድሚያ ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ቀርቦ ከተመረመረና ከተጠና በኋላ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

፱. የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በማንኛውም መንገድ ለመንፈሳዊ አገል ግሎት የሚሰበስቡት ገንዘብ ለአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ገንዘብ ቤት ገቢ ይሆናል፡፡ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ ዝርዝር ጥናቱ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ቀርቦ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲. ማንኛውንም የሚሰበስቡትን ሀብት ገንዘቡን በቤተ ክርስቲያኒቱ ሞዴል ፴ እና ፴፩ ንብረቱን በሞዴል ፲፱ ሰብስቦ ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት ገቢ ያስደርጋል፡፡ ገንዘቡንና ንብረቱንም በአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያስመረምራል፡፡

፲፩. የሰንበት ት/ቤት አመራር ሊሆኑ የሚገባቸው ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች ሆነው በሰበካ ጉባኤው አስመራጭነት በመላው ሰንበት ት/ቤት አባላት ይመረጣሉ፡፡ የሚያገለግሉትም ለ፫ ዓመታት ይሆናል፡፡ የሰንበት ት/ቤት አባላት ከፈለጓቸው ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ተመርጠው ለ፫ ዓመታት ያገለግላሉ፡፡

፲፪. ቀሳውስት የንስሓ ልጆቻቸው ልጆች መንፈሳዊውን ትምህርት እንዲ ከታተሉ ወላጆችም ልጆቻቸው በሰንበት ት/ቤት ተመዝግበው መንፈ ሳዊውን ዕውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታቸው መሆኑን ያሳውቃል፤ ይከታተላል፡፡

፲፫. የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች መንፈሳዊውን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችንን እምነትና ሥርዓት በተከተለ ሁኔታ የመለያ ልብስ (ዩኒፎርም) እንዲዘጋጅላቸው ያስደርጋል፡፡

፲፬. በሰበካ ጉባኤ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አካል ካልታወቀና በጽሑፍ

ካልተፈቀደ በስተቀር በሰንበት ት/ቤት ስም የአዳር መርሐ ግብር እንዳ ይደረግ በጥብቅ ይከታተላል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፲፫. ከስብከተ ወንጌልና መንፈሳዊ ት/ቤት ክፍሎች ጋር በመተባበር በሀገረ ስብከቱ እንዲያስተምሩ የተፈቀደላቸው መምህራንን ብቻ እየጋበዘ ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ብቃትና ጥራት ያለው ትም ህርት እንዲሰጣቸው ያስደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፳፪

## የዕቅድና ልማት ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ልዩ ልዩ የሥራ ዕቅዶች ማስፈጸሚያ ገንዘብ ፣ የዕቃ፣ የዕውቀትና የጉልበት ርዳታና መዋጮ ከምእመናን፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ሊገኝ የሚችልበትን ሁኔታ እያጠና ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፪. ለአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የገቢ ምንጭ የሚገኝበትን ተስማሚ የሥራ መስክ ያዘጋጃል፤ ለንዋየ ቅድሳት፣ ለመጻሕፍት፣ ለአልባሳትና ለሌላም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውልና ለገቢ ማስገኛ የሚሆን የቅርጻ ቅርጽና የተግባረእድ ሥራ እንዲቋቋም ያስደርጋል፡፡

፫. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችም ያላቸውን ዕውቀት፣ የጥሬ ገንዘብ (ሀብት)፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎችና የሰውን ጉልበት ጭምር በማስተባበር ለቤተ ክርስ ቲያኑ ልማት ሥራ እንዲውል ያስደርጋል፡፡

፬. ካህናት በትርፍ ጊዜአቸው ራሳቸውን ለመርዳት እንዲችሉ የገቢ ምንጭ ለማስገኘት የሚመለከታቸውን በማስተባበር ከቤተ ክርስቲያኑ

አገልጋዮች መካከል እየሠለጠኑ በየዝንባሌያቸው እንዲሰማሩና የምርት ውጤት እንዲያስገኙ ያስደርጋል፡፡

፷. ከልማቱ የሚገኘው ገቢ በሰበካ ጉባኤው ካርኒ እየተሰበሰበና በገንዘብ ቤቱ እየተጠቃለለ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሒሳብ ገቢ ይሆናል፡፡

፷. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ቦታዎች እንዲለሙ እያጠናና እያስጠና ተግባራዊ እንዲሆን ለሰበካ ጉባኤው ያቀርባል፡፡

፯. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የይዞታ ቦታዎች ከመመሪያ ውጪ የበላይ አካል ሳይፈቅድ ለሦስተኛ ወገን እንዳይሰጡ ይቈጣጠራል፤ ይከታተላል፡፡

፰. የሥራውንም ውጤት በሚመለከት በየሦስት ወር ለሰበካ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ ፳፫
## የምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. ይህ ክፍል በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን የሰንበቴ፣ የዕድር፣ የልዩ ልዩ ምግባረ ሠናይ ማኅበራትን እና በጎ አድራጊ ግለሰቦችን በማስተባበር አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን አረጋውያንና ችግረኞችን ለመርዳት የሚያስችል ክፍል ነው፡፡

፪. በአጥቢያው ሰበካ ያሉት ችግረኞች በተደራጀ አቋም የሚረዱበትንና ራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ ለመፈለግ መንግሥታዊና መንግ

ሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል፡፡

፫. ለመሥራት ችሎታና ዕውቀት ያላቸው ችግረኞችን መርጦ በራስ አገዝ የልማት መርሐ ግብር ሠርተው እንዲጠቀሙ ከሚመለከታቸው ሁሉ ጋር በመነጋገርና በመጻጻፍ ሁኔታውን እየተከታተለ ያስፈጽማል፡፡

፬. መንፈሳዊና ሥጋዊ አኗኗራቸው የተሻሻለ እንዲሆን ከካህናቱ መካከል በዕውቀቱና በግብረ ገብነቱ የተሻለው ካህን ተመርጦ በተወሰነ ሰዓት እንዲያስተምራቸውና እንዲመክራቸው የትምህርት መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

፭. በሰንበት ፣ በወርና በዓመት በዓላት በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በትምህርተ ወንጌል ሰዓትና ሌላውም መንፈሳዊ አገልግሎት ሲካሄድ በዓውደ ምሕረት እየተዘዋወሩ ድምፅ በማሰማት እንዳያስቸግሩ አመች በሆነ ቦታ በአንድነት አሰባስቦ ጸሎተ ቅዳሴና ትምህርተ ወንጌሉን እንዲ ከታተሉ ርዳታም ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፮. በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት ጊዜያዊና ዘላቂ ርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ እያ ጠና ለሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በማቅረብ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

፯. ምእመናንን፣ በጎ አድራጊ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን በማስተባበር ችግ ረኞች፣ ጧሪና ረዳት የሌላቸው ሽማግሌዎችና ባልቴቶች በቤተ ክርስ ቲያን አካባቢ መጠለያና ምግብ እንዲያገኙ ዐቅም በፈቀደ መጠን ያመቻቻል፤ ጤናቸውንም ይንከባከባል፡፡

## አንቀጽ ፷፬

## የሕግ ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና ድንጋጌዎች በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚወሰኑ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ለሰበካው ጉባኤ ኀላፊዎችና በጠቅላላው ለካህናትና ለምእመናን በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት ሕጋዊ መመ ሪያና መግለጫ እየሰጠ እንዲያውቁትና እንዲያጠኑት ያደርጋል፡፡

፪. በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ በካህናትም ሆነ በምእመናን መካከል የሚ ፈጠር አለመግባባት ቢኖር ወደ ክስ ደረጃ ሳይደርስ እርስ በእርስ በመተ ራረም በይቅርታና በዕርቅ እንዲወገድ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

፫. የክሱ አቤቱታ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ የከ ሳሹና የተከሳሹን የሕግ መብት በመጠበቅ የሁለቱንም ወገን ማስረ ጃዎች በጥንቃቄ ተመልክቶ በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፷፫ መሠረት የውሳኔ ሐሳብ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፬. በክብረ በዓል ቀን ከሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በሚ ሰጠው መመሪያ መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የበዓሉን ሥነ ሥርዓት ያስከብራል፡፡

፭. ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት የማይጠቅሙና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የማይውሉ ሸቀጣ ሸቀጦች በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ እንዳይሸጡና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት የሚቃረኑ

ተግባራት እንዳይፈጸሙ ከሰብከተ ወንጌል እና ከሰንበት ት/ቤት ክፍ ሎች ጋር በመሆን ይከላከላል፤ ሥነ ሥርዓቱንም ያስጠብቃል፡፡

፯. ማንኛውንም መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕግ ነክ ጉዳዮችን ይከታተላል፤ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደርም የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

፰. ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክሎ በማንኛውም የሕግ አካል ዘንድ ይከራ ከራል፡፡

## አንቀጽ ፳፫
## የንብረት፣ የንዋየ ቅድሳትና የቅርሳ ቅርስ
## ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. ከታቦተ ሕጉ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት፣ አልባሳት፣ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ለዚሁ ሥራ ተመርጦ በተመደበ ካህን (ቄስ ገበዝ) በጥንቃቄ እየተመዘገቡ እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

፪. የሰበካ ጉባኤውን አላቂና ቋሚ ዕቃዎችን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በየዓይነታቸው ለይቶ ይመዘግባል፡፡

፫. ወጪ ሆነው ለሥራ የሚሰጡትን ዕቃዎችና ንብረቶች በደረሰኝ ያስረ ክባል፤ ወጪ የተደረጉ ንብረቶችም ሥራ ላይ መዋላቸውንና መጠበቃ ቸውን ይቈጣጠራል፤ የሚመለሱትንም መርምሮ ይረከባል፡፡

፬. ለቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጣዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉትን ሁሉ እንዲሟሉ ያስደርጋል፡፡

፭. በቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ቅርሳ ቅርሶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋል፤ ለጐብኝዎችና ለታሪክ ጸሐፊዎችም ተለይ ተው እንዲታዩ አድርጎ ምቹ በሆነ ሥፍራ በጥንቃቄ ያዘጋጃል፡፡

፺. ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት፣ ሥዕሎች፣ አልባሳት፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ፣ ከብረትና ከዕፅ የተቀረጹ መስቀሎችና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት፣ የባህልና የወግ ዕቃዎች ለብል፣ ለዝገት፣ ለፍሳሽ፣ለእሳትና ለመሳሰሉት አደጋዎች እንዳይጋለጡ፡-

ሀ) ለቅርሳ ቅርስ አጠባበቅ አመች የሆነ ዕቃ ቤት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

ለ) ቅርሳ ቅርሱን በኀላፊነት የሚጠብቁ ሠራተኞችና አስጐብኝዎች እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡

ሐ) በየበጀት ዓመቱ መጨረሻና የቅርሳ ቅርስ ኀላፊ ዝውውር በሚደ ረግበት ጊዜ ሁሉ ማንኛውም ቅርስ እየተቈጠረና እየተመረመረ ውጤቱ ደረጃውን ጠብቆ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ መግ ለጽ ግዴታው ይሆናል፡፡

መ) ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ጐብኝዎች ሲመጡ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በየጊዜው በሚሰጠው የአፈጻጸም መመሪያና የክፍያ ደረጃ መሠረት ከጐብኝዎች ገቢ እንዲገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

ሠ) ከጐብኝዎች የሚገኘው ገቢ በሕጋዊ ካርኒ እየተመዘገበ ከቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ሒሳብ ጋር እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

፺፩. ለአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ንብረትና ታሪካዊ ቅርሳ ቅርስ ኀላፊ ሆኖ የሚመደበው ካህን የገንዘብ ጒድለት ያልተ ገኘበት፣ በንብረት ማባከንም ሆነ በሌላ ወንጀል ተከሶ በጉባኤ ያልተወ ሰነበት፣በፍርድ ቤት ያልተፈረደበትና በቂ ተያዥ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፳. ረዘም ላሉ ዘመናት ያገለገሉ አልባሳት፣ ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት አገልግሎት ከመስጠት ነጻ ሆነው ዓይነታቸው ሳይለወጥ ጥገና እየተ ደረገላቸው በቅርስነት ተከብረው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

፱. ሀ/ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅርሶች በልዩ ልዩ ምክንያት በውሰት እንዲ ወሰዱ በሚጠየቅበት ጊዜ በክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ሰብሳቢነት በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ተወስኖና ተፈቅዶ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤትም አውቆት የማስፈጸሚያ ትእዛዝ ከሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሲደርሰው ሕጋዊ በሆነ ደረሰኝ አስፈርሞ ለተ ወሰነ ጊዜ በትውስት እንዲሰጥና እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

ለ/ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ማስታወሻ በማቅረብ ወደ ነበረበት ቦታ እስኪመለስ ድረስ እስከ መጨረሻው ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡

፲. ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኑ ንብረቶች በየዓመቱ መጨረሻ እየተቈጠሩና እየተመዘገቡ መያዛቸውንና በጥንቃቄ መቀመጣቸውን ያረጋግጣል፡፡ ያሉትንና የሌሉትንም ለይቶ በመዘርዘር ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፲፩. በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ጥንታዊና አገር በቀል ዕፀዋት ደኅንነ ታቸው ተጠብቆ እና እንክብካቤ እየተደረገላቸው እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፳፪
## የሒሳብ ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. የሒሳብ መዛግብትን በተሟላ ሁኔታ አዘጋጅቶ ገቢና ወጪውን ይመዘግባል፡፡

፪. ገቢው በሕጋዊ የሒሳብ አያያዝ ደንብ መሠረት በሕጋዊ ደረሰኝ መግባቱንና ወጪውም ሕጋዊ የወጪ አርእስትን ጠብቆ በመደበኛ የወጪ ማዘዣና ማስመስከሪያ ሰነድ መውጣቱን እያረጋገጠና እየተ ከታተለ ይሠራል።

፫. በየወሩ መጨረሻ ሒሳቡን በመዝጋት የወሩን ገቢ፣ ወጪውንና ከወጪ ቀሪውን በሠንጠረዥ እያዘጋጀ ለጽ/ቤቱ ያቀርባል።

፬. ማንኛውም የገንዘብ ወጪ ከተፈቀደውና ከተወሰነው በጀት በላይ እንዳያልፍ ይቈጣጠራል፤ ይጠብቃል።

፭. በጀት በሚደለደልበት ጊዜ ለሚደለደለው በጀት በቂ ገንዘብ መኖ ሩን ያረጋግጣል።

፮. የበጀት ዓመቱ ከማለቁ ከሁለት ወራት በፊት በባንክና በሣጥን ያለውን ገንዘብ የየወሩን ገቢ ገምግሞ የተከታዩን ዓመት በጀት በመ ሥራት የበጀቱን ዝርዝር ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ያቀርባል።

፯. ዓመታዊም ሆነ ወርኃዊ ሒሳብ እንዲመረመር ሲታዘዝ የገቢና የወጪ ሰነዶችን በማቅረብ ያስመረምራል።

፰. የሒሳብ ሰነዶችንና ቼኮችን በጥንቃቄ ይይዛል።

፱. የገንዘብ ገቢና ወጪ ሰነዶች (ሞዴሎች) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የበላይ ተቈጣ ጣሪነትና በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኀላፊነት ታትሞ በሚወጣ በአንድ ዓይነት ደረሰኝ (ካርኒ) ብቻ ይሠራል፤ የሚሠራ መሆኑንም ያረጋግጣል።

## አንቀጽ ፳፯
## የገንዘብ ቤት ሥራና ኀላፊነት

፩. ገንዘብ ያዡው ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን የገባውን ገንዘብ ሁሉ በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፶፪ ተራ ቍጥር ፬ በተጠቀሰው ሕጋዊ ደረሰኝ (ካርኒ) ይቀበላል፡፡

፪. የተቀበለውን ገንዘብ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በዕለቱ ባንክ ያስገባል፡፡ ገንዘቡን የተቀበለበት ጊዜ (ሰዓት) ካለፈ በኋላ ከሆነ ወይም ባንክ ዝግ በሆነበት ቀን ከሆነ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመፈራረም ገንዘቡ በጊዜያዊነት በካዝና እንዲቀመጥና ገንዘብ ቤቱ እንዲታሽግ ያደርጋል፡፡

፫. በአካባቢው ባንክ ከሌለ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው በሚወ ስነው ቦታ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

፬. በካዝና ስለሚቀመጠው መጠባበቂያ ሒሳብ እንደጊዜውና እንደአ ካባቢው እየታየ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በሚወስነው መሠ ረት ይፈጽማል፡፡

፭. ለማንኛውም የገንዘብ ወጪ ሕጋዊ ትእዛዝ ሲደርሰው ብቻ በመ ደበኛ የወጪ ማስመስከሪያ ሰነድ (ቫውቸር) አስፈርሞ ይከፍላል፡፡

፮. ገቢና ወጪውን በተለይ በተዘጋጀ የገቢና የወጪ መዛግብት ላይ ይመ ዘግባል፤ በየወሩ መጨረሻ በጠቅላላ የገባውንና የወጣውን ገንዘብ ልክ ከወጪ ቀሪውን ከሒሳብ ክፍሉ መዛግብት ጋር እያመሳከረ ሒሳቡን በጥንቃቄ መዝግቦ ይይዛል፡፡

፯. የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የወሰነውን የወጪ

ሒሳብ አስተዳዳሪው ማዘዣ ካልጻፈ በስተቀር አንዳችም ገንዘብ ወጪ ማድረግ አይችልም፣ ሆኖም አስተዳዳሪው በሌለ ጊዜ በም/ሰብሳቢው ትእዛዝ የታወቀውን፣ የተወሰነውንና የተመደበውን የወር ወጪ ብቻ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፳፰
## የቍጥጥር ክፍል ሥራና ኀላፊነት

፩. ገቢና ወጪውን በየዕለቱ፣ በየሳምንቱ እና በየወሩ ተቈጣጥሮ ገንዘቡ በባንክ መቀመጡን ያረጋግጣል፡፡

፪. ገቢና ወጪ የተደረገባቸው ካርኒዎችና ሰነዶች ሕጋዊ መሆናቸውን ይመረምራል፡፡

፫. ከሰበካ ጉባኤው ንብረት መዝገብ ጋር አስተያይቶ በንብረት ክፍሉ ኀላፊነት የሚገኙትን ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን በየመልካቸው ለይቶ በአገልግሎት ያለቁትን፣ በአያያዝ የተበላሹትን፣ የጐደሉትን፣ የተረፉ ትንና ያልተመዘገቡትን ንብረቶች ሁሉ እያስቈጠረ ዓይነቱና ብዛቱ በሠንጠረዥ ተዘጋጅቶ መመዝገቡን እያመሳከረ ይቈጣጠራል፡፡

፬. የሒሳቡ አያያዝና የንብረቱ አጠባበቅ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን በዝርዝር መዝግቦ በየሦስት ወሩ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት መግለጫ ያቀርባል፡፡

፭. በገንዘብ አያያዝና በንብረት አጠባበቅ ጒድለት ቢገኝ ጒድለት ወይም ጥፋት ያደረሰውን ግለሰብ መተማመኛ አስፈርሞ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፮. በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡት የኢጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የከፈሉት ክፍያ በቃለ ዐዋዲው መሠረት መክፈሉንና ማንኛ ውም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ ገቢ በትክክል መግባቱን ይቈጣ ጠራል፡፡

፯. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ ለወርና ለዓመት ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን ይቈጣ ጠራል፡፡

፰. በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን የሥራ ዘርፎች የሚካሄዱት ሥራ ዎች ሁሉ በወቅቱ መከናወናቸውን እየተቈጣጠረ ሥራው የሚመለ ከታቸውን ሠራተኞች በማሰባሰብ ወይም በየክፍሉ በመዘዋወር እንደ አስፈላጊነቱ ስለ ሒሳብ አያያዝና የሞዴሎች አጠቃቀም ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፱. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት የስእለትና የሙዳየ ምጽዋት ሣጥኖች ምልክትና መለያ ቍጥር እየተሰጣቸው ብዛታቸው እየታወቀ፤ የተቀመጡበትም ቦታ ግልጽና አስተማማኝ መሆኑን ያረጋግጣል፤ በሰበካው አስተዳደር ጽ/ቤት ያልተመዘገቡና ያልታወቁ ሣጥኖችም ሆኑ ሌሎች የገንዘብ መሰብሰቢያዎች ሁሉ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይኖሩ በጥብቅ ይቈጣጠራል፡፡

፲. የስእለትና የሙዳየ ምጽዋት ሣጥኖች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በተመረጡ አባላት፣ አስተዳዳሪው፣ ሒሳብ ሹሙና ራሱም ተቈጣጣሪው በሚገኙበት የጋራ ፊርማና በደብሩ ማኅ

ተም መታሸጋቸውንና ሲከፈቱም የፈረሙት አባላት ሁሉ መገኘታቸውን ይከታተላል፡፡

፲፩. በዐውደ ምሕረቱም ሆነ በሌላ ቦታ ሙዳየ ምጽዋትና ጥላ በማዞር ስጋጃ በማንጠፍ ወይም በሌላ መንገድ የሚሰበሰበው ማንኛውም ገንዘብና ልዩ ልዩ ስጦታ ሁሉ በአግባቡ እየተመዘገበ በቤተ ክርስ ቲያኑ ካርኒ (ደረሰኝ) ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፲፪. በስእለትና በሌላም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት እንስ ሳት፣ ብር፣ ወርቅና ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ግምታቸው እንዲታወቅ እና በሕጋዊ መንገድ ገቢ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡፡

፲፫. ከንብረት ክፍሉ ጋር በመተባበር የቤተ ክርስቲያኑን ንብረት በየዓ መቱ እያስቈጠረና እየመዘገበ የጎደለውንና የጨመረውን አረጋግጦ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፲፬. ከንብረት ክፍል ወጪ ሆነው ለሚመለከተው ክፍል የሚሰጡትን ንብ ረቶች በደረሰኝ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ የተሰጡትም ሥራ ላይ መዋላ ቸውንና መጠበቃቸውን ይቈጣጠራል፤የሚመለሱትንም መርምሮ ትክክል መሆናቸውን አረጋግጦ ንብረት ክፍሉ እንዲረከብ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፳፱

## የሕንጻ ሥራ፣ ጥገናና እድሳት ክፍል

## የሥራ ኀላፊነት

፩. ይህ ክፍል ቤተ ክርስቲያንን፣ ቤተልሔምን፣ ትምህርት ቤትን፣ የሕ ክምና ተቋማትን፣ ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ሕንጻዎችን፣ የመሰብሰቢያ

አዳራሽን፣ የሰንበት ት/ቤት መማሪያ ክፍልን፣ የካህናትና የእንግዶች ማረፊያ ቤትን፣ ቅጽረ ቤተ ክርስቲያንን ሌሎችንም እንደ አስፈላጊነታቸው ሊሠሩ የሚገባቸውን ዕቅዶች አጥንቶ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ እያቀረበና እያስፈቀደ በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፲፪ ተራ ቊጥር ፲፯ መሠረት ከሚቋቋመው የሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ ጋር በመተባበር የሚሠራ ክፍል ነው።

፪. ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ፣ ጥገናና እድሳት አፈጻጸም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ልዩ የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ደንብና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፫. የሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ በሚቋቋምበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ጽ/ቤት መመሪያ እየተቀበለ ካህናትና ምእመናን በጉዳዩ እንዲያስቡበት አስፈላጊውን ቅስቀሳ ያደርጋል፤ ትምህርትም ይሰጣል።

፬. ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ሥራ የሚውል የገንዘብና የቁሳቊስ ርዳታ የሚገኝበትን መንገድ እያጠና ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሚቋቋሙት የሕንጻ አሠሪ ኮሚቴዎች አማካይነት ርዳታው እንዲሰበሰብ ያደርጋል። የርዳታ መሰብሰቢያውም ጊዜና ቦታ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው በሚወስነው ይሆናል።

፭. ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ሥራ የሚያስፈልጉትን የገንዘብና የንብረት መቀበያና ወጪ ማድረጊያ ካርኒዎችን፣ ሰነዶችንና መዛግብትን በጠቅላላ የሚያስፈልጉትን የጽሕፈት መሣሪያዎች ሁሉ ከአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ አስተዳደር መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት በደረሰኝ እየተረከበ ለተቋቋመው ኮሚቴ እንደ አስፈላጊነቱ ያከፋፍላል።

፮. ለሕንጻው ሥራ ርዳታ ለሚለግሱ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት የሚተላለፈውን የጥያቄና የትብብር ደብዳቤዎች ለሚመለከተው ሁሉ እንዲደርስ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

፯. የሕንጻ ሥራ ዐቢይ ኮሚቴው በሚያደርገው ስብሰባ ሁሉ እየተገኘ ስለሥራው ሂደት የተደረሰበትን ፍሬ ሐሳብ ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

፰. በሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ስም ከአካባቢው ምእመናን የሚሰበሰበውና ከልዩ ልዩ በጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚለገሰው ገንዘብ በቤተ ክርስ ቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሒሳብ ቍጥር ተለይቶ መቀመጡን ያረጋ ግጣል፤ ወጪ በሚሆንበት ጊዜም በአንቀጽ ፲፪ ተራ ቍጥር ፲፱ (ለ) መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል።

፱. የሕንጻው ሥራ ተጠናቅቆ ካበቃ በኋላ ለሕንጻው ሥራና ከሕንጻው ጋር ግንኙነት ያለው ንብረት፣ የገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲሁም ከወጭ ቀሪ ሒሳብ በሚመለከተው የበላይ አካል በምርመራ (በኦዲት) ተጣ ርቶ ለቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ቤትና ንብረት ክፍል ገቢ መሆኑን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል።

፲. የሙታን መካነ መቃብር ሥርዓት በሌለው ልሾ ሥራና በሐውልት ግንባታ እየተጣበበ የመጣውን ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ችግር ለማቃ ለል ለወደፊቱ ይህ ዓይነቱ አሠራር ቀርቶ በምትኩ የተሻሻለ አሠራር እንዲኖር ለማድረግ ባለሙያዎችን እያማከረና ዕቅዱን ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ እያቀረበ ሲወሰንና በበላይ አካል ሲፈ ቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

፲፩. ቦታው ለቀጣይ አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሰባት ዓመታትና ከዚያ በላይ የቆየ ዐፅመ ክርስቲያን በክብር የሚያርፍበት ቤት እንዲ ዘጋጅና እንዲጠበቅ ያስደረጋል፡፡

፲፪. በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ክፍት ቦታዎች እና ለመካነ መቃ ብር የተከለሉት ስፍራዎች በጽዳት እንዲጠበቁና የተለያዩ የዕፀዋት ዓይነቶችንና አበቦችን ያስተክላል፤ ያስከብራል፡፡

፲፫. የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ዲዛይን ትውፊቱንና ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲ ሠራ ያደርጋል፡፡ ዲዛይኑ ሊቀ ጳጳሱ በሚሰበስቡት የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ታይቶ፣ ተወስኖና ጸድቆ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛ ውንም ዲዛይን መሥራት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ ፴

## የአኃዛዊ መረጃ /ስታትስቲክስ/ ክፍል

## ሥራና ኀላፊነት

፩. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ነዋሪ ለሆኑ ምእመናን ቋሚ መዛግብት ሆነው የሚያገለግሉትን፡-

ሀ) መዝገበ ልደትና ጥምቀት

ለ) መዝገበ ሕያዋን፣ መዝገበ ሙታን እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መዛ ግብትን ሁሉ እንዲሠራባቸው ያደርጋል፡፡

፪. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ስምና አድራሻ፣ የትከል ዓይነትና ዘመን፣ የሕንጻውን አሠራር፣ ቅርጽና ዓይነቱን፣ ቁመቱንና ስፋቱን አይቶና አጣርቶ ባለሙያ እያማከረ ይመዘግባል፡፡

፫. የአጥቢያውን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት፣ ቀሳውስት፣ መምህራን፣ ሰባክያን፣ ዲያቆናት፣ መዘምራንና ልዩ ልዩ ሠራተኞች ብዛት እንዲሁም የምእመናንን ብዛት በጢስ፣ በቤተሰብ፣ በዕድሜ፣ በፆታና በትምህርት ደረጃ ለይቶ ይመዘግባል፡፡

፬. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የጉባኤ መምህር ካለ ስሙንና የተማሪዎችን ብዛት የትምህርቱን ዓይነት እና የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችን ብዛት የሚማሩትንም የትምህርት ዓይነት ይመዘግባል፡፡

፭. ሕፃናት አርባ ቀንና ሰማንያ ቀን ሞልቶአቸው በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ክርስትና ሲነሱ በመዝገበ ልደት፣ ጥምቀትና በአጠቃላይ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን በተዘጋጀው መዝገበ ሕያዋን ላይ ይመዘግባቸዋል፡፡

፮. ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ስማቸውን በመዝገበ ሙታን ያስፍራል፡፡

፯. በዓመቱ መጨረሻ በጠቅላላ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን በነዋሪነት የተመዘገቡትን ክርስቲያኖችና ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ብዛት እንዲሁም የተወለዱትንና በዓመቱ ውስጥ በሥራ ዝውውርም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ አጥቢያው ቤተ ክርስቲያን በነዋሪነት አዲስ የመጡትንም ሆነ ወደ ሌላ አጥቢያ የሄዱትን ሁሉ በጥንቃቄና በጥራት መዝግቦ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

፰. የአጥቢያ ሰበካውን የሰውና የገንዘብ ኀይል በየዓመቱ እየመዘገበ ካለፈው ዓመት ጋር ያለውን ልዩነት እያነጻጸረ በሠንጠረዥ ወይም በሥዕላዊ መግለጫ ያሳያል፡፡

፱. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመገናኘት ለአጥቢያው የሚያስፈልገውን አኃዛዊ መረጃ ሁሉ ይሰበስባል፡፡

፲. ሰበካ ጉባኤ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ተመራጭ የሰበካ ጉባኤ አባላትን እያማከረ የአጥቢያው ምእመናን የአባልነት ክፍያ በወቅቱ እንዲከፍሉ ያስተባብራል፡፡

፲፩. የቤተ ክርስቲያኗ ገቢ የሚያድግበትን ሁኔታ እያመቻቸና የሰበካ ጉባኤ አባላትን እያስተባበረ ይሠራል፡፡

## ምዕራፍ ፫

## ስለ ወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎች

## አንቀጽ ፴፩

## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት የሥራ ክፍሎች እና ሥልጣንና ተግባር

## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አቋም

፩. አመሠራረት፤

ሀ) በወረዳው ቤተ ክህነት ሥር ብዛታቸው ከአንድ በላይ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በተወካዮቻቸው አማካይነት በወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሰብሳቢነት በአንድነት ተሰብስበው የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያቋቁማሉ፡፡ ተወካዮቻቸውም ከእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የተመረጡና በቤተ ክርስቲያኑ አስተ ዳዳሪ የሚመሩ አንድ ካህን፣ አንድ ምእመንና አንድ ወጣት ሲሆኑ የወረዳው ቤተ ክህነት ጸሓፊና የልዩ ልዩ ክፍል ኀላፊዎች አባላት ይሆናሉ፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይሆናል፡፡

ለ) የወረዳው ሰበካ መንፈዊ ጉባኤ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግቡ ለማድ ረስ ኀላፊነቱንና ተግባሩን ለማከናወን እንዲችል በወር አንድ ጊዜ የሚሰ በሰብ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እና የወረዳው ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ፤

ሐ) የወረዳው ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት (የወረዳው ቤተ ክህነት ጽ/ቤት)፤

መ) የወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ ክፍሎች (የወረዳው ቤተ ክህ ነት የሥራ ክፍሎች) ናቸው፡፡

## አንቀጽ ፴፪

## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት

፩. የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የተወከለ ካህን ........................ የጉባኤው ሰብሳቢ

፪. በዚሁ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፫፣ ፬ እና ፭ ከተመለከቱት የካህናትና ምእመናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፸ ዓመት ያልበለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይም ምእ መን ............................ የጉባኤው ምክትል ሰብሳቢ

፫. በወረዳው ክልል ውስጥ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ................. የጉባኤው አባላት

፬. ከወረዳው ክልል ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠው የተወከሉ ካህናት ..................... የጉባኤው አባላት

፭. ከወረዳው ክልል ወስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠው የተወከሉ ምእመናን .................. የጉባኤው አባላት

፮. ከወረዳው ክልል ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠው የተወከሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ............... የጉባኤው አባላት

፯. የወረዳው ቤተ ክህነት ጸሐፊ ወይም እሱ በሌለ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የተወከለ ካህን .................. የጉባኤው አባልና ጸሐፊ፣

## አንቀጽ ፴፫
## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በምዕራፍ ፪ በአንቀጽ ፫ እና ፯ የተዘረዘረውን ዐላማና ተግባር እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀጥሎ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. በወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ተዘጋጅቶ በቀረበው የመነጋገሪያ ርእስ (አጀንዳ) መሠረት የወረዳውን ሰበካ አባላትና አገል ጋዮች ሁኔታ፣ የሥራ ክንውን፣ የገንዘብና ንብረት አጠቃላይ መግለጫ ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪. የቀረበለትን የወረዳውን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ ዕቅድና የልዩ ልዩ አገልግሎት መርሐ ግብር እየመረመረ ሲስማማበት ከአስተያየት ጋር ለመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

፫. ለበላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀርቦ ለተፈቀደው የሥራ ዕቅድና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ይወስናል፤ መሰብ ሰቡንና በሥራ ላይ መዋሉንም ይቈጣጠራል፡፡

፬. የወረዳውን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገንዘብና ንብረት በሒሳብ አጣሪ (ኦዲተር) ያስመረምራል፡፡

፭. ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ከአራት ያላነሱ ከስምንት ያልበለጡ አባላትን ይመርጣል፡፡

፮. የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብ ከት ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፴፩
## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ
## (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

፩. የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ በሀገረ ስብከት የተወከለ ካህን ....................................የጉባኤው ሰብሳቢ

፪. በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፫፣፬ እና ፭ ከተመለከቱት የካህናትና ምእ መናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፷ ዓመት ያልበለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይም ምእመን ........................... የጉባኤው ም/ሰብሳቢ

፫. ቍጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ የአጥቢያ ቤተ ክርስ ቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን የሚወክሉ ካህናት.................................. የጉባኤው አባላት

፬. ከአንድ የወጣት ተወካይ ጋር ቍጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን የሚወክሉ ምእመናን ......................................የጉባኤው አባላት

፳. የወረዳው ቤተ ክህነት ጸሐፊ ወይም እሱ በሌለ ጊዜ በሀገረ ስብከት የተወከለ ካህን ..........................................የጉባኤው አባልና ጸሐፊ

## አንቀጽ ፴፫
## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ
## (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲ በምዕራፍ ፪ አንቀጽ ፳ እና ፯ ከተዘረዘረው ዐላማና ተግባር በተጨማሪ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. በወረዳው ውስጥ የሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤያት የተቋቋሙበትን ዐላማ ከግቡ እንዲያደርሱ ተግባራቸውንም እንዲያከናውኑ ያደርጋል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፪. ለአጥቢያ ሰበካ ጉባኤ አባልነት ተመርጠው በአስመራጭ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ተፈርሞና በደብሩ አስተዳዳሪ ሽኚ ደብዳቤ የተላከለትን የምርጫ ውጤት መርምሮ እንዲጸድቅ ከሪፖርት ጋር ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

፫. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚደርሱትን ልዩ ልዩ ጉዳዮችንና መግለጫዎችን መርምሮ አስፈላጊውንና ተገቢውን ተግባር ይፈጽማል፡፡

፬. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደርና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚከፈለውን ፳% (ሃያ ከመቶ) ገንዘብ ተቈጣጥሮ በወቅቱ ለሀገረ ስብከቱ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፫. በወረዳው ውስጥ ለጋራ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጥቅም የሚውሉ የኀብረት ሥራ ዕቅዶችንና የአጥቢያ ሰበካውን አገልግሎት መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ለጉባኤው ያቀርባል፡፡

፬. ለተፈቀደው የኀብረት ሥራ ዕቅድ ማስፈጸሚያና ለልዩ ልዩ አገልግሎት ማከናወኛ ከእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነውን ገንዘብ በወረዳው ቤተ ክህነት ኀላፊነት በሕጋዊ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡

፭. ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ጋር በአግባቡ ተባብሮ ይሠራል፤ ከበላይ የሚተላለፉትን መመሪያዎችና ትእዛዞች ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፮. ያለፈውንም የሥራ ክንውን፣ የወደፊቱን የሥራ ዕቅድ፣ የበጀት ድል ድልና የአጥቢያ ሰበካውን አባላትና አገልጋዮች ሁኔታ መግለጫ ለወረ ዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አቅርቦ ከታየና ስምምነት ከተደረገበት በኋላ ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ለውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

፯. ከየአጥቢያው የሚቀርብለትን የሥራ ዕቅድ መርምሮ በወረዳው ሊቀ ካህናት በኩል ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

፰. ከአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት መካከል ለሀገረ ስብከቱ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚወከሉ ከወረዳው ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናት ወይም ወኪል ሌላ አንድ ካህን፣ አንድ ምእመንና አንድ ወጣት ይመርጣል፡፡

፱. ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከተወከሉት መካከል ለሀገረ ስብ ከቱ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በመመረጣቸውና በሌላም

ምክንያት የወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ቍጥር ከአምስት ያነሰ እንደሆነ በምትካቸው በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ ፫ በአንቀጽ ፲፩ በተራ ቍጥር ፬ በተገለጸው መሠረት ይፈጽማል፡፡

፲፪. የወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ተጠሪነቱ ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፲፫. የተመራጮች አባላት የአገልግሎት ዘመን በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፲፩ በተራ ቍጥር ፪ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፴፮
## የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

፩. በወረዳው ክልል ውስጥ ለሚገኙት ገዳማት፣ አድባራት፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና በየደረጃው ለተቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የሥራ አመራርና ከፍተኛ የአስተዳደር ኀላፊነት ያለው መሥሪያ ቤት ነው፡፡

፪. ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሆነ የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ይኖራል፡፡

፫. የቃለ ዐዋዲውንና ከሀገረ ስብከቱ የሚተላለፉትን ደንቦችና መመሪያዎች የሚፈጽምለትና የሚያስፈጽምለት አንድ የአስተዳደር ጉባኤና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፬. ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት የሥራ ክፍ ሎች መቋቋም በአንቀጽ ፲፮ ከሀ-ኘ የተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች (ክፍሎች) በወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ የሥራ

ዝርዝራቸው በቃለ ዐዋዲው ከአንቀጽ ፲፯ እስከ ፴ የተዘረዘረው የወረዳ ቤተ ክህነቱን ሁኔታ እያገናዘበና እንዲስማማ እያደረገ ለወረ ዳው ቤተ ክህነትም ያገለግላል።

## አንቀጽ ፴፯
## የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ ፪ በአንቀጽ ፫ እና ፮ የተዘረዘሩትን ዐላማና ተግባር እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፩. የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢና የበላይ ሥራ አስፈ ጻሚ በመሆን በቃለ ዐዋዲውና ከበላይ በሚሰጠው መመሪያና ውሳኔ መሠረት ሰበካ ጉባኤውን የመሰብሰብና በቃለ ጉባኤ የተመዘገቡትን ውሳኔዎች የመፈጸምና የማስፈጸም፣ የመጻጻፍ፣ የሒሳብና የንብረት አጠ ባበቅ ሌሎችንም የሰበካ ሥራዎችን የመሥራትና የማሠራት በጠቅላላው ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር ኀላፊና ተጠሪ ነው።

፪. በወረዳው ሰበካ ውስጥ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በቃለ ዐዋዲው መሠረት በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ የማድረግ ኀላፊነት አለበት።

፫. የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ምርጫ አፈጻጸም ግንባር ቀደም አስተባባሪ ስለሆነ ምር ጫው ከመከናወኑ አስቀድሞ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ቃለ ዐዋዲውን የሚያጠናክር ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል።

፬. በወረዳው የሚገኙትን የቤተ ክህነት ሠራተኞችንና ሌሎችንም በማስ ተባበር በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደርና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ ያለ ክፍያ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

፭. ለወረዳው ቤተ ክህነት የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ከሀገረ ስብከቱ መመሪያ እየተቀበለ በቃለ ዐዋዲው ደንብ መሠረት ያቋቁማል፤ ያደራጃል፡፡

፮. ለየሰበካው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉትን የገንዘብና ንብ ረት ገቢና ወጪ ካርኒዎችንና ሞዴሎችን ሌሎችንም አስፈላጊ እትሞችን ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር በወቅቱ ያቀርባል፤ ያከፋፍላል፡፡

፯. ማንኛውም የሰበካ አስተዳደርና የልዩ ልዩ ክፍሎች ሥራ በቃለ ዐዋዲ መሠረት መካሄዱን ይቈጣጠራል፡፡

፰. በወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ውስጥ የሚገኙትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባ ላትና የሌሎችም ኀላፊዎች ምርጫ እንዲጸድቅ ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

፱. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የሥራ ዕቅድ ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አቅርቦ ካስጠና በኋላ እንዲጸድቅ ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም እንዲሠራበት ያደርጋል፡፡

፲. በየጊዜው የዕለትና የዘወትር መርሐ ግብር በማዘጋጀት በየሰበካው እየተ ዘዋወረ ወንጌልን በመስበክና በማሰበክ፣ ምእመናንን በማንቃትና በማጥ ጋት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲደራጅና እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

፲፮. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ለሀገረ ስብከቱ የሚከፈለው ገንዘብ በወቅቱ መሰብሰቡንና ገቢ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፲፪. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ተመዝግቦ ከቀረበለት መረጃ በተጨማሪ በልዩ ልዩ የትምህርትና የሥራ ተቋማትና ድርጅቶች ሁሉ የሚገኙትን ካህናት፣ መምህራን፣ ሰባክያንና ምእመናን ከነቤተሰቦቻቸው እየመዘገበ የወረዳውን አኃዛዊ መረጃዎች /ስታትስቲክስ/ ፣ የበጀት ዓመቱን የሥራ ክንውን እና የፋይናንስ ሪፖርት ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት በወቅቱ ያቀርባል፡

፲፫. የወረዳውን የባንክ ሒሳብ ከወረዳው ሒሳብ ሹም ጋር ያንቀሳቅሳል፡፡

## ምዕራፍ ፮
## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት የሥራ ክፍሎች ሥልጣንና ተግባር
## አንቀጽ ፴፫
## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አደረጃጀት

### ፩. አመሠራረት፡-

ሀ) በሀገረ ስብከት ሥር የሚገኙት በወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የተመረጡ ከካህናት አንድ፣ ከምእ መናን አንድ፣ ከሰንበት ት/ቤት ወጣቶች አንድ፣ ከወረዳው ቤተ ክህ ነት ሥራ አስኪያጅ ጋር አራት አራት ልኡካን እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና ዋና ጸሐፊ ጀምሮ የክፍል ኀላፊዎች በአንድነት ለቀ

ጳጳሱ ሰብሳቢ የሆነበት የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ይመሠርታሉ፡፡

ለ) በዚህ አኳኋን የተመሠረተው የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንደ አስፈላጊነቱ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚሰበሰብ አንድ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡

ሐ) ይህ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣኑንና ተግባሩን የሚያስፈጽምለት በየሦስት ወር አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ የአስተዳደር ጉባኤ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣል፡፡

## ፪. አደረጃጀት፡-

## በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሥር፡-

ሀ) የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሰብሳቢ የሆነበት አንድ የሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፤

ለ) የሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እና የሀገረ ስብከቱ ቤተ ክህነት አስተዳደደር ጉባኤ፤

ሐ) የሀገረ ስብከቱ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት (የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት)፤

መ) በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፩ተራ ቍጥር ፬ የተደነገጉትና በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፲፮ በተራ ቍጥር ፩ በአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተዋቀሩት የሥራ ክፍሎች የሀገረ ስብከቱ ቤተ ክህነት የሥራ ክፍሎች ናቸው፡፡ የሥራ ዝርዝራቸውም በቃለ ዐዋዲው ከአንቀጽ ፲፯ እስከ ፴ የተዘረዘረው የሀገረ ስብከቱን ሁኔታ እያገናዘበና እንዲስማማ እያደረገ ለሀገረ ስብከቱ እንዲያገለግል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፴፱
## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ
## ጉባኤ አባላት

፩. የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ........................................................ የጉባኤው ርእሰ መንበር

፪. ሊቀ ጳጳሱ በሌለበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ...................... የጉባኤው ሰብሳቢ

፫. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ዋና ጸሐፊና የክፍል ኀላፊዎች......................... የጉባኤው አባላት

፬. የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጆች .............................. የጉባኤው አባላት

፭. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ወረዳ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የተወከሉ ካህናት .......................................የጉባኤው አባላት

፮. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ወረዳ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የተወከሉ ምእመናን ..................................... የጉባኤው አባላት

፯. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ወረዳ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤ ያት የተወከሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ............................................. የጉባኤው አባላት

፰. ሊቀ ጳጳሱ የጉባኤው ርእሰ መንበር በሚሆንበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ........................................................የጉባኤው አባልና ጸሐፊ

፱. የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሰብሳቢ በሚሆንበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ ..................................የጉባኤው አባልና ጸሐፊ

## አንቀጽ ፵

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፪ በተደነገገውና በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፫ እና ፮ የተመለከተውን ዐላማና ተግባር እየፈጸመና እያስ ፈጸመ በተጨማሪ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. ከቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው የሚወጣውን ሕግና የቃለ ዐዋዲውን መሠ ረታዊ ሐሳብ ሳይለቅ ለሀገረ ስብከቱ መንፈሳዊ ጉባኤ የተዘጋጀውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፣ የሥራ መመሪያ እና ከአስተዳደር ጉባኤ የሚቀርቡለትን ልዩ ልዩ የሥራ ዕቅዶች አይቶ ከውሳኔ ሐሳብ ጋር ለሊቀ ጳጳሱ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፪. በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተዘጋጅቶ የቀረበውን የየአጥቢያውንና የየወረዳውን በጠቅላላው የሀገረ ስብከቱን ያለፈውን የሥራ ክንውን የወደፊቱን የሥራ ዕቅድ የሰበካውን ካህናትና ምእመናን ሁኔታ የገንዘብና ንብረት መግለጫ እየመረመረ በየእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፫. የቤተ ክርስቲያንን የሥራ እንቅስቃሴ ለማጠናከር የመንፈሳዊ ት/ ቤቶችን፣ ሰባክያነ ወንጌልን፣ የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትን፣ የልማት

ሥራዎችን፣ የበጎ አድራጎትና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በሀገረ ስብከቱ ውስጥ እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

፴. በሀገረ ስብከት ደረጃ ለሚከናወኑት የሥራ ዕቅዶችና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት ይወስናል፡፡ መሰብሰቡንና በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፡፡

፴፩. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደርና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚከፈለውን ፳% (ሃያ ከመቶ) ገንዘብ በወቅቱ ገቢ መሆኑን ይቈጣጠራል፡፡

፴፪. በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፷፩ ለተመለከቱት የአስተዳደር ጉባኤ አባላት የሚስማሙትን ከአራት የማያንሱ ከስምንት የማይበልጡ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን ተወካይ በድምፅ ብልጫ ይመርጣል፡፡

፴፫. የሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ይሆናል፡፡.

## አንቀጽ ፷፩

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

፩. የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ------------------------የጉባኤው ሰብሳቢ

፪. በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፫ እና ፬ ከተመለከቱት የካህናት እና

የምእመናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፷ ዓመት ያልበለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን /ምእመን/ -------------------------- የጉባኤው ምክትል ሰብሳቢ

፫. ቍጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በሀገረ ስብከቱ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ የተመረጡ ካህናት ———————————የጉባኤው አባላት

፬. ከአንድ የወጣት ተወካይ ጋር ቍጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ የተመረጡ ምእመናን --------------------------የጉባኤው አባላት

፭. የሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ ----------------------------------የጉባኤው አባልና ጸሐፊ

## አንቀጽ ፵፪

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፫ እና ፲ የተገለጸውን ዐላማና ተግባር እየፈጸመና በትክክል መፈጸሙን እየተቈጣጠረ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

፩. በቅዱስ ሲኖዶስ የወጣውን ሕግ፣ ደንብና መመሪያ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚተላለፈውን ውሳኔና በመንበረ ጵጵስና ጠቅላላ የሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ የሚሰጠውን መመሪያ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል::

፪. ስለ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት፣ ስለ ስብከተ ወንጌል፣ ስለ ልማትና በጎ አድራጎት በጠቅላላው የሀገረ ስብከቱን ሀብትና አገልግሎት ለማስ ፋፋት ዕቅድ እያወጣና ከየወረዳው የተላኩትን የሥራ ዕቅዶች እያጠና ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲ ውል ያደርጋል።

፫. በሀገረ ስብከቱ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የተፈቀዱትን ዕቅዶች አፈጻጸም ይከታተላል።

፬. ለዕቅዶች የተፈቀደውን ገንዘብ በደንቡ መሠረት ወጭ ሆኖ ለታቀደለት ሥራ መዋሉን ይቈጣጠራል።

፭. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ከተሰበሰበው ፳ ከመቶ እና ከማና ቸውም የሀገረ ስብከቱ ገቢ ላይ ከዚህ በታች በተዘረዘው መሠረት ለእያንዳንዱ እንደ ድርሻው እንዲከፈል ያደርጋል።

ሀ) ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ..........፴፭%

ለ) ለሀገረ ስብከቱ........................................................................፴%

ሐ) በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙት የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች..........፴%

መ) በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙ የአብነት ትምህርት ቤቶች ማስፋፊያ.....፭%

፮. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ከሰበሰበው ፳% /ሃያ ከመቶ/ እና ከማናቸውም ሀገረ ስብከቱ ገቢ ላይ፦

ሀ/ ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ፷፭ % (ስድሳ አምስት ከመቶ)

ለ/ ለሀገረ ስብከቱ ፴፫% (ሠላሣ አምስት ከመቶ) እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

፯. የሀገረ ስብከቱን የልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማስፋፋት አግ ባብ ካላቸው ድርጅቶችና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር የበጎ አድራ ጊና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፰. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) አጥንቶ ከአስተያየት ጋር ለመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡ በሀገረ ስብከቱ ሰበካ መንፈሳዊ አስተ ዳደር ጉባኤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ለጠየቀው ክፍል ያስተላልፋል፡፡

፱. ማንኛውም የገንዘብ ክፍያ በወቅቱ መሰብሰቡን፣ በደንቡ መሠረት በትክክል መያዙንና መጠበቁን ያረጋግጣል፡፡

፲. የሰበካውን አስተዳደር፣ የገንዘብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ይከታ ተላል፤ በየጊዜውም ገንዘቡንም ሆነ ንብረቱን በሒሳብ ተቈጣጣሪ ያስመ ረምራል፡፡

፲፩. በሀገረ ስብከቱ በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ሁሉ የሰው ኀይላቸውን፣ የሥራ ክንውናቸውን፣ የወደፊት ዕቅዳ ቸውን፣ የንብረት ይዞታቸውን፣ የገንዘብ ገቢያቸውንና ወጪያቸውን በመግለጽ ሪፖርታቸውን አሟልተው በወቅቱ እንዲያቀርቡ በየጊዜው ክትትል ያደርጋል፡፡

፲፪. ለጠቅላላው ጉባኤ ስብሰባ የመነጋገሪያ አርእስት እና የሥራ መርሐ ግብር በቅድሚያ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

፲፫. የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እንደ አስፈላጊነቱ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲጠራ ለጠቅላላ ጉባኤው ርእሰ መንበር (ሊቀ ጳጳስ) ያሳስባል፡፡

፲፬. ከአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት መካከል በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መን ፈሳዊ ጉባኤ ስብሰባ የሚገኙ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሌላ በሀገረ ስብከቱ ሥር ካሉ አድባራትና ገዳማት የሚመረጡ አንድ ካህን፣ አንድ ምእመን፣ አንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣት ፣የሀገረ ስብከቱ የስብከተ ወንጌልና የሰበካ ጉባኤ ክፍል ኀላፊዎች በድምሩ አምስት ሰዎችን መርጦ ይልካል፡፡

፲፭. ከመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት መካከል ለመንበረ ፓትርያርክ አጠ ቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በመመረጣቸውና በሌላም ምክንያት የመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ሰብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ብዛት ከአምስት ያነሰ እንደሆነ የመተካቱ ሥርዓት በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ ፫ በአንቀጽ ፲፩ በተራ ቁጥር ፬ በተገለጸው መሠረት ይፈጽማል፡፡

፲፮. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት የአገልግሎት ዘመን በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ ፫ በአንቀጽ ፲፩ በተራ ቍጥር ፪ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

፲፯. የሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተጠሪነቱ ለመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፵፫

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፶፩ ተራ ቍጥር ፮ በተደነገገው መሠረት የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

፩. በሀገረ ስብከቱ ክልል ውስጥ ለሚገኙት ገዳማት፣ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት፣በየደረጃው ለተቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትና ለወረዳ ቤተ ክህነት የሥራ አመራር ከፍተኛ የአስተዳደር ኀላፊነት ያለው መሥሪያ ቤት ነው፡፡

፪. በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፶፩ ተራ ቍጥር ፪ ድንጋጌ መሠረት እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በሊቀ ጳጳስ ወይም በጳጳስ ወይም በኤጲስ ቆጶስ ይመራል ፡፡

፫. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፶፪ የተደነገ ገውንና የቃለ ዐዋዲውን ዐላማና ተግባር ከበላይ የሚተላለፈውን ሕግ፣ ደንብና መመሪያ የሚፈጽምበትና የሚያስፈጽምበት አንድ አስተ ዳደር ጉባኤና በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፶፩ ተራ ቍጥር ፬ የተደ ነገገውንና በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፲፮ ተራ ቍጥር ፩ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ የሥራ ዝርዝራቸውም እንደ የአህጉረ ስብከቱ ሁኔታ እየታየ ከአንቀጽ ፲፮ እስከ አንቀጽ ፴ ድረስ የተገለጸው ይሆናል፡፡

፬. አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በቃለ ዐዋዲ ድንጋጌና ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያ ወጣው ልዩ ደንብና መመሪያ ይተዳደራል፡፡

## አንቀጽ ፺፩

## የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሥልጣንና ተግባር

በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፴፯ እና ፵፫ የተደነገገውና የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩. ሊቀ ጳጳሱ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡ የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና ጠቅላላ የቤተ ክህነት አስተዳደር መሪ እና የበላይ ኀላፊ የጠቅላላው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ርእሰ መንበር ነው፡፡

፪. በሀገረ ስብከቱ ለምትገኘው ለጠቅላላዋ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አባት በመሆኑ ለሰበካ ጉባኤያት መሪዎች በየጊዜው መንፈሳዊ ምክር፣ መመያሪና ቡራኬ ይሰጣል፤ ያበረታታል፡፡ ለካህናት፣ ለምእመናን ለሰንበት ት/ቤት ሕፃናትና ወጣቶች ትምህርት ይሰጣል፤ ያጽናናል፡፡

፫. አንዲት ቅድስት ከሁሉ በላይና ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲ ያናችን ጥንታዊነቷና ታሪካዊነቷ በሰላም ተጠብቆ እንዲኖር እና ተከ ታዮቿ ምእመናን በባዕድ ሃይማኖት አስፋፊዎች እንዳይሰረቁ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

፬. በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፮ እና ፯፣ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፫ ተራ ቍጥር ፬ በተደነገገው መሠረትና በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፳ ተራ ቍጥር ፰ እና ፱ የተመለከተውን መስፈርት አሟልተው ለቀረ ቡት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በትምህርት ክፍሉ፣ በአቡነ ቀሲሱና ሀገረ ስብከቱ በሚመድባቸው ሌሎች ካህናት አማካይነት በቃልና በጽ ሑፍ ፈተና እየተጣራ ፈተናውን ላለፉት ብቻ የዲቁናና የቅስና ማዕርግ ይሰጣል፡፡ ማዕርጉን ለተቀበሉትም ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

፫. ከሚያገለግሉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሸኛ ደብዳቤ ላልያዙና በቂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለሌላቸው ክህነት አይሰጥም።

፬. በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ እያስጠና፣ እየወሰነና እያስወሰነ ለሀገረ ስብከቱ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች እንዲቋቋሙና ኀላፊዎችም እንዲመደቡ ያደርጋል። አፈጻጸሙንም ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ያሳውቃል።

፮. በሀገረ ስብከቱ ክልል ውስጥ አዳዲስ ለሚተከሉት አብያተ ክርስ ቲያናት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ የመሠረት ድንጋይ ያኖራል፣ ቅዳሴ ቤቱን ይባርካል፤ ያከብራል።

፯. በሀገረ ስብከቱ ሥር ለሚገኙ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ልዩ ልዩ ሠራተኞች መመሪያ ያስተላልፋል። ጥፋት ሲፈጸምም የማስ ተካከያ እርማት ይሰጣል። ከባድ ጥፋቶችንም በሀገረ ስብከቱ አስተ ዳደር ጉባኤ እያየ ይወስናል።

፱. በሀገረ ስብከቱ ክልል ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የሚቀ ርበውን የሕግና ሥነ ሥርዓት ጉዳይ ከሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ጋር ያያል። ይግባኝ የሚጠየቅበትንም ጉዳይ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲተላለፍ ያደርጋል።

፲. በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፫ ተራ ቍጥር ፱ ላይ በተደነገገው መሠ ረት የሀገረ ስብከቱን የባንክ ሒሳብ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር ያንቀሳቅሳል።

፲፩. ሊቀ ጳጳሱ የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ ነው።

## አንቀጽ ፵፫

## የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

፩. ሥራ አስኪያጁ የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና የቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚና በሀገረ ስብከት ደረጃ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ ነው።

፪. ሊቀ ጳጳሱ በሌለበት ጊዜ ሥራ አስኪያጁ የሀገረ ስብከቱን (የቤተ ክህነቱን) አስተዳደር ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል።

፫. ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣው መመሪያ ከመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና በሀገረ ስብከት ደረጃ የጠቅላላው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔዎች ለወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶችና ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያት በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

፬. በየጊዜው ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚከፈለውን ገንዘብ ተቈጣጥሮ በወቅቱ ገቢ እንዲሆንና በአንቀጽ ፵፪ ተራ ቍጥር ፫ በተደነገገው መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል።

፭. ማንኛውም ወጪ ለሀገረ ስብከቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት መሆኑን፤ የሒሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቁ በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፳፫ እስከ ፳፯ በተደነገገው መሠረት መፈጸሙን ይቈጣጠራል።

፮. ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አግልግሎት የሚውሉትን የገቢና የወጪ ካርኒዎች፣ ሞዴሎችንና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች እትሞችን በመንበረ ፓትያርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት የበላይ ተቈጣጣሪነትና በመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኀላፊነት አሳትሞ በወረዳው አማካ

ይነት ለአጥቢያ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ያከፋፍላል፡፡ በትክክል መድረሱንም ይከታተላል፡፡

፯. ሥራ አስኪያጁ ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ ሳይቀበልና በሀገረ ስብከቱ አስተ ዳደር ጉባኤ ሳይወሰን ሠራተኛ መቅጠር፣ እድገት መስጠት፣ ዝውውር ማድረግ፣ ደመወዝ መጨመር፣ ከሥራ ማሰናበትና የመሳሰሉትን ሁሉ መፈጸም አይችልም፡፡

፰. በሀገረ ስብከቱ ሥር ለሚገኙ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ልዩ ልዩ ሠራተኞች የሥራ መመሪያ ያስተላልፋል፤ ይመክራል፡፡ ጥፋት ሲፈጸምም ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ እንደየጥፋቱ መጠን የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

፱. ከየወረዳው ቤተ ክህነት ተመዝግቦ ከቀረበለት መረጃ በተጨማሪ በልዩ ልዩ የትምህርት፣ የሥራ ተቋማት እና በመሳሰሉት ድርጅቶች ሁሉ የሚገኙትን ካህናት፣ መምህራን፣ ሰባክያን እና ምእመናንን ከነቤተሰቦቻቸው እንዲመዘገቡ በማድረግ የሀገረ ስብከቱን አኃዛዊ መረጃዎች /ስታትስቲክስ/ የበጀት ዓመቱን የሥራ ክንውን እና የፋይናንስ ሪፖርት ለመንበረ ጵጵስናው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በወቅቱ ያቀርባል፡፡

፲. የሀገረ ስብከቱን የባንክ ሒሳብ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጋር ያንቀሳቅሳል፡፤

፲፩. በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፵፬ ተራ ቍጥር ፲ በተደነገገው መሠረት የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ነው፡፡

## ምዕራፍ ፫

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ

## አንቀጽ ፵፯

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አደረጃጀት

### ፩. አመሠራረት፡-

ሀ/ በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች፣ ከየመንበረ ጵጵስናው ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ተመርጠው የተወከሉ የካህናት፣ የምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በመንበረ ፓትርያርኩ ውስጥ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያና የድርጅት ኀላፊዎች በአንድነት ተሰብስበው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ይመሠርታሉ፡፡

ለ/ በዚህ አኳኋን የተመሠረተው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ አንድ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባ ይሆናል፡፡

ሐ/ ይኸው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣኑንና ተግባሩን የሚያስፈጽምለት እንደየአስፈላጊነቱ የሚሰበሰብ የአስተዳደር ጉባኤ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣል፡፡

### ፪. አደረጃጀት፡-

ሀ/ ፓትርያርኩ ርእሰ መንበር የሆነበት አንድ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባ)፤

ለ/ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሰብሳቢ የሆነበት አንድ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እና የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ፤

ሐ/ የአጠቃላይ ሰበካ አስተዳደር ጽ/ቤት (የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት)፤

መ/ የአጠቃላይ ሰበካ አስተዳደር የሥራ ክፍሎች የጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎችና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ናቸው፡፡

## አንቀጽ ፵፯

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰባካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት

፩. ፓትርያርኩ -------------------------------የጉባኤው ርእሰ መንበር

፪. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ---------------------የጉባኤው ም/ሰብሳቢ

፫. በየሀገረ ስብከቱና በቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የተመደቡት ሊቃነ ጳጳሳት ———————— የጉባኤው አባላት

፬. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ --------------------- የጉባኤው አባልና ጸሐፊ

፭. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ)------------------------የጉባኤው አባላት

፮. የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የየመምሪያው፣ የኮሚሽንና የድርጅት ኀላፊዎች ------------- የጉባኤው አባላት

፯. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች --------------- የጉባኤው አባላት፣

፰. ከየመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከቱ መንፈሳውያን የአስተዳደር ጉባኤያት ተመርጠው የተወከሉ ካህናት --------------------የጉባኤው አባላት

፱. ከየመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳውያን የአስተዳደር ጉባኤያት ተመርጠው የተወከሉ ምእመናን ------------------------------------ የጉባኤው አባላት

፲. ከየመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳውያን አስተዳደር ጉባኤያት ተመርጠው የተወከሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ---------------------------- የጉባኤው አባላት

፲፩. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት የስብከተ ወንጌልና የሰበካ ጉባኤ ክፍል ኀላፊዎች .................................. የጉባኤው አባላት፣

፲፪. በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች —————————————————— የጉባኤው አባላት፣

## አንቀጽ ፵፰

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፫ እና ፯ የተዘረዘሩትን ዐላማና ተግባር እየፈ ጸመና እያስፈጸመ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀጥሎ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. የየአህጉረ ስብከቱን መግለጫዎች እንዲሁም የወደፊት ዕቅዶች ከሰማ በኋላ በቅድሚያ በተዘጋጀው የመነጋገሪያ ርእስ (አጀንዳ) መሠረት አንድ በአንድ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ የውሳኔ ሀሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፡፡

፱. በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በኩል ተጣርተው የሚቀርቡትን የየሀገረ ስብከት ከፍተኛ የሰበካ አስተ ዳደር ጉዳዮችን እየመረመረ አስፈላጊውንና ተገቢውን ይፈጽማል፡፡

፲. የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማጠናከር የአብ ነት ት/ቤቶች፣ ከፍተኛ የመንፈሳዊ ት/ቤቶች ፣ የካህናት፣ የሰባክያንና የሰንበት ት/ቤት መምህራን ማሠልጠኛዎች፣ የልማትና በጎ አድራጎት ተቋማት፣ በሀገረ ስብከቱና በማእከል ደረጃ እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

፬. በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፵፱ የተዘረዘሩትን ከአራት ያላነሱ ከስምንት ያልበለጡ የአጠቃላዩን አስተዳደር ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (ሥራ አስፈ ጻሚ ኮሚቴ) አባላት ይመርጣል፡፡

፭. የተመረጡት አባላት የአገልግሎት ዘመን በቃለ ዐዋዲው በምዕራፍ ፲ በአንቀጽ ፲፩ በተራ ቍጥር ፱ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

፮. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡

## <u>አንቀጽ ፵፱</u>

## <u>የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት</u>

፩. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ------------------ የጉባኤው ሰብሳቢ

፪. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ የጉባኤው---------------

አንደኛ ም/ሰብሳቢ

፫. በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፬ እና ፭ ከተመለከቱት የካህናትና የምእመናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፷ ዓመት ያልበለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይም ምእመን-------------------------------የጉባኤው ሁለተኛ ም/ሰብሳቢ

፬. ቍጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በአጠቃላይ ጉባኤው ተመርጠው የተወከሉ ካህናት ------------------------የጉባኤው አባላት

፭. ከአንድ የወጣት ተወካይ ጋር ቍጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በአጠቃላይ ጉባኤው ተመርጠው የተወከሉ ምእመናን ------------------------------------ የጉባኤው አባላት

፮. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኀላፊ -------------------------የጉባኤው አባል

፯. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ዋና ጸሐፊ ---------------------- የጉባኤው ጸሐፊ

## አንቀጽ ፵

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፭ እና ፮ የተዘረዘሩትን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዐላማና ተግባር እየፈጸመና በሥራ መተርጐሙን እየተቈጣጠረ በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣውን ደንብ፣ መመሪያና በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚተላለፈውን ውሳኔና መግለጫ ለየአህጉረ ስብከቱና ለሚመለከታቸው ሁሉ በወቅቱ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

፪. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚሠሩት ከፍተኛ ዕቅዶችና ለልዩ ልዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የተወሰነውን ገንዘብ በደንቡ መሠረት በትክክል መያዙንና መጠበቁን ይከታተላል፡፡

፫. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደርና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚከፈ ለውን ገንዘብ ተቈጣጥሮ በየጊዜው ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፬. የአጠቃላዩ ሰበካ አስተዳደር ገንዘብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ በቃለ ዐዋዲው ከአንቀጽ ፳፫ እስከ ፳፯ በተደነገገው መሠረት መከናወኑን ይከታተላል በሒሳብ አጣሪም ያስመረምራል፡፡

፭. የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የመተዳደሪያ ደንብና የሥራ መመሪያ እንደ ዚሁም ሊሻሻል የሚገባውን የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ሕግጋትና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች እያጠና ለአጠቃላዩ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፮. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚከናወኑት የቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ተግባራት ማለት ለስብከተ ወንጌል፣ ለመንፈሳዊ ትምህርት፣ ለልማት፣ ለበጎ አድ ራጎት፣ ለሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ሀብትና አገልግሎት መስፋፋት ዕቅድ እያወጣና መርሐ ግብር እያዘጋጀ ለአጠቃላዩ ጉባኤ አቅርቦ ሲፈቀ ድለት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲. ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ስብሰባ አጠቃላይ ሪፖርት፣ የመነጋገሪያ አርእስት (አጀንዳ) እና መርሐ ግብር ያዘጋጃል።

፲፩. የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ወይም ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለመንበረ ፓትርያርኩ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይሆናል።

፲፪. በየዓመቱ ጥቅምት ወር የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲካሄድ ያደርጋል።

## አንቀጽ ፵፩

## የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

**በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፩ መሠረት፡-**

፩. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለሚገኙት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና አህጉረ ስብከት ፣ለገዳማትና አድባራት እንዲሁም በየደረጃው ለተቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ሁሉ የአስተዳደር ማእከልና ርእስ፣ ለቤተ ክህነት ሥራ አመራርና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ የበላይ ኀላፊና ባለሙሉ ሥልጣን መሥሪያ ቤት ነው።

፪. የቅዱስ ሲኖዶስ ሕግና ደንብ፣ የቋሚ ሲኖዶስ ውሳኔና መመሪያ እንዲሁም የቃለ ዐዋዲው ድንጋጌ ሁሉ ተግባራዊ የሚሆነው በጽ/ቤቱና በሥሩ በሚገኙት መምሪያዎችና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች አማካይነት ነው።

፫. ከየአህጉረ ስብከቱ የሚቀርቡትን የአስተዳደርና የፍትሕ መንፈሳዊ ጉዳዮችን እየተቀበለ የሚወስን የአስተዳደር ጉባኤ አለው።

## አንቀጽ ፵፪
## የፓትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር

ፓትርያርኩ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፴፪ የተደነገገውና የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

፩. ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለምትገኘዋ መላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አባትና የበላይ ጠባቂ፣ ለአንድነትዋና ለአስተዳደርዋ ከፍተኛ ኃላፊና ባለሙሉ ሥልጣን በመሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በርእሰ መንበርነት ይመራል፡፡

፪. ፓትርያርኩ የሁሉም መንፈሳዊ አባትና መሪ እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው ለሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት መሪዎች፣ ለካህናትና ለምእመናን መመሪያ፣ ትምህርትና ቡራኬ ይሰጣል፡፡

፫. በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የሚቀርቡት ጉዳዮች በጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም በቋሚ ሲኖዶስ ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲታዩና ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፬. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልሱና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ዐበይት ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለመላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት (ሊቃነ ጳጳሳት)፤ አስፈላጊም ከሆነ ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት አስቸኳይ ጥሪ የማድረግ ሙብትና ኃላፊነት አለው፡፡

፰. ከጥንት ጀምሮ ያለው የአኃት ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግንኙነት በበለጠ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፵፫

## የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፪ ንኡስ ቍጥር ፫ እና አንቀጽ ፵፩ የተደነገገውና የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

፩. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለቅዱስ ፓትርያርክ ሆኖ ለመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥራ አመራር የገንዘብና ንብረት አስተዳደር የበላይ ኀላፊ በጠቅላላው የቤተ ክህነት ዋና ባለሥልጣን ነው፡፡

፪. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በም/ሰብሳቢነት፤ የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤን በዋና ሰብሳቢነት ይመራል፡፡

፫. የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የቆመለትን ዐላማና ተግባር ለመፈጸምና ልዩ ልዩ የክፍል ሥራዎችንም ለማሟላት ለጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎችና ድርጅቶች የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤ እያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ ኀላፊም የተመደበበትን የሥራ ድርሻ በትክክል እያከናወነ መሆኑን ይከታተላል ይቈጣጠራል፡፡

፬. በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የሚቀርቡትን ጉዳዮች በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ እንዲታዩና እንዲ

ወሰኑ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ጉባኤ ሥልጣን በላይ የሆነውን ጉዳይ ለቋሚ ሲኖዶስ ወይም ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፡፡

፭. በየጊዜው ከየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ለጠቅላላው አገልግሎት ጉዳይ ተብሎ የሚከፈለው ገንዘብ ተጠቃልሎ መሰብሰቡንና በትክክለኛው ቦታ በወቅቱ ገቢ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፮. ማንኛውም ዓይነት ወጪ በሚደረግበት ጊዜ ለመንበረ ፓትርያርኩ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በተፈቀደው በጀት መሠረት መሆኑንና የሒሳቡ አያያዝና የንብረቱ አጠባበቅ በቃለ ዐዋዲ አንቀጽ ፳፭፣ ፳፮፣፳፯ እና ፵፮ በተዘረዘረው መሠረት መፈጸሙን ይቈጣጠራል፡፡

፯. በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፬ ቍጥር ፲ በተደነገገው መሠረት በበጀት የተመደበውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብና ንብረት ከቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡ በየዓመቱና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜም በሕጋዊ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

፰. የየአህጉረ ስብከቱን የባንክ ሒሳብ ለሚያንቀሳቅሱ ተወካዮች የውክልና ደብዳቤ ለሚመለከተው ባንክ ይጽፋል፡፡

፱. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚገኙ አህጉረ ስብከትና አብያተ ክርስቲያናት የሥራ ሂደታቸውን ይከታተላል፤ ይቈጣጠራል፡፡

፲. የየዓመቱን የሥራ ፍሬና የወደፊቱንም ዕቅድ የሚያስረዳ ሪፖርት በየዓመቱ በጥቅምት ወር ለሚደረገው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያቀርባል፤ አጠቃላይ ጉባኤው የመከረበትና ያሳለፈው የውሳኔ ሐሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ሲጸድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፩. የየመምሪያዎቹ፣የድርጅቶችና የልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች የሥራ ኀላፊ ዎችን የሥራ ዝውውር እድገት በተመለከተ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት ተጠንቶና ቅዱስ ፓትርያርኩ ሲስማሙበት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፪. አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ቅዱስ ፓትርያርኩን እያማከረ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

## አንቀጽ ፶

## ስለ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ

ም/ሥራ አስኪያጅ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፫ የተደነገገውና የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

፩. ም/ሥራ አስኪያጁ

ሀ/ ከጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ተለይተው በመመሪያ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል

ለ/ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ጊዜ ተከቶት ይሠራል፡፡

፪. ም/ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ፰

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ ፶፩

**የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የአመራር ሥነ ሥርዓትና ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ**

፩. የሰበካ መንፈሳዊያን ጉባኤያት የአመራር ሥነ ሥርዓት

በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የአመራር ሥነ ሥርዓት ቀጥሎ እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

ሀ/ በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከአባሎቹ ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ጉባኤው እንደተሟላ ተቈጥሮ ሥራውን ሊቀጥል ይችላል፡፡

ለ/ ለጉባኤው የቀረቡት ጉዳዮች የሚወሰኑት በዕለቱ በተገኙት አባሎች ድምፅ ብልጫ ሲሆን ድምፁ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳ ቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

ሐ/ በእያንዳንዱ ስብሰባ ላይ የተወሰነው ጉዳይ በቃለ ጉባኤ ተዘጋጅቶ በዕለቱ ስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት ብቻ በሙሉ ይፈርሙበታል፡፡

መ/ የሰበካውን መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔ የመፈጸምና የማስፈጸም ኀላፊነት የጉባኤው ሰብሳቢ ነው፡፡

## ፪. ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ

በቃለ ዐዋዲ በምዕራፍ ፫ በአንቀጽ ፲ በተራ ቍጥር ፩ በፊደል (ለ) እና (ሐ)፣ በምዕራፍ ፰ አንቀጽ ፴፩ በተራ ቍጥር ፩፣ በአንቀጽ ፴፲ ተራ ቍጥር ፪ ከተገለጸው መደበኛ የስብሰባ ጊዜ በተጨማሪ በየደረጃው የሚገኙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አስቸኳይ ጉዳይ ሲገጥማቸውና አስፈላጊ የሆነ ምክንያት ሲኖራቸው ወይም ከጉባኤው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት ስብሰባ እንዲደረግ ሲጠይቁ በየሰብሳቢዎቻቸው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ፵፫

## ስለ ሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ገቢ

በቅዱሳት መጻሕፍት (በኦሪት ዘሌ ፳፯÷፴-፴፬፤ በኦሪት ዘዳ ፲፬÷፳፪-፳፱፤ በኦሪት ዘኊ ፲፰÷፳፩-፳፰፤ ነህ ፲÷፴፪-፴፱፤ትን.ሚል ፫÷፯-፲፫፤ ማቴ ፳፪÷፳፩፤ የሐዋ ሥራ ፬÷፴፪-፴፯፤ ፩ኛ ቆሮ ፲፮÷፩-፪) በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፫ ተራ ቍጥር ፲፩ እንደተደነገገው ማንኛውም ምእመን ከሚያገኘው ከማናቸውም ሀብቱና ንብረቱ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎትና ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት በጠቅላላው ለመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚውል ዐሥራት፣ በኵራት፣ ቀዳ ምያት መክፈል ክርስቲያናዊ ግዴታው ነው::

ከሰበካው ካህናትና ምእመናንም ሆነ ከሌሎች ልዩ ልዩ ቦታዎች የሚ ገኘው የቤተ ክርስቲያን የገቢ ዓይነት ቀጥሎ የተመለከተው ነው::

፩. የወርና የዓመት ክፍያ፣

ሀ/ ማንኛውም ክርስቲያን ከሚያገኘው ገቢ ላይ አስቦ ዐሥራት (ከዐሥር አንድ) መክፈል በቅዱስ መጽሐፍ የታዘዘ ግዴታ ነው::

ለ/ ገቢ ያለው ካህንም ሆነ ምእመን ለሚገለገልበት አጥቢያ ቤተ ክርስ ቲያን የሰበካ ጉባኤ የአባልነት ክፍያ በየወሩ ብር ፳ (ሃያ) ይከፍላል:: ሆኖም ግን የአከባቢውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በአስተዳደር ጉባኤ እየወሰነ ከ፳ (ከሃያ) ብር በላይ ሊያስከፍል ይችላል::

ሐ/ በጎ ፈቃድ ያለው ከላይ ከተጠቀሰው የበለጠ ክፍያ ሊያደርግ ይችላል::

መ/ ጥሬ ገንዘብ መክፈል ያልቻለ በዓይነት ከምርቱና ከሀብቱ የመክፈል ክርስቲያናዊ ግዴታ አለበት፡፡

ሠ/ በዚሁ ተራ ቍጥር ከፊደል ሀ እስከ መ የተመለከተውን ክፍያ መክፈል የማይችል ቢኖር ሁኔታው በሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተጠንቶ ሊከፍል በሚችለው መጠን ይወሰ ንለታል፡፡ ፈጽሞ ለመክፈል የማይችል ከሆነም በነጻ መንፈሳዊ አገል ግሎት ይፈጸምለታል፡፡

ረ/ በጕልበትና በዕውቀት ሥራ መርዳት የሚችል ሆኖ ሲገኝ እንደች ሎታው ለቤተ ክርስቲያን ተገቢውን አገልግሎት ማበርከት ይችላል፡፡

፪. <u>ከሰበካውና ከሌሎች ምእመናን የሚገኘው የገንዘብ ገቢ፣</u>

ሀ/ ስእለት

ለ/ ሙዳየ ምጽዋት

ሐ/ ስጦታ /መባእ/

መ/ የወርና የዓመት በዓል ገቢ

ሠ/ የቅርጻ ቅርጽና የተግባረ እድ ሽያጭ

ረ/ በጠበል አገልግሎት በሙዳየ ምጽዋት የሚገኝ ገቢና ከቤተ ክርስ ቲያን ጕብኝዎች

ሰ/ ከሰንበት ት/ቤት፣ ከስብከተ ወንጌል እና ከልዩ ልዩ ክፍሎች መንፈ ሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች

ሸ/ ከልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች

ቀ/ በዚህ የገቢ አርእስት ውስጥ ያልተጠቀሰ ማናቸውም ዓይነት ገቢና ሌላም ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር የሚገኝ ገንዘብና ንብረት ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፩ እና ፪ በዝርዝር የተገለጸው ገንዘብና ንብረት ተጠቃልሎ በቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ቤት የገንዘብ ወጪ የሚደረገው በተፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል /በጀት/ መሠረት የሰበካው ሰብሳቢ በጽሑፍ ሲያዝ ብቻ ነው፡፡

፬. ማናቸውም ዓይነት የሰበካው ገንዘብና ንብረት ገቢ ለቍጥጥር እንዲያመች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የበላይ ተቈጣጣሪነትና በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኀላፊነት ታትሞ በሚወጣው በአንድ ዓይነት ሕጋዊ ደረሰኝ /ካርኒ/ ብቻ ይሰበሰባል፡፡

፭. ይህን ቃለ ዐዋዲ በመተላለፍ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሳያውቀውና ሳይፈቅድ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም ሌላ የገቢ ካርኒ አሳትሞ የሚሠራ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ወይም ግለሰብ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ሲሠራባቸው የተገኙ ካርኒዎችም ዋጋ እንደሌላቸው ተቈጥሮ እንዳይሠራባቸው ይታሸጋሉ፡፡ በተያዙት ካርኒዎች የተሰበሰበው ገንዘብም በሕጋዊ ደረሰኝ ለቤተ ክርስቲያኑ ገቢ ይሆናል፡፡

፮. በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚገኘው ገንዘብ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ስም፣ ከወረዳ እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚገኘው ገንዘብ፣ በየደረጃው በተቋ

ቋመው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ስም የባንክ ሒሳብ ተከፍቶለት ይቀመጣል፤ እንደየ አስፈላጊነቱ በውሳኔም በበጀት ዓመቱ በተያዘው ዕቅድ መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፡፡

## አንቀጽ ፶፯
## ስለ ሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ወጪ

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የገንዘብ ወጪ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

፩. አጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ከካህናትና ምእመናን ክፍያ፣ ከስእለት፣ ከሙዳየ ምጽዋት፣ ከልማት ሥራዎችና ከማንኛውም ገቢ ላይ ፳% (ሃያ ከመቶ) ለሀገረ ስብከት ይከፍላል፡፡ ሀገረ ስብከቱም በዚህ ቃለ ዐዋዲ አንቀጽ ፵፪ ተራ ቍጥር ፫ መሠረት ክፍያውን ይፈጽማል

፪. ከበላይ አካል በተፈቀደ በጀት ድልድል መሠረት፡-

ሀ/ ለደመወዝ

ለ/ ለሥራ ማስኬጃ

ሐ/ በዕቅድ ለተያዙ ልዩ ልዩ ሥራዎች ወጪ ያደርጋል፡፡

፫. ከቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም በየደረጃው ከሚገኘው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገንዘብ ቤት የገንዘብ ወጪ የሚደረገው በተፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል /በጀት/ መሠረት የአጥቢያ ሰበካው አስተዳደሪ /ሰብሳቢ/ በጽሑፍ ሲያዝ ብቻ ነው፡፡

፬. በማንኛውም ደረጃ የሚገኘው የሰበካ አስተዳደር የበጀት ዓመት ሐምሌ ፩ ቀን ተጀምሮ ሰኔ ፴ ቀን ይዘጋል፡፡

፭. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በየደረጃው የተጠናቀረው የንብረት አያያዝና አጠባበቅ የገንዘብ ገቢና ወጪ ሒሳብና የሥራ ክንውን ሪፖርት እስከ ሐምሌ ፴ ቀን ድረስ መንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት መድረስ አለበት። ሀገረ ስብከት ጽ/ቤትም የበኩሉን አጥንቶና አጣርቶ ዓመታዊ ሪፖርት እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል።

፮. በየደረጃው የተቋቋሙት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያት ከተፈቀደላቸው በጀት ውጭ የገንዘብ ወጪ ማድረግ አይችሉም

፯. የእያንዳንዱ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገቢ የአንዱ ዓመት ከፍ፣ የአንዱ ዓመት ገቢ ዝቅ ሊል ስለሚችል ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃና ለቤተ ክርስቲያን ማደሻ ታጥቶ ችግር እንዳይደርስ አስቀድሞ ጥንቃቄ በማ ድረግ ማንኛውም የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት አዲስ የበጀት ድል ድል በሚያደርግበት ወቅት በበጀት ከሚደለደለው ሒሳብ ላይ ለመጠ ባበቂያ በበጀት ዓመቱ ከተሰበሰበው ገቢ ላይ ፳፭% /ሃያ አምስት ከመቶ/ በባንክ ማስቀመጥ አለበት። ይህም ሒሳብ የሚንቀሳቀሰው ተጠንቶ ሲቀርብ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ ይሆናል።

## አንቀጽ ፶፫
## የንብረትና ታሪካዊ ቅርሶች አመዘጋገብና አያያዝ

፩. በቤተ ክርስቲያን ስም የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳትና ጥንታውያን ቅርሶች አመዘጋገብ በቤተ ክርስቲያኒቱ ቋንቋ የግእዝ ፊደልና አኃዝ እንዲ ሁም የተለመደው የመለያ ቍጥር (ኮድ) እየተሰጣቸው በቋሚ ባሕር መዝገብ ተመዝግበው በጥንቃቄ ይቀመጣሉ።

፪. በገዳማት፣ አድባራትና ገጠር አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት ጥንታ ውያን ቅርሶች በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግር ምክንያት ጉዳት የሚደ ርስባቸው መሆኑ ሲታመንበትና ለጥንቃቄ ሲባል ከቦታ ወደ ቦታ ለማዛወር ቢያስፈልግ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሰብሳቢነት በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ሲወሰን በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ትእዛዝ እንዲንቀሳቀሱ ካልተደረገ በስተቀር ካሉበት ታሪካዊ ቦታ በምንም ዓይነት መንቀሳቀስ የለባቸውም ፡፡

፫. የአንዱን ቤተ ክርስቲያን ቅርስ ወይም ንብረት ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ያዛወረ ወይም የሰወረ ወይም የሰረቀና ያሰረቀ ወይም የሸጠና የለወጠ ግለሰብ ወይም ድርጅት በፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ ነው፡፡ አድራጎቱን የፈጸመው ሰው ካህን ከሆነ ከሥልጣነ ክህነቱና ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ከጥቅሙ ሁሉ ታግዶ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ወይም በሀገረ ስብከት ጽ/ቤት አማካይነት ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ አስፈ ላጊው ቅጣት ይወሰንበታል፡፡

፬. ለቅርሶች ደኅንነት ሲባል በበላይ አካል ታውቆና ተፈቅዶ ካልሆነ በቀር ቅርሶችን በካሜራ፣ በማይክሮ ፊልም እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ማንሣት የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ ፶፱
## ስለሚሾሙ፣ ስለሚቀጠሩና በበጎ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያገለግሉ

### ፩. የደብር አስተዳዳሪ መመዘኛ

አንድ ካህን የደብር አስተዳዳሪ ሆኖ ለመሾም የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት

፩. ክህነት ያለው እና ዕድሜው ከ፴ ዓመት በላይ የሆነው

፪. ቀድሶ ማስተማር የሚችል ቢቻል የሐዲሳት፣ የብሉያትና የሊቃውንት መጻሕፍት የትርጓሜ ትምህርት ከሦስቱ አንዱን የተማረ ወይም ከመንፈሳዊ ኮሌጆች በዲፕሎማ ወይም ከዚያ በላይ የተመረቀ

፫. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቅን አገልግሎት የሰጠ

፬. በሥነ ምግባሩ እና በአርኣያ ክህነቱ የተመሰከረለት

፭. የአስተዳደር ሥራ ልምድ ያለው

፮. ቢቻል በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ የሚናገር

፪. <u>የወረዳ ሊቀ ካህናት /ሥራ አስኪያጅ/ መመዘኛዎች</u>

አንድ ካህን የወረዳ ሊቀ ካህናት /ሥራ አስኪያጅ/ ሆኖ ለመሾም የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት

፩. ዕድሜው ከ፴፫ ዓመት በላይ ሆኖ ክህነት ያለው

፪. በደብር አስተዳዳሪነት ወይም በሀገረ ስብከት በኀላፊነት ቢያንስ ለ፭ ዓመታት ያገለገለ

፫. ቅኔ ያወቀና ቀድሶ ማስተማር የሚችል

፬. ቢቻል የሐዲሳት፣ የብሉያትና የሊቃውንት መጻሕፍት የትርጓሜ ትምህርት ከሦስቱ አንዱን የተማረ ወይም ከመንፈሳዊ ኮሌጆች በዲፕሎማ ወይም ከዚያ በላይ የተመረቀ

፭. በሥነ ምግባሩ እና በአርኣያ ክህነቱ የተመሰከረለት

፮. የአስተዳደር ሥራ ልምድ ያለው

፯. ቢቻል በወረዳው የሚነገረውን ቋንቋ የሚናገር

## ፫. የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መመዘኛ

አንድ ካህን የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ለመሾም በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፫ ተራ ቍጥር ፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት

፩. ዕድሜው ከ፴፫ ዓመት በላይ ሆኖ ክህነት ያለው

፪. በደብር አስተዳዳሪነት ወይም በወረዳ ሊቀ ካህናትነት ወይም በሀገረ ስብከት ወይም በጠቅላይ ቤተ ክህነት በኀላፊነት የሠራ

፫. ቅኔ ያወቀና ቀድሶ ማስተማር የሚችል

፬. ከታወቁ የትርጓሜ ት/ቤቶች በአንዱ የተመረቀ ወይም ከመንፈሳዊያን ኮሌጆች በአንዱ የተመረቀ

፭. በሥነ ምግባሩ እና በአርአያ ክህነቱ የተመሰከረለት

፮. የአስተዳደር ሥራ ልምድ ያለው

፯. ቢቻል በሀገረ ስብከቱ የሚነገረውን ቋንቋ የሚናገር

## ፬. የገዳማት የአድባራት እና የውስጥ አገልጋዮች ሹመት

በሙያቸው ብቁ የሆኑ ከትዕቢት፣ ከተንኮል፣ ከአድማ፣ ከስካርና ከልዩ ልዩ አስነዋሪ ነገሮች የራቁ፣ በመልካም ሥነ ምግባራቸውና በመንፈሳዊነ ታቸው የተመሰከረላቸው ከካህናት መካከል እየተመረጡ፤

ሀ/ በቅዱስ ፓትርያርኩ የሚሾሙ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች፣

አበምኔቶችና እመምኔቶች በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቅራቢነት በቅዱስ ፓትርያርኩ ይሾማሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ግን ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሆናል፡፡

ለ/ የሌሎች ገዳማት፣ አድባራት እና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አስተዳ ዳሪዎች በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሾማሉ፡፡ በገዳም የገዳሙ ማኅበር መርጦ እና ምርጫው በቃለ ጉባኤ ተደግፎ ሲቀርብ፤ ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት በየሰበካው ካህናትና ምእመናን ተመርጠው እና በወረዳው ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በአስተዳደር ጉባኤ ተወስኖ ሲቀርብ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሾማሉ፡፡

ሐ/ በደብር አስተዳዳሪነት የሚሾም ካህን በደብሩ የማዕርግ ሥም ይጠራል፡፡

፫. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት በመቍነን የሚተዳደሩ የወንድ ወይም የሴት ገዳማት መነኮሳት ወይም መነኮሳይያት በሥርዓተ ገዳሙ መሠረት አበ ምኔታቸውን ወይም እመምኔታቸውን መርጠው ሲያቀርቡ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ያጸድቃል፡፡

፬. ሀ/ ሊቀ ጠበብት፣ ቄሰ ገበዝ፣ ቀኝ ጌታ፣ ግራ ጌታ፣ ርእሰ ደብር፣ አጋፋሪና ሊቀ ዲያቆናት በመባል የሚሰጡት የቤተ ክርስቲያን ማዕርጋተ ሢመት ሙያቸውና ሥነ ምግባራቸው በካህናት ጉባኤ እየተጠና የሚመረጡት ካህናት በበላይ አካል ሲፈቀድ በአስተ ዳዳሪው ይሾማሉ፡፡

ለ/ የማዕርግ ስም ማግኘት የሚገባቸው ካህናት የአገልግሎት ዘመና ቸው፣ ሞያቸውና ሥነ ምግባራቸው በሰበካ ጉባኤ ታይቶና ተወስኖ

ለሀገረ ስብከቱ ሲቀርብና ትክክለኛነቱ ሲረጋገጥ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሾማሉ።

ሐ/ ከምእመናን መካከል ለቤተ ክርስቲያን ቅን አገልግሎት የሰጡ ለመሆናቸው በአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ተወስኖ ሲቀርብ እና በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ሲረጋገጥ በሊቀ ጳጳሱ ይሾማሉ።

መ/ የቤተ ክርስቲያን፣ የካህናትና የምእመናን የማዕርግ ስም ከቅዱስ ፓትርያርኩ እና ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ውጪ በሌላ አካል ሊሰጥ አይችልም።

፯. የወረዳ ቤተ ክህነት ከሀገረ ስብከት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የጠባይና የሥራ ችሎታ (የሙያ) መመዘኛ ሥራውንና ቦታውን በመጥቀስ በይፋ ማስታወቂያ አውጥቶ በማወዳደር መምህራንን፣ ሰባክያንን፣ ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ መዘምራንና ልዩ ልዩ ሠራተኞችን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጥር የሚችለው በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ታምኖበት በሊቀ ጳጳሱ ሲፈቀድ ብቻ ነው።

፰. በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ደንብ መሠረት በሀገረ ስብከቱ በኩል በፈተና ተወዳድረው የሚያልፉት ብቻ ከሚላኩላቸው በስተቀር በአጥቢያው አስተዳዳሪ ወይም በሰበካ ጉባኤ ሥልጣን ማንኛውም ቅጥር ሊፈጸም አይችልም።

፱. ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ ወረዳ ቤተ ክህነት የሚመደቡት ሠራተኞች የቅጥር ሁኔታ በማእከል ደረጃ በጠቅላይ ቤተ ክህነት እንደ ሥራው አስፈላጊነት እየተጠና ይፈጸማል።

፲. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በካህናትና በምእመናን ኅብረት የተመ ሠረተ እንደመሆኑ መጠን ደመወዝ ከሚያገኙትና በቋሚነት ከተመ ደቡት ካህናት ውጭ የሌሎችን ዕውቀትና ጉልበት መጨመር (ማግኘት) እንዲቻል፤

ሀ/ ከቤተ ክርስቲያን መደበኛ አገልግሎት ውጭ በግል፣ በተለያዩ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች በሥራ ላይ የሚገኙ ካህናት በበ ላይ አካል ሲፈቀድ በትርፍ ጊዜያቸው እንደየሙያቸውና እንደ ምርጫቸው በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አማካይነት በሰበካው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ ተመድበው የነጻ አገልግሎት ማበርከት ይችላሉ።

ለ/ ምእመናን ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያንን በማይመለከቱ በማንኛ ቸውም የሥራ መስኮችና ቤተ ክርስቲያን በምታስማራቸው የአገል ግሎት ድርሻ በነጻ ፈቃዳቸውና በትርፍ ጊዜያቸው የሚገባቸ ውንና የሚፈለግባቸውን አገልግሎት ማበርከት ክርስቲያናዊ መብታቸውና ግዴታቸው ነው።

## <u>አንቀጽ ፳</u>
## <u>የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች መብትና ግዴታ</u>

በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፲፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ሠራተኞች የሚከተሉት መብቶችና ግዴታ ዎች ይኖሯቸዋል።

፮. መብት፡-

ሀ/ በሰበካው አስተዳደር ውስጥ የሚያገለግሉት ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች እንደየሥራቸውና እንደየሙያቸው በሚሰጡት አገል ግሎት መጠን ደመወዝ ማግኘት ሕጋዊ መብታቸው ነው፡፡

ለ/ በወር ደመወዝ ሲከፈላቸው ቆይቶ የጡረታ ክፍያቸውን ላሟሉ አገል ጋይ ካህናትና ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ከቤተ ክርስቲ ያኒቱ የጡረታ አበል የማግኘት መብት አላቸው ፡፡

ሐ/ ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህንና ሠራተኛ ሕግ በሚፈ ቅደው መሠረት የዓመት ፈቃድና የሕመም ፈቃድ ለሴት ሠራተኛም የወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብት የተጠበቀ ነው፡፡

መ/ ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህንና ሠራተኛ በሙያ፣ በአገልግሎት፣ በሥራ ጥራት፣ በታማኝነትና በሚያበረክተው የሥራ ውጤት ብቁ ሆኖ ሲገኝ የደረጃና የደመወዝ እድገት የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

ሠ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ድረስ በደመ ወዝ ተቀጥሮ የሚያገለግል ሁሉ በዕድሜ ጸጋ ከሥራው በጡረታ የሚገለለው የዕድሜው ገደብ ፷ ዓመት (ስድሳ ዓመት) ሲመ ላው ነው፡፡ ነገር ግን ለሥራው ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ በቅርብ ኀላፊው አስተያየት በጡረታ ኮሚቴ ተጣርቶ ለአስተዳደር ጉባኤ ቀርቦ ሲታመ ንበትና በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሲፈቀድ በኮንትራት ሊቀጠር ይችላል፡፡

ሐ/ የአጥቢያው ነዋሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ሕጋዊ መታወቂያ ያላቸው፡፡

መ) በአጥቢያው የአባልነት ግዴታቸውን የፈጸሙ፣

ሠ) ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በላይ የሆኑ ካህናት፣ የጾታ ልዩነት ሳይኖር ምእመናንና ምእመናት ብቻ ናቸው፡፡

፬. የአጥቢያውን የምርጫ ሥነ ሥርዓት የሚያስፈጽም ከአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የተውጣጡ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት ከአምስት ያላነሱ ከሰባት ያልበለጡ አባላት ያሉበት አስመራጭ ኮሚቴ መርጦ ይሠይማል፡፡ አስመራጭ ኮሚቴ ውም ምርጫውን በዕለቱ ያስፈጽማል፡፡ የኮሚቴው አባላትም በዚህ አንቀጽ በተራ ቍጥር ፫ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ፣ በመንፈሳዊነታቸው፣ በግብረ ገብነታቸውና በአስተዋይነታቸው የታ ወቁ፣ በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ፣ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ይሆናሉ፡፡

፭. በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፲፩ ተራ ቍጥር ፬ መሠረት አዲስ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ምርጫ ከመካሄዱ ከአንድ ወር በፊት የቆየው የሰ በካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በሥራ ዘመኑ የፈጸማቸውንና ያስፈጸማቸውን፣ በዕቅድ የተያዙ ሥራዎችን እና አጠቃላይ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃውን ጠብቆ ለሀገረ ስብከቱ ከቀረበ በኋላ ዕቅዱና ሪፖርቱ ታይቶ ሲፈቀድ ለአጥቢያው እንዲቀርብ ይሆናል፡፡

፮. በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱትን የሰበካ መንፈሳዊ አስተ ዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላትን በዕለቱ በዕጩነት ከቀረቡት መካከል በድምፅ ብልጫ ይመርጣል፡፡

ረ/ የኮንትራት ቅጥር ከዚህ በላይ ከተደነገገው ውጭ ሲፈጸም ሕጋዊነት አይኖረውም፡፡

ሰ/ በሕዝባዊም ሆነ በመንግሥታዊ ድርጅቶች ሲያገለግሉ ቆይተው የጡረታ መብታቸው የተጠበቀላቸው ግለሰቦች ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ባሉት የሥራ መስኮች ለማገልገል በፈለጉ ጊዜ በነጻ ከሚሠሩ በስተቀር ደመወዝ አይከፈላቸውም፡፡ ሆኖም ልዩ ሙያ የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ በኮንትራት ተቀጥረው እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡

ሸ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ባሉት መሥሪያ ቤቶች ተቀጥሮ ሲያገለግል የኖረው ሠራተኛ በሥራው ላይ እንዳለ ወይም የጡረታ መብቱ ተከብሮለት ከተገለለ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የጡረታ መብቱ ሕግ ለሚፈቅድላቸው ቤተሰቦቹ ይተላለፋል፡፡

ቀ/ ሠራተኛው የጡረታ መብቱ የሚጠበቅለት በቋሚ ሠራተኛነት የጡረታ መዋጮውን እየከፈለ ከዐሥር ዓመት በላይ ያገለገለ ሲሆን ነው፡፡ የአገልግሎት ዘመኑ ከዐሥር ዓመት በታች ከሆነ ግን የሚያገኘው የወር ደመወዝ በአገልግሎት ዘመኑ ልክ ታስቦ አንድ ጊዜ ብቻ ይከፈለዋል፡፡

በ/ ሠራተኞች ከአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም ከአንድ መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት በሥራ ተዛውረው ጡረታ በሚወጡበት ጊዜ ለጡረታው አበል አከፋፈል እንዲያመች ከየደመወዛቸው ያዋጡት ፬% (አራት ከመቶ) የጡረታ

ሒሳብ እና አሠሪው መሥሪያ ቤት በስማቸው ያስቀመጠው ፮% (ስድ ስት ከመቶ) ታስቦ ጡረታ ወደ ወጡበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም መሥሪያ ቤቱ በማእከል ደረጃ ወደሚያቋቁመው ድርጅት ይዛወርላቸዋል::

ተ/ ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በየደረጃው በሚ ገኙት ት/ቤቶች የሚያስተምሩ የትርጓሜ መጻሕፍት፣ የቅኔ (የግእዝ)፣ የጸዋትወ ዜማ፣ የአቋቋምና የቅዳሴ መምህራን ጉባኤ ዘርግተው በማስ ተማር ላይ ከሆኑ የመሥራት ኀይላቸው ሳይደክም በዕድሜ ገደብ ብቻ በጡረታ እንዳይገለሉ የሥራ መብታቸው የተጠበቀ ነው::

## ፪. ግዴታ

ሀ/ ካህናትና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሠራተኞች ለተቀጠሩበት ሥራ በሙሉ ኀይልና ችሎታ መሥራት ይኖርባቸዋል::

ለ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ያሉት ማንኛ ውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ሠራተኞች ከደመወዛቸው ፬% (አራት ከመቶ) የጡረታ መዋጮ ይከፍላሉ::

ሐ/ እያንዳንዱ ካህን የንስሓ ልጆቹን የማስተማርና በሰበካ ጉባኤ የማስመዝገብ፣ የተወሰነውን ክፍያ በወቅቱ እንዲከፍሉ የማትጋትና የማስተባበር ኀላፊነት አለበት ::

መ/ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ምእመናንና ምእመናት ከጥምቀት እስከ ጸሎተ ፍትሐት ድረስ አስፈላጊውን መን ፈሳዊ አገልግሎት መስጠት የካህናት ግዴታና ኀላፊነት ይሆናል::

ሠ/እያንዳንዱ ካህን ወይም ሠራተኛ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ጠብቆ የማስጠበቅ፣ ቤተ ክርስቲያንን ከሚያስነቅፍ የነውር ሥራ ሁሉ መራቅ ግዴታው ነው::

ረ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ የሚገኙት ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ ወረዳ ቤተ ክህነት ወደ ሌላ ወረዳ ቤተ ክህነት፤ ከአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተዛውረው የመሥራት ግዴታ አለባቸው ::

ሰ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ የሚገኙት ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች የተመደቡበትን ሥራ በትክክል የማከናወን፣ሥራውን በሚመለከት ጉዳይ ለበላይ የመታዘዝና መመሪያ የመቀበል፣ ግብረ ገብነትንና ቅን አገልግሎትን የማሳየት፣ ሥራውንና የሥራ ሰዓትን የማክበር ግዴታ አለባቸው::

ሸ/ በሕመም ወይም በዕክል ምክንያት ካልሆነ በቀር ካህን ሥራ ፈትቶ መቀመጥ የለበትም::

ከእግዚአብሔር በተቀበለው ጸጋ እያንዳንዱ ካህን እንደ ስጦታው ማገ ልግል ይኖርበታል::

ይልቁንም ምእመናንና ወጣቶችን ከባዕድ ሃይማኖት የመጠበቅና የማስተማር ኀላፊነትና ግዴታ አለበት::

ቀ/ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ዲያቆናት በዲቁና ማዕርጋቸው ሊቀድሱ

(ሊያገለግሉ) የሚችሉት ከዐሥራ አምስት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ነው፡፡ ዕድሜቸው ከሃያ አምስት ዓመት በላይ ከሆነ በጋብቻ ሕግ በመወሰን ወይም በድንግልና ለመኖር ቢፈቅዱ ጉዳም ጉብተው በሥርዓተ ምንኵስና ጸንተው አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ፷፩
## የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መብትና ግዴታ

በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፲፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምእመናን የሚከተሉት መብቶችና ግዴታዎች ይኖሯቸዋል፡፡

፩. መብት፡-

ሀ/ በሰበካው ውስጥ ነዋሪ የሆነ በአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ በአባልነት ታውቆ የተመዘገበና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ያሟላ፣ መታወቂያ የተሰጠው ምእ መን ከቤተ ክርስቲያን ለምእመናን የሚገባውን ፣መንፈሳዊ አገልግሎት ማግኘት መብቱ ነው፡፡

ለ/ ከነበረበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባውን የአባልነት ክፍያ የከፈለ ምእመን ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ቢዛወርና መንፈሳዊ አገልግሎት ማግኘት ቢፈልግ ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቅም፡፡

ሐ/ እንግዳ ደራሽና ባይተዋር ቢሞት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባልነቱ በመታወቂያ ካርድ ወይም ኦርቶዶክሳዊነቱን የሚገልጽ ማተብ በአንገቱ ቢገኝ ወይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ መሆኑ በምስክር ከተረጋገጠ የዕለት ጸሎተ ፍትሐት በነጻ ይደረግለታል፡፡

መ/ ማንኛውም ምእመን በሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦ ወርኃዊና ዓመታዊ ክፍያ የከፈለ እና እሱ ካስመዘገባቸው ቤተሰቦች መካከል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ያለ ምንም ክፍያ የዕለት ጸሎተ ፍትሐት ይፈጸምላቸዋል፡፡ ሥርዓተ ቀብራቸውም ይፈጸማል፡፡

ሠ/ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦና ተገቢውን ክፍያ ሲከፍል ቆይቶ በቂ ባልሆነ ምክንያት ክፍያውን ለሁለት ዓመት ያቋረጠ ምእመን ውዝፉን ብቻ በመክፈል፣ ሳይከፍል የቆየው ከሁለት ዓመት በላይ ከሆነ ከዋናው ክፍያ በተጨማሪ ተገቢውን መቀጫ ከፍሎ ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

ሰ/ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገበና ተገቢውን ወርኃዊና ዓመታዊ ክፍያ ያልከፈለ ምእመንም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆኑ በንስሓ አባቱ ተረጋግጦ የአገልግሎት ዋጋ ከፍለው ጸሎተ ፍትሐት እንዲደርስለት የሚችሉ ቤተሰቦች የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

ሸ/ ማንኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ በአለበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት ከተደረገለት በኋላ የመቃብር ቦታ ማግኘት መብቱ ነው፡፡

__፪. ግዴታ፡-__

ሀ/ የአጥቢያው ሰበካ ምእመናን በገንዘብ ክፍያ በአስተዳደር፣ በትምህርት፣ በልማትና በማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት በጠቅላላው በሀብት፣ በዕውቀትና በጉልበት በመርዳት በሰበካው ልዩ ልዩ የክፍል ሥራዎች

ውስጥ በመሳተፍ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ክርስቲያናዊ ግዴታቸው ነው፡፡

ለ/ ማንኛውም በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የሚኖርና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆነ ምእመን በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መመዝገብ፣ በዚህ ደንብ የተወሰነውን ወርኃዊ እና ዓመታዊ ክፍያ መክፈል፣ የአባልነቱን መታወቂያ መያዝ እንዲሁም ቤተሰቡንና ልጆቹን በዝርዝር ማስመዝገብና አካለ መጠን ለደረሱትም በየራሳቸው የአባልነት መታወቂያ እንዲይዙ ማድረግ፣ በሰንበት ት/ቤት የሃይማኖት ትምህርት እንዲከታተሉና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

ሐ/ ማንኛውም ምእመን ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚተላለፍ ፣ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ነቅፎ የሚያስነቅፍ፣ ክብረ ቤተ ክርስቲያንን ደፍሮ የሚያ ስደፍር መሆን የለበትም፣ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና በቅዱሳት መጻ ሕፍት ትምህርት መመራትና በተወሰነለት የምእመንነት ደረጃ ጸንቶ መኖር ግዴታው ነው፡፡

መ/ አንድ ምእመን ከሚኖርበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ምክ ንያት ወደ ሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲዛወር ቀድሞ ከነበረበት ሰበካ ጉባኤ የተቀበለውን የአባልነት መታወቂያ ካስረከበ በኋላ የመሸኛ ደብ ዳቤ መቀበልና ለተዛወረበት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በወቅቱ አቅርቦ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ አንድ ምእመን በሰበካው ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባ ላትን የመምረጥ መብት እንዳለው ሁሉ የመመረጥና የማገልገል ግዴ ታም አለበት፡፡

፪/ እያንዳንዱ ምእመን ሥልጣነ ክህነት ካላቸው ቀሳውስት መካከል አንዱን መርጦ በንስሐ አባትነት መያዝ መንፈሳዊ ግዴታው ነው፡፡

## አንቀጽ ፷፱

## የአገልጋይ ካህናትን ብዛት ስለመወሰን

በገዳማት፣ በአድባራትና በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በማገባር የሚያገ ለግሉት ካህናት እና ልዩ ልዩ ሠራተኞች ብዛት እንደ ቤተ ክርስቲያኑ የአገልግሎት ስፋትና የገቢ መጠን በሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ፣ በወረዳው ቤተ ክህነትና በሀገረ ስብከቱ ደረጃ በደረጃ እየተጠና ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ፸

## ይህን ቃለ ዐዋዲና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በሚተላለፍ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ

፩. ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን ወይም ሠራተኛ በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፰ ተራ ቊጥር ፪ የተደነገገውን ተላልፎ ቢገኝ እንደጥፋቱ ሁኔታ በመጀመሪያ ምክርና ተግሣጽ፣በሁለተኛ ማስጠ ንቀቂያ ይሰጠዋል፤ በሦስተኛ ጊዜ ቅጣት ይወስንበታል፤ ቅጣቱም እንደ ጥፋቱ ክብደት ተመዛዝኖ በገንዘብ ወይም በቀኖና፣ ከሥራ በማዛወር፣ ከሥራ በማገድ፣ ከሥራ በማሰናበት ወይም ከአባልነት በመለየት ሊወሰን ይችላል። ሆኖም የመጨረሻው ውሳኔ ማለት ከሥራ የማሰናበቱ ወይም ከአባልነት የመለየቱ ቅጣት ሊጸና የሚችለው የወረዳው ቤተ ክህነት ተስማምቶበት ወደ መንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ቀርቦ በሊቀ ጳጳሱ ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

፪. አንድ ካህን ከሥራው እንዲታገድ ወይም እንዲሰናበት ከከህነቱ እንዲ ታገድ የሚሰጠው ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው

ሀ/ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በወረዳ ደረጃ ከሆነ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በአስተዳደር ጉባኤ አይቶ ሲያጸድቀው፤

ለ/ ከሀገረ ስብከቱ ጀምሮ ባሉት የሥራ ዘርፎች የተመደበ ሠራተኛ ከሆነ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ አይቶ ሲያጸድቀው ብቻ ነው፡፡

፫. አንድ ካህን ክህነትን በሚያስይዝ ጥፋት ላይ ቢገኝ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሰብሳቢነት በአስተዳደር ጉባኤ ተወስኖ በሊቀ ጳጳሱ ክህነቱ ሊያዝ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ተራ ቍጥር ፩ መሠረት ምክርና ተግሣጽ እንዲሁም ማስጠ ንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ አንድ ካህን የንስሓ ልጁን በሰበካ ጉባኤ ሳያስ መዝግብ ወርኃዊና ዓመታዊ ክፍያውን እንዲከፍል ሳያደርግ ሌሎችንም መንፈሳዊ ግዴታዎች ሳይፈጽምና ሳያስፈጽም ቆይቶ የንስሓ ልጁ ሲሞት ለፍትሐት ብቻ የሚያቀርብ ከሆነ ፡-

ሀ/ ለመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ

ለ/ ለሁለተኛ የአንድ ወር ግማሽ ደመ ወዙን

ሐ/ ለሦስተኛ ጊዜ ከመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ጋር የአንድ ወር ሙሉ ደመወዙን ይቀጣል

መ/ በመጨረሻም ከሥልጣነ ክህነቱ ይታገዳል፡፡

፭. አንድ ምእመን መፈሳዊ ግዴታውን መወጣት ካልቻለና በቃለ ዐዋዲው አንቀጽ ፷፩ ተራ ቍጥር ፪ የተደነገገውን ተላልፎ ቢገኝ

ሀ/ በመጀመሪያ ጊዜ በንሥሐ አባቱ ወይም ከቤተ ክርስቲያኑ
በተወከለ አባት አማካይነት ምክርና ትምህርት

ለ/ በሁለተኛ ጊዜ ተግሣጽና ቀኖና ይሰጠዋል

ሐ/ በሦስተኛ ጊዜ ከማስጠንቀቂያ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ከአባልነቱ እንዲታገድ ይሆናል።

፮. አንድ ምእመን ከአባልነት እዲሠረዝ የሚተላለፈው ውሳኔ ሊጸና የሚችለው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በልዩ ጉባኤ አይቶ ሲያጸድቀው ብቻ ይሆናል።

## አንቀጽ ፰፬

## የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት

፩. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ቢኖር ጉዳዩ ደረጃ ውን ጠብቆ ለወረዳው ቤተ ክህነት በይግባኝ ሊቀርብ ይችላል።

፪. በወረዳው ቤተ ክህነት የተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካስከተለ የሀገረ ስብ ከቱ ሊቀ ጳጳስ በተገኘበት በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ታይቶ ይወሰናል።

፫. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ ወረዳ ያሉት የሰበካ ጉባኤ አባላት ተመርጠው ሥራ ከጀመሩ በኋላ ገንዘብ ቢያጠፉ ወይም ሌላ ችግር ቢፈጥሩ የመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት አስተዳደር ጉባኤ በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት ተመልክቶ የመሻር ሥልጣን አለው።

፬. በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት የተመረጡት የሰበካ መንፈሳዊ አስተ ዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት የአሠራር በደል ወይም

ጥፋት ፈጽመው ቢገኙ በጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ታይቶ ሲወሰን በምትካቸው ሌሎች አባላት ይተካሉ፡፡

፫. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የሒሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ በማእከላዊ አሠራር በጠቅላይ ቤተ ክህነት እየተዘጋጁ በሚወጡት ሞዴሎች ካርኒዎችና መዝገቦች የመሥራት ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህ ውጭ በሌላ ሞዴልና ካርኒ ሲሠሩ የተገኙ በሕግ ይጠየቃሉ፡፡

፬. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ፣ የአገልጋዮቿን ካህናት ኑሮ ለማሻሻልና ለልጆቿ ምእመናን የሚሰጠውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማሟላት የወጣውን ይህን የቃለ ዐዋዲ ደንብና ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሥራ ላይ እንዳይውል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቃወሙ ካህናት ከክህነታቸው፤ ምእመናን ከአባልነታቸው ይሠረዛሉ፡፡

፭. ከአሁን በፊት ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም የወጣው ቃለ ዐዋዲ፣ ታኅሣሥ ፲ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም የወጣው የቃለ ዐዋዲ ማሻሻያ፣ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም የወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ውስጥ ደንብና ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፺፩ ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣው ቃለ ዐዋዲ በየጊዜው የተላለፉት መመሪያዎች ሁሉ በዚህ ቃለ ዐዋዲ ተሻሽለዋል፡፡

## አንቀጽ ፷፫

## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ቃለ ዐዋዲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት፣ ትውፊት መሠረት አድርገው በየትኛውም የዓለም ክፍል በተቋቋሙና በሚቋቋሙ አህጉረ ስብከት፣ ወረዳ ቤተ ክህነት፣ ገዳማት፣ አድባ

ራት፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙት የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋዮችና ሠራተኞች፣ ምእመናንና ምእመናት እንዲ ሁም በቤተ ክርስቲያኗ ሥር ልማትና እድገት ለማፋጠን በተቋቋሙና በሚቋቋሙ መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተቋማት ላይ ተፈጻ ሚነት ይኖረዋል።


ይህ ቃለ ዐዋዲ በማእከል ደረጃ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተተርጉሞም በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ አህጉረ ስብከት የቃለ ዐዋዲውን ይዘት ሳይለቅ ከየሀገራቱ ሕግ ጋር በማጣጣም በየሀገራቱ ቋንቋ እያስተረጎሙ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋሉ።

## አንቀጽ ፳፮
## የቃለ ዐዋዲው መሻሻል

ይህ ቃለ ዐዋዲ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፹በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ በተደነገገው መሠረት ሊሻሻል ይችላል።

## አንቀጽ ፳፯
## ቃለ ዐዋዲው የሚጸናበት ጊዜ

**ይህ ቃለ ዐዋዲ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ጸድቆ**
**ከወጣበት ከሐምሌ ፳፻፪ ዓ.ም.**
**ጀምሮ የጸና ይሆናል ።**
**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን**
**ቅዱስ ሲኖዶስ**
**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፻፪ ዓ.ም.**




የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መዋቅር

## ስለካህናት ተልእኮና ስለሢመተ ክህነት፤

### የካህናት ተልእኮ

እነሆ እኔ እንደበጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ (ማቴ. ፲.፲፮)::

ወደዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ:: ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል (ማርቆስ. ፲፮.፲፭-፲፮)::

እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃች ኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተ ማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነ ሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴዎስ. ፳፰.፲፱-፳)::

አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም:: እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን (የሐዋርያት ሥራ. ፮.፪-፬)::

እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥ ራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታ ዘዙም:: ኢሳይያስ ጌታ ሆይ ምስክርነታችንን ማን አመነ? ብሎአልና:: እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው (ሮሜ. ፲.፲፬-፲፯)::

ኢየሱስ ስምኦን ጴጥሮስን ትወደኛለህን? አለው:: አዎን ጌታ ሆይ እንድወድህ አንተ ታው ቃለህ አለው:: ግልገሎቼን አሰማራ አለው:: ደግሞ ሁለተኛ ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው:: ሦስ ተኛ ጊዜ በጎቼን አሰማራ አለው (ዮሐንስ ፳፩.፲፭-፲፯)::

በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔር መንጋ ጠብቁ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥ ፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት ለመ ንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማነበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ (፩ኛ ጴጥ. ፭.፪-፬)::

በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ (ግብረ ሐዋርያት ፳ .፳፰)::

### ሢመተ ክህነት

፩/ «አሙን ነገር» :: ነገሩ ደግ ነው:: ዘይፈቅድ ይሡየም ጳጳስ ሠናየ ግብረ ፈተወ / ግብ.ሐዋ. ፳.፳፰/:: ቅስና ሊሾም የወደደ በጎ አደረገ ቢወድ አይደለም በቅቶ ቢገኝ ነው::

፪/ ወባሕቱ ርቱዕ ይሡየም ጳጳስ ዘኢያደሉ ለገጽ (ዘሌዋ. ፳፩.፲፯ ቲቶ. ፩.፮.፯)::

ነገር ግን በፍርድ በብያኔ በጸሎት በትምህርት በምጽዋት ፊት አይቶ የማያደላ ሊሾም ይገባል:: ዘአልቦ ምክንያት:: ምክንያት ኃጢአት የሌለ በት:: ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ:: ያልደገመ (ድንግል አይሾም አላለም):: ብእሲ ንቁህ ከንቃመ ሐኬት የነቃ:: ወጠቢብ ብልህ አስተዋይ:: ወመ ፍቀሬ ነግድ:: እንግዳ ተቀባይ:: ዘአንጽሐ ርእሰ ሰውነቱን ከኃጢአት የለየ:: መመህር ወመገሥጽ የሚመክር የሚያስተምር::

፫/ ዘኢያበዝኅ ስትየ ወይን /ዘሌዋ. ፲፰.፱ ቲቶ. ፩.፯/ መጠጥ የማያበዛ:: ዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ:: ፈጥኖ የማይማታ:: አንድም ፈጥኖ የማይገዝት:: ባቁዕ:: መከሮ አስተምሮ የሚረባ የሚጠቅም:: ዘኢይትገዓዝ በማይረባ በማይ ጠቅም ነገር የማይከራከር:: ዘኢያፈቅር ንዋየ ኃላፊውን ከብት የማይወድ::

፬/ ዘሠናይ ሥርዓተ ቤቱ:: የቤቱ ሥርዓት የተከናወነለት:: ዘቦ ውሉድ ዘይትኤዘዙ በኩሉ ንጽሕ (፩ሳሙ. ፪.፲፪):: በንጽሕና ሆነው የተሠሩ የተቀጡ ልጆች ያሉት::

፭/ ወዘሰ ኢይከል ሠሪዐ ቤቱ እፎኑ ያስተ ሐምም ቤተ እግዚአብሔር ቤተ ሰብኡን ሠርቶ ቀጥቶ ማሳደር የማይቻለው ከሆነ በዓራቱ መዓ ዝን ያሉ ምእመናንን ሠርቶ ቀጥቶ ያሳድራል ብለው እንደ ምን ይሾሙታል?

፮/ ወኢይኩን ዘእምሐዲስ ተከለ:: ከሐዲስ አማኒ ወገን አይሾም:: ከመ ኢይትዓበይ እንዳ ይታበይ ከኔ በላይ ቢያጡ እንጂ ሾሙኝ ብሎ:: ወኢይጸለል:: በድንቁርና እንዳይያዝ:: ወኢይደቅ ውስተ መሥገርተ ሰይጣን:: ሰይጣን በተያዘበት አሽክላ እንዳይያዝ /አለ/ ትዕቢት ነው::

፯/ ወዓዲ ርቱዕ ዘሰብእ አፍአ ይንዕድዎ / ም. ፩.፲/:: ዳግመኛም ከምግባር ከሃይማኖት በአፍአ ያሉ ሰዎች ያመሰገኑት ሊሆን ይገባል:: ከመ ኢይደቅ ውስተ ጽእለት (፩ኛ. ቆሮ. ፩.፲፪. ፲፫):: በስድብ እንዳይወድቅ ማለት ተነቅፎ ምእመናንን እንዳያሰነቅፍ ወመሥገርተ ሰይጣን ሰይጣን ሰውን በሚይዝበት አሽከላ እንዳይያዝ::

## ስለ ዲያቆናት

፰/ ወዲያቆናትኒ ከማሁ ንጹሓን:: ዲያቆ ናቱም ከማሁ እንደቄሱ ንጹሐን ይኹኑ:: ወእስተ ርኩባን:: በአንድ ቦታ የተወሰኑ:: አንድም ሕዋሳ ታቸውን የሰበሰቡ ይኹኑ:: እለ ኢያበዝኅ ስትየ ወይን:: መጠጥ የማያበዙ ይኹኑ እለ ኢያፈቅሩ ረቢሐ ከንቶ (ፊልጵ. ፩.፩፤ ግብሐዋ. ፮.፫):: ኃላፊውን ገንዘብ የማይወዱ ይኹኑ::

፱/ እለ የዐቅቡ ምክረ ሃይማኖቶሙ በልብ ንጹሕ:: ከክህደት ከኑፋቄ ንጹሕ በሆነ ልቡና የሃይማኖታቸውን ትምህርት አጽንተው የያዙ ይኹኑ::

፲/ ወሎሙኒ ይቅድሙ አመክሮቶሙ:: እሊያን ቅሉ አስቀድመው ይፍተኗቸው:: ወእምዝ ይትለአኩ እምከመ ኅሩያን እሙንቱ:: ከዚህ በኋላ በቅተው ቢገኙ ይሾሙ::

## ስለዲያቆናውያት ሴቶች

፲፩/ ወአንስትኒ ከማሁ እለ አንጽሐ ርእሶን (ቲቶ. ፪.፫):: እሁን ወንዶችን ዲያቆናት ንጹሐን ይኹኑ እንዳልሁ ዲያቆናውያት ሴቶችም ሰውነታ ቸውን ከኃጢአት የለዩ ይኹኑ እለ ተምህራ ሥርዓተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተማሩ እለ ኢያስተዳትጻ:: ነገር ሠርተው አንዱን ከአንዱ የማያጣሉ ይኹኑ:: ጠባባት ብልሆች ራትዓት:: ቅኖች ይኹኑ:: ወምእመናት በኩሉ በውሥጥ በአፍአ በሥራው ኹሉ የታመኑ ይኹኑ ወይት ለአካ:: (ይትለአካ) እንዲህ እንዲህ ያሉት ይሾሙ::

## በመልካም ላገለገሉ ዲያቆናት የበለጠ ያድርጉላቸው

፲፪/ ውብእሲኒ ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ የቄሱን ተናግሮ የዲያቆኑን አልተናገረውም ነበርና ዲያቆንም ያልደጋገመ ይሾም (ድንግል አይሾም አላለም):: ዘቦ ወሉድ የተሠሩ የተቀጡ ልጆች ያሉት ዘሠናይ ግዕዘ ቤቱ ቍ. ፪ የቤቱ ሥርዓት የተከናወነለት::

፲፫ / ወአለስ ሠናየ ይትለአኩ አንተ ተዐቢ ሢመተ ይግበሩ ሎሙ (ማቴ. ፳፫.፳፮):: (ሎሙ ለአለ ይትለአኩ በጎ ማገልገልን ላገለገሉ)ዲያቆናት የበለጠ ያድርጉላቸው (አለ) ከዲቁና ወደ ቅስና:: ከቅስና ወደ ኤጲስ ቆጶስነት ያውጧቸው በብዙኀ ሞገስ በሃይማኖተ ኢየሱስ ክርስቶስ (፩ኛ ዮሐ. ፫.፳፭):: በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የሚሾሙት ብዙ መዓርገ ሁብት አለና አንተ ተዐቢ ሢመተ ይግበሩ ሎሙ:: አንድም በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የሚሠሩት ብዙ ምግባር ትሩፋት አለና ይቅድሙ አመክሮቶሙ አምከመ ኀሩያን እሙንቱ:: /የግዕዙ ንባብ ከነትርጓሜው ፩ኛ. ጢሞ. ፫.፩-፲፫/::

## ልዩ ልዩ መንፈሳዊ መልእክትና መመሪያ

፩/ እለ ሠናየ ተልእኩ ቀሲሳን ምክዕቢተ ይደልዎሙ (ሮሜ. ፲፪.፳፫ና፲፫.፳፪):: በጎ ማገልገልን ላገለገሉ ቀሳውስት እጽፍ ድርብ ዋጋ ክብር ይገባቸዋል:: ወፈድፋደሰ ለእለ ይሰርሑ በቃል ወበምህሮ ይልቁንም ቢቃል ቃል ለቃል የሰሙትን ወበምህሮ ከመጽሐፍ ያገኙትን በማስተማር ለሚደከሙ መምህራን እጽፍ ድርብ ክብር ይገባቸዋል::

፪/ወይብል መጽሐፍ ኢትፍጽም አፋሁ ለላህም ሶበ ታከይድ እክለከ (ዘዳግ. ፳፫.፬፣ ፩ኛ ቆሮ. ፱.፱):: እህልህን በምታሄድበት ጊዜ የላምህን አፉን አትሠረው ብሏልና:: ወይደልዎ አስቡ ለዘይትቀነይ ሉቃ. (፲፥፯):: ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና::

፫/ ላዕለ ልሂቅ ኢትስማዕ ውዴተ:: በቄሱ ነገረ ሠሪ አትስማበት:: ዘእንበለ ይዝልፍዎ ክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት (ዮሐ. ፰.፲፯):: ሁለት ሶስት ሰዎች ሳይመሰክሩበት::

፬/ ወለእለሂ ስሕቱ በቅድመ ኩሉ ገሥጾሙ /ኤፌ. ፭.፲፪.፲፫/:: ስሕቱ በቅድመ ኩሉ ገሥጾሙ በቅድመ ኩሉ በጉባኤ የበደሉትንም በጉባኤ ገሥፃቸው:: ከመ ባዕድኒ ይፍራህ:: ሌላው ፈርቶ ይገሠጽ ዘንድ ዝሉፍ እንዘ ይትጌሠጽ አብድ ይከውን ማእምረ፤፤

፭/ አሰምዕ ለከ በቅድመ እግዚአብሔር:: በእግዚአብሔር ፊት አዳኝብሃለሁ:: ከመ ትዕቀብ ዘንተ እንዘ ኢታደሉ:: በፍርድ በብያኔ በጸሎት በትምህርት በምጽዋት ፊት አይተህ ሳታደላ ይህን ትጠብቅ ዘንድ አዳኝብሃለሁ:: ወኢታጽድቆ ለሰብእ ቅድመ ፍትሕ:: ሳይመሰከርበት እንዲያደርግ አውቃለሁ አትበል:: ወኢትግበር ምንተሂ በዘትትሔመይ:: በምትነቀፍ ገንዘብ የምትነቀፍበት ሥራ አትሥራ:: ነገር ሠሪ እንጂ ሰምቶ ቃል ለቃል ተጨዋውቶ ይሉታልና:: ወኢታጽድቆ ለሰብእ ቅድመ ፍትሕ:: /አንድም/ ሳይመሰከርለት እንዳያደርግ አውቃለሁ አትበል:: ወኢትግበር ምንተሂ በዘትትሔመይ:: በምትነቀፍ ገንዘብ የምትነቀፍበትን ሥራ አትሥራ መማለጃ በልቶ ተዘምዶ ሥጋ ኑሮት አድልቶ ይሉታልና::

፮/ ወኢትሢም ፍጡነ ወኢመነሂ /ግብ ሐዋ. ፮-፯/ ማንንም ማን ሳትመረምር ፈጥነህ አትሹም:: ወኢትሳተፍ በዝ ውስተ ኃጢአተ ባዕድ:: በዚህ ሌላው በሠራው ኃጢአት አንተ በፍዳ እንዳትያዝ አኮ ዘገብረ ባሕቲቶ ዘይትኳነን አላ ዘሂ ሠምረ በኃጢአተ ዝኩ እንዲል:: ወአንጽሕ እንከ ርእሰከ:: ሰውነትህን ከኃጢአት ለይ:: /፩ኛ. ጢሞ. ፭.፲፯-፳፪/ የግዕዙ ንባብ ከነትርጓሜው::

## ስለ ምእመናን የገንዘብ አስተዋጽኦ ማብራሪያ

እስመ ፈቀድክሙ ወአቅደምክሙ ትሙጥው

ነፍስከሙ እምቀዳሚ ዓም:: ካምና ጀምሮ ከጥንተ ስብከት ጀምሮ ከብታችሁን /ሀብታችሁን/ ታወጣጡ ዘንድ አስቀድማችሁ ወዳችኋልና::

፩/ ይእዜሰ አሁንስ እንዲያው በምኞት ትቀሩ? ግበሩሂ:: አስተዋጽኦውን አወጣጡ:: እስመ ፈቂድሂ እምፈቲው:: ቁርጽ ሐልዮ፤ ከነቅዕ ሐልዮ የተነሣ ነውና:: ወገቢርሂ እምረኪብ:: መስጠትም ከማግኘት የተነሣ ነውና ግበሩሂ ወፈጽሙሂ::

፪/ ወእምከመሰ ፈቂድ ሀሎ ይትመዘገብ በዘይትከሀሎ:: መስጠቱንስ መውደዱ ካለ:: ወአኮ በአምጣነ ዘኢይትከሀሎ:: /ምሳ. ፫.፳፰ ማር. ፲፪.፵፫/። የሌለውን ገንዘብ ሰጥቶ ያይደለ መስጠቱን በመውደዱ ብቻ ይመሰገናል:: ዘሰ ይፈቅድ ይግበር ወኢይክል ይትዔረዮ ለዘይገብር ወይክል እንዲል /አፈወርቅ/ አንድም የሌለውን ብዙውን ለጥቶ ያይደለ ያለውን ጥቂቱን ሰጥቶ ይመሰገናል::

፫/ ወዘአኮ ከመ ባዕድ ያዕርፍ ኪያከሙ ናጠውቅ:: ነገር ግን በእናንተ ከብት ሌላው ተድላ ደስታ ሊያደርግበት እናንተን የምናስቸግር አይደለንም:: ዳዕሙ ተሀልው ፅሩየ በዝ መዋ ዕል:: በዚህ ወራት አነዋራችሁ አንድ ወገን ይሆን ዘንድ ነው እንጂ እስመ ተረፈ ዚአከሙ ውስተ ንትጋ እልከቱ ይከውን:: የናንተ ተረፍ የነዚያን ጉድለት ይመላልና::

፬/ ወተረፈ ዚአሆሙ ውስተ ንትጋ ዚአ ከሙ ይከውን:: የነዚያም ተረፍ የናንተን ጉድ ለት ይመላልና:: ከመ ይኩን ሀልዎትከሙ ዕሩየ በኩሉ:: /ም. ፱.፲፪/ አነዋራችሁ በሥራው ሁሉ አንድ ወገን ይሆን ዘንድ::

፭ / እስመ ከመዝ ይቤ መጽሐፍ ዘቦ ብዙኀ ኢያትረፈ ብዙ ያለው አልተረፈውም:: ወዘቦ ውኁድ ኢያሕፀፀ /ዘፀአ. ፲፮.፲፰/:: ጥቂትም ያለው አላነሰውም ብሎ መጽሐፍ እንደ ተናገረ /ሐተታ/ ዘቦ ብዙኀ በኦሪቱ አምሳ ጎሞር ያገባ ነው አልተረፈውም አለ አምሳ ሆኖ ይመገ በዋልና ዘቦ ውኁድ አምስት ጎሞር ያገባ ነው አላነሰውም አለ አምስት ሆኖ ይመገበዋልና:: (አንድም) በአዲሱ /ዘቦ ብዙኀ/ ብዙ ብዕለ ሥጋ ያላቸው ምእመናን አሉ እንደመጠኑ ተክል ተክለው ተጉበሮ ይዘው ይኖራሉ፡ አላነሳቸውም አለ አሕዛብ ይጨምሩላቸዋልና:: አንድም /ዘቦ ብዙኀ/ ብዙ ብዕለ ነፍስ ያላቸው ምእመናን አሉ አልተረፋቸውም አለ ለአሕዛብ ይጸልያሉና:: / ዘቦ ውኁድ/ ጥቂት ብዕለ ነፍስ ያላቸው አሕዛብ አሉ አላነሳቸውም አለ ምእመናን ይጸልዩላቸ ዋልና:: /የግዕዙ ንባብ ከነትርጓሜው ፪ኛ.ቆሮ. ፰ .፲-፲፭/::

፮/ ወበእንተ አስተጋብኦሰ ለቅዱሳን /ግብ ሐዋ. ፲፩.፳፱.፪ ቆሮ. ም. ፰ና ፱/:: ለቅዱሳን ስለ ሚሆን ስለአስተዋጽኦው ነገር:: በከመ ሥራዕ ክዎሙ ለቤተ ክርስቲያን ዘገላትያ /ገላት. ፪.፬/:: ለገላትያ ሰዎች እንደጻፍኩላቸው:: እንዳዘዝ ኋቸው ከማሁ አንትሙሂ ግበሩ:: እናንተም አወጣጡ::

፯/ በበእሑድ /ግብ. ሐዋ. ፳፥፯/ :: በበእሑድ/ እሑድ እሑድ /በበውኁድ/ ጥቂት ጥቂት/ በበአሐዱ/ ባያንዳንዱ:: ኵሉ ብእሲ እምኔከሙ ይዝግብ ሎቱ ዘተሰርሐ:: ከናንተ ወገን ሰው ሁሉ የደከመበትን:: አንድም የቀናውን ያወ ጣጣ:: ወዘረከበ በቤቱ ይዕቀብ:: ያወጣጣ ውንም በቤቱ አኑሮ ይጠብቅ:: ከመ ኢይኩን ቅስት አመ መጻእኩ:: በመጣሁ ጊዜ ጾብ ክርክር እንዳይሆን ይህ የኔ ይህ የኔ በማለት::

፰/ ወአመ በጻሕኩ እፌኑ ዘኀረይክሙ ቦቱ ምስለ መልእክትየ:: በመጣሁም ጊዜ ለመረ

ጣችሁት ሰው አስይዤ ከኪታቤ ጋራ እሰድላ ችኋለሁ:: ከመ ይትረከብ ሀብትከሙ በኢየሩ ሳሌም:: ስጦታችሁ በኢየሩሳሌም ይገኝ ዘንድ ከዚያ ቤተ ማኅበር አለና:: አንድም በኢየሩ ሳሌም ሰማያዊት ዋጋ በማሰጠት ይታወቅ ዘንድ:: /፩ኛ. ቆሮ. ፲፯.፩-፫/:: የግዕዙ ንባብ ከነትርጓሜው:

፱/ ወአምዝ አስተዋጽኡ አርድእት መጠነ ይክሉ ወፈነው ለቢጾሙ እለ ይነብሩ ብሔረ ይሁዳ ምስለ በርናባስ ወሳውል ኀበ ኲሎሙ ቀሲሳን::

ከዚህም በኋላ ምእመናን የሚቻላቸውን ያህል ገንዘብ አወጣጥተው በብሔረ ይሁዳ ላሉ ምእመናን ለበርናባስና ለሳውል አስይዘው ከቀሳውስት ዘንድ ላኩ:: /ግብረ ሐዋርያት ፲፩.፳፱/ የግዕዙ ንባብ ከነትርጓሜው::

## የድሀዋ መበለት አስተዋጽኦ

ኢየሱስም በመዝገብ አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በመዝገቡ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንዲጥሉ ያይ ነበር ብዙ ባለ ጠጎችም ብዙ ይጥሉ ነበር አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች:: ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ እውነት እላችኋለሁ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሃ መበለት አብልጣ ጣለች ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና ይህች ግን ከጉድለቷዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አላቸው /ማር. ፲፪.፵፩-፵፬/::

እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳ ልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኅዘን ወይም በግድ አይደለም /፪ኛ. ቆሮ. ፱.፯/::

## ለታመመው በጌታ ስም ይጸልዩለት::

ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች /ቀሳውስት/ ወደ እርሱ ይጥራ:: በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት:: የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል:: እርስ በርሳችሁ በኃጢ አታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች /ያዕ. ፭.፲፬-፲፯/::

## ሕፃናት ወደጌታ ይመጡ ዘንድ ለተከለከሏቸው

ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሉአቸው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና:: እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይ ቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው:: አቀፋ ቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው:: /ማር. ፲.፲፬-፲፯/::

## ሊሠራ የማይወድ አይብላ

ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን:: እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደ ሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና በእናንተ ዘንድ ያለሥርዓት አልሄድንምና:: ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም:: ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም:: ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን እዘናችሁ ነበርና:: ሥራ ከቶ ሳይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና:: እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን:: እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራ አትታክቱ::

ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና ሊፈት ኑት:- ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት:: ኢየሱስ ግን መልሶ እንዲህ አለ፡ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፣ ዓለም:- ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም:: እግዚብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየውም:: እነ ርሱም:- እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥ ተው እንዲፈቱአት ስለምን አዘዘ? አሉት:: እር ሱም:- ሙሴ ስለልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም:: እኔ ግን እላችኋለሁ፤ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፣ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው::

ደቀ መዛሙርቱም:- የባልና የሚስት ሥር ዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም አሉት:: እርሱ ግን:- ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፣ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፣ ሰውም የሰለባቸው ጃንደ ረቦች አሉ፣ ስለመንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ:: ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው (ማቴ.፲፱፥፫—፲፪)::

መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፣ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚብሔር ይፈርድባቸዋል (ዕብ.፲፫፥፬)::

## በሥጋ ወደሙ መወሰን

ከምእመናን መካከል ለሰበካ መንፈሳዊ አስተ ዳደር ጉባኤ የሚመረጡት አባላት በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ እንዲሆኑ በቃለ ዐዋዲው ምዕ ራፍ ሦስት አንቀጽ ፲ ንኡስ አንቀጽ ፪ ፊደል (ለ) ቁጥር ፩ የተደነገገው የቅዱስ ወንጌልን ቃል መሠረት በማድረግ ነው::

ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው:: እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠ ጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ:: ሥጋዬ እውነተኛ መብል፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚ ጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ:: ሕያው አብ እንደላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል::

ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው አባቶ ቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይደለም ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘለዓለም ይኖራል (ዮሐ. ፮፥፶፫-፶፱)::

ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና:- እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ:: ጽዋንም አንሥቶ አመስ ግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ:- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው (ማቴ፳፮፥ ፳፮-፳፰)::

ወንድሞች ሆይ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ (ዕብራ. ፫፥፩)።

ክብር

ትምህርተ መስቀሉን
አርዌ ብርቱን ተመልከት

ለእግዚአብሔር

የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ። (ዕብራ. ፲፱፥፮-፱)

## አርዌ ብርቱን /የናሱን እባብ/ ያየ ዳነ

ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን፣ እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያየው በሕይወት ይኖራል አለው። ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ ዘኁል. ፳፩.፰-፱/።

## ያመነ በክርስቶስ መስቀል ዳነ

ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና (ዮሐ. ፫.፲፬-፲፮)።

**ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና (ማቴ. 7፥12)**

## ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ

ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል።

አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው። ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው (ያዕ. ፩.፳፪-፳፯)።

የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንስማ ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና፣ እግዚአብሔርን ፍራ ትእዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሠወረውንም ነገር ሁሉ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ወደ ፍርድ ያመጣዋልና። (መክ. ፲፪.፲፫-፲፬)።

## በእምነት በኩል ሁሉም እኩል ነው።

በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና (ገላ. ፫፥፳፮ -፳፰)።

## ማነው ታላቅነትን የሚወድ?

ምንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም። (ማቴ. ፳.፳፮-፳፰)።

በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ ሉቃ. ፪፥፲

## በመንፈስ ተመላለሱ

ወንድሞች ሆይ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና እርሱም ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፉ ተጠንቀቁ።

ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት ርኩሰት መዳራት ጣዖትን ማምለክ ምዋርት ጥል ክርክር ቅንዓት ቁጣ አድመኛነት መለያየት መናፍቅነት ምቀኝነት መግደል ስካር ዘፋኝነት ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአ ብሔር መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ደስታ ሰላም ትዕግሥት ቸርነት በጎነት እምነት የውሃትራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ። በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ (ገላ፭.፲፫ -፳፭)።

መንፈስን አታጥፉ ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ። (፩ኛ. ተሰ. ፭.፲፱-፳፪)።

## በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ (መክ. ፲፪.፩)።

ጎልማሳ መንገዱን በምን ያቀናል? ቃልህን በመጠበቅ ነው። በፍጹም ልቤ ፈለግሁህ፤ ከትእዛዝህ አታርቀኝ። አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ። አቤቱ አንተ ቡሩክ ነህ ሥርዓትህን አስተምረኝ (መዝ ፻፲፰.፱-፲፪)።

## መንፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያናት ምን ይላል?

በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል፡-


ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል እንዲሁም ሳይሆኑ፡- ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፤ ታግሥህማል፤ ስለስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም፡፡ ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና፡፡ እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና፡፡ እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ አለህ፤ እኔ ደግሞ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና፡፡ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፡፡ ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ (ራእ. ፪፥፩—፯)፡፡................

በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡-...........

በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ፡፡ በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር፡፡ እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው፡፡ ሀብታም ነኝና ባለጠጋም ሆኜ አለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለሆንህ፤ ጎስቋላና ምስኪንም ድሀም እውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፤ ባለጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፤ ተገናጽ ፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፤ እንድታይም ዓይኖችህም የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ፡፡ እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ፡፡ እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምጼን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፤ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል፡፡ እኔ ደግሞ ድል እንደነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ ፤ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ፡፡ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ (ራእ.፫፥ ፲፬—፳፪)፡፡



131




## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር
## በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አጠቃላይ መዋቅር

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ